## የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ጥናት ክፍል ሁለት

**ማስታወሻ፡-**

ይህ የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ክፍል ሁለት ከክፍል አንድ (ሐዋ. ሥራ 1-12) የቀጠለ ሲሆን ጥናቱ ከሐዋ. ሥራ 13-28 ምዕራፎች መሠረት ያደረገ ሆኖ ሃያ ሁለት ጥናቶች አሉት። እነዚህ ከ13-28 ያሉት ምዕራፎች ሐዋርያት ከ3-4 በሚሆኑ ዓለም አቀፍ የወንጌል ጉዞዎች ቤተ ክርስቲያንን እንዴት እንደመሠረቱ፣እንደጎበኙና እንዳጸኑ ያስተምራል። እንደሚናውቀው የታሪኩ ጸሐፊ ሐኪሙ ሉቃስ ሆኖ እግዚአብሔር በወንጌላት የተናገረውን ሰዎችን ከጨለማ ዓለም የማዳን ተልዕኮ (ማቴ 28:19-20፣ሐዋ.ሥራ 1:8) የፈጸመበትና ለዛሬውም አብያተ ክርስቲያናት እጅግ በጣም ጥሩ የሆኑ መርሆችን የሚያስተምር መጽሐፍ ነው።

ከተዘጋጁት ከሃያ ሁለቱ ጥናቶች ከመጀመሪያ ያሉት ሶስቱ ጥናቶች በሶስት ርዕሶች ላይ ያተኮረ ይሆናል። ይህም በሐዋርያት ሥራ 13:1-3 እና በኤፌ 4:11-13 አምስቱ ቢሮዎች መሠረት በማድረግ በዚህ ዘመን በአብያተ ክርስቲያናት ብዙ አነጋጋሪ የሆኑትን በተለይም ሶስቱን ቢሮዎች ማለትም ስለ ሐዋርያት፣ ስለ ነቢያትና ስለ አስተማሪዎች እንድናጤን የሚረዳን ይሆናል። በተረፈው የተቀሩት አስራ ዘጠኙ ጥናቶች በሐዋ. ሥራ ከ13-28 ምዕራፎች የተዘጋጀ ይሆናል። “ቢሮዎች” የሚለው ቃል እንደ ቤተ ክርስቲያን አቅምና በጀት የሙሉ ጊዜ **አገልጋይን የሚፈልግ የአገልግሎት ጸጋ ማለት ይሆናል።**

**ጥናት አንድ**

**ከአምስቱ የቤተ ክርስቲያን የጸጋ ስጦታዎች (ቢሮዎች)**

**ሐዋርያት ወይም የሐዋርያነት ስጦታ**

የንባብ ክፍል፡- 1ቆሮ 12:12-31፣ሐዋ. ሥራ 13:1-3፣ኤፌ 4:11-13 ሌሎችም

**ርዕስ፡-** የሐዋርያነት የጸጋ ስጦታ ምንነትና አገልግሎታቸው ወይም ተግባራቸው

**ዓላማ፡-** የሐዋርያነት የጸጋ ስጦታ ምንነታቸውንና ተግባራቸውን በተመለከተ የተሻለ እውቀትና ግንዛቤ እንዲኖረን ታስቦ የተዘጋጀ፡-

**መግቢያ፡-**

ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ አካል ናት። አማኝ በዚህች የክርስቶስ አካል ውስጥ ብልት ሆኖ በልዩ ልዩ ጸጋዎች ይገለገላል፤ያገለግላልም። ጌታችን ኢየሱስ ካረገም በኋላ አካሉን አልተዋትም፤ነገር ግን በመንፈስ ቅዱስ ልዩ ልዩ የጸጋ ስጦታዎችን በመስጠት ይመግባታል፣እንዲሁም ያንጻታል፤ወደ እርሱም ያቀርባታል (ኤፌ 4:6-13። ይህ እውነት ደግሞ በተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ተጽፎ እናገኛለን (ለምሳሌ 1ቆሮ 12-14፣ ሮሜ 14፣ 1ጴጥ 4:8-10፣ ሐዋ. ሥራ 13:1-3 እና ሌሎችም)።

**ይህ ጥናት ለምን አስፈለገ?** በዚህ ዘመን በአብያተ ክርስቲያናትና በአማኞች መካከል በሐዋ.ሥራ 13:1-3፣1ቆሮ 12:28-31፣በኤፌ 4:11-13 እና ሌሎችም ክፍሎች ከተጠቀሱት የመንፈስ ቅዱስ የጸጋ ስጦታዎች አንዱ ስለሆነው ስለ ሐዋርያ ወይም ስለ ሐዋርያነት ስጦታ ብዙ መደነጋገርና አለመስማማቶችም ሰፍኖ እናገኛለን። ይህንን ችግር ደግሞ ሚዲያው በጣም አግዝፎታል። ስለዚህ ይህ ጥናት የክርስቶስ አካል ከዚህ ጸጋ የጎደለች እንዳትሆንና ከእነዚህ ከተለያዩ ስህተቶችም እንድትጠበቅ 1) ሐዋርያ ትርጉሙ ምንድ ነው? 2) ሐዋርያ ማን ነው? 3) አገልግሎቱስ ምንድ ነው? 4) በዛሬስ ዘመን ሐዋርያ አለ ወይ? 5) መለኪያውስ ምንድ ነው? ለሚሉትና ለሌሎችም ጥያቄዎች መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይለናል የሚለውን ከራሱ ከቃሉ እናያለን።

**ሐዋርያ ወይም የሐዋርያት ጸጋ ወይም ቢሮ**

I. **ሐዋርያ ወይም ሐዋርያት ምንድ ነው?** ሐዋርያ የሚለው ቃል አዲስ ኪዳን በተጻፈው የግሪክ ቋንቋ «አፖስቶሎስ» የሚል ሲሆን ትርጉሙም ለአንድ ዓላማ «የተላከ» ማለት ነው፡፡ ቃሉ በብሉይ ኪዳን ብዙም የማይታወቅ ቢሆንም በዕብራይስጥ “ሻሊያ” ማለትም ወኪል የሚለውን ጽንስ ሀሳብ የሚይዝ ሲሆን በአዲስ ኪዳን ግን ቃሉም ይሁን አገልግሎቱ ግልጽ ሆኖ ተቀምጧል። ትርጉሙ “የተላከ” ሲባል ላኪውን በመወከል የላኪውን መልእክት ብቻ በትክክል የሚያስተላልፍ መልእክተኛ ማለት ነው፡፡ ቃሉ በግሪክ ባህልና ቋንቋ ውስጥ ማንኛውንም ዓይነት መልእክተኛ የሚያመለክት ቢሆንም በአዲስ ኪዳንም ይሁን በጥንቷ ቤ/ክን ግን በዋናነት የሚያገለግለው እግዚአብሔር ለድነት አዋጅ የላካቸውን ብቻ ነው፡፡ ሐዋርያት የሚለው ቃል በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ብዙ ቦታ ተጠቅሶና በተግባርም ተከናውኖ እናገኛለን (ሐዋ ሥራ 1፡ 26፣ 2:37፣ 5:41፣ 8:18፣ 14:18)።

II. ሐዋርያ ማን ነው?

1. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ (የሁሉ ጀማሪና መሪ)

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሃይማኖታችን (የእምነታችን) ሐዋርያ እንደሆነ ቃሉ ይናገራል «... የሃይማኖታችንን (የእምነታችንን) ሐዋርያና ሊቀካህናት ኢየሱስ ክርስቶስን ተመልከቱ» (ዕብ.3፡1)። ይህም ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ <u>**ራሱ በሰውነቱ ሐዋርያ እንደሆነ የሚናገር ቃል**</u> ነው፡፡ በእርግጥም ኢየሱስ እርሱ ስለራሱ ሲናገር «... እርሱ [አባቱ] ልኮኛልና አውቀዋለሁ» በማለት እና «እርሱ [አባቱ] ላከኝ እንጂ ከራሴ አልመጣሁምና» በማለት ከአብ ዘንድ የተላከ መሆኑን በግልጽ ተናግሯል (ዮሐ.7፡28፤ 8፡42)፡፡ እርሱ በሰውነቱ የሚናገረውም ሆነ የሚያደርገው ሁሉ ከአብ የሰማውንና አብን ደስ የሚያሰኘውን ብቻ ነበር፤ ይህንንም ሲገልጽ «... ዳሩ ግን የላከኝ እውነተኛ ነው፤ እኔም ከእርሱ የሰማሁትን ይህን ለዓለም እናገራለሁ፤ .... አባቴም እንዳስተማረኝ እነዚህን እናገር ዘንድ እንጂ ከራሴ አንዳች እንዳላደርግ በዚያን ጊዜ ታውቃላችሁ...» (ዮሐ.8፡26-30) ብሏል። ይህ ደግሞ የሐዋርያን መሰረታዊ ትርጉምና ተጠያቅነትን ያሚላል።

2. አሥራ ሁለቱ ሐዋርያት

በወንጌላት 12ቱን ሐዋርያት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሾማቸው፣ ኃይልና ሥልጣን እንደሰጣቸውና እንዲሁም <u>**እንደላካቸው**</u> ይናገራል (ማር 3:13-19፣ማር 6:7-13፣ ሉቃ 6:12-16፣ሉቃስ 9:1-2፣ ማቴ 10:1-4)። የመረጣቸውና የላካቸው እራሱ ክርስቶስ ነበር። ይህ አሁንም ለሐዋርያ ያለውን ትርጉምና ተጠያቅነትን ያሚላል። አስራ ሁለቱ ሐዋርያት ተልከው ወደ ዓለም ሁሉ ወንጌልን አድርሰዋል፣ጀምረዋል፣መርተዋል። በእርግጥ ማወቅ የሚገባን ነገር ቢኖር እነዚህ አስራ ሁለቱ ሐዋርያት "የበጉ ሐዋርያት" ተብለው የሚጠሩ ሲሆን ብዙዎቹን የአዲስ ኪዳን ቅዱሳን መጽሐፍትን የጻፉና የጥንቷንም ቤተ ክርስቲያን የመሩ ነበሩ (ሐዋ ሥራ 15:1-10)። ከእነርሱ በኋላ ሐዋርያት ከተባሉት በዋናነት እንዲለዩ የሚያደርጋቸው ነጥብ ይህ ነው።

**3. ሐዋርያው ጳውሎስ**

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ካረገ በኋላም ሐዋርያው ጳውሎስን ሐዋርያ አድርጎታል ወይም በሐዋርያነት ጸጋ ቀብቶታል። ማለትም የሐዋርያነት ጸጋ ከበጉ ሐዋርያትም በኋላ ቀጥሏል። ሐዋርያው ጳውሎስ በሚከተሉት ጥቅሶች ሐዋርያ ተብሉ ተነግሯል ( ሮሜ 1:1 "ጳውሎስ፣ የክርስቶስ ኢየሱስ ባሪያ፣ ሐዋርያ ሊሆን የተጠራና ለእግዚአብሔር ወንጌል የተለየ" ወይም የተላከ ነው (1ቆሮ 1:1፣ ቆላ 1:1፣ 2ቆሮ 1:1፣ ቲቶ 1:1-2)።

እራሱ ሐዋርያ ስለራሱ ጥሪ ሲመሰክር እንደሚከተለው ይላል "እኔም ለዚህ ነገር <u>የምሥራች አብሣሪና ሐዋርያ</u> እንዲሁም ለአሕዛብ የእውነተኛ እምነት አስተማሪ ሆኜ ተሾምሁ፤ እውነቱን እናገራለሁ፤ አልዋሽም" (1 ጢሞ 2:7)። ለዚህ ቃል ትኩረት ከሰጠን ለወንጌል አብሣሪነት የተጠራ መሆኑ ግልጽ ነው (ሐዋ ሥራ 9:15 ማንበብ ይቻላል)።

4. ሌሎችም ሐዋርያት ነበሩ

ከሐዋ ሥራ 13:1-3 ከተጠቀሰው በተጨማሪ በሮሜ መልዕክት ምዕራፍ 16 ከተዘረዘሩ 29 አገልጋዮች መካከል ሐዋርያት እንደነበሩ ይነገራል ለምሳሌ 16:7 እንዲህ ይላል "ከእኔ ጋር ታስረው ለነበሩና በሐዋርያትም መካከል ታዋቂዎች ለነበሩት አይሁድ ዘመዶቼ፥ ለአንድሮኒቆስና ለዩኒያስ ሰላምታ አቅርቡልኝ፤ እነርሱ በክርስቶስ በማመን እኔን ይቀድሙኛል"። የሐዋርያት ሥራ 14:14 ደግሞ በርናባስም ሐዋርያ እንደሆነ ይናገራል "ሐዋርያቱ ጳውሎስና በርናባስ ግን ይህን በሰሙ ጊዜ በሐዘን ልብሳቸውን ቀደዱ" ይላል። እንዲሁም ስለ ሌሎች በ1 ተሰሎንቄ 2:7 እንደሚከተለው ይላል "የክርስቶስ ሐዋርያት

እንደ መሆናችን አስፈላጊውን ከእናንተ ለመጠየቅ እንችል ነበር…”፡፡ይህ ደግሞ ሐዋርያው ጳውሎስ ከእርሱ ጋር ሐዋርያት እንደነበሩ ያሳያል፡፡

**5. የጥንቷ ቤ/ክ አሰራርና ምስክርነት**

ከአስራ ሁለቱ የበጉ ሐዋርያት በተጨማሪ የአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች በሐዋ. ሥራ 13:2-3 እንደተገለጸው መሪዎች ሐዋርያትን ሲሾሙና ሲልኳቸው እናያለን “እነዚህም ጌታን እያመለኩና እየጾሙ ሳሉ፣ መንፈስ ቅዱስ፣ “በርናባስንና ሳውልን እኔ ለጠራኋቸው ሥራ ለዩልኝ አለ፡፡ 3 እነርሱም ከጾሙና ከጸለዩ በኋላ እጃቸውን ጭነው አሰናበቷቸው፡፡” ይህ ቃል እንደሚነግረን ሐዋርያው ጳውሎስ ስለ ሐዋርያነቱ የአጥቢያ ቤ/ክ መሪዎች ምስክርነት አስፈላጊ ነበር፡፡ እግዚአብሔር በግሉ በድምጽ የተጠራው ቢሆንም በመሪዎችም ዘንድ በጸሎት ጊዜ ተጠርቷል፡፡ የቤተ ክርስቲያን ምስክርነት ወሳኝ ነው፡፡ የአዲስ ኪዳን ሐዋርያት አንዱ ለአንዱ ተጠያቅነት ነበረባቸው፡፡ በጥንቷ ቤ/ክንም “ሐዋርያት ሳይሆኑ ሐዋርያት ነን የሚሉ” ነበሩ (በራእ.2፡2 ላይ «ሐዋርያት ነን የሚሉቱን መርምረህ ሐሰተኞች ሆነው እንዳገኘሃቸው አውቃለሁ» በማለት ጌታ ኢየሱስ በኤፌሶን ወዳለው ቤተክርስቲያን መልአክ የላከውን መልእክት እናነባለን፡፡ ጌታ ኢየሱስ በኤፌሶን ባለች ቤተክርስቲያን ካገኛቸው መልካም ነገሮች መካከል አንዱ ሐዋርያት ነን የሚሉትን መርምሮ ሐሰተኞች መሆናቸውን ማረጋገጡ ነበር፡፡ በዚያ በሐዋርያት ዘመን ከነበሩት የሐሰት አስተማሪዎች መካከል ብዙዎቹ ሐዋርያት ሳያዝዟቸውና ሳይልኳቸው ሐዋርያት አዝዘውናል ወይም ልከውናል በማለት በተለያዩ ከተሞችና መንደሮች በሚገኙ አጥቢያ ጉባኤያት እየዞሩ ተቀባይነት ለማግኘት ይሞክሩ ነበር (የሐዋ. ሥራ15፡24)፤ ይህ አልሳካ ያላቸው ደግሞ እንደ ክርስቶስ ሐዋርያት ተቀባይነትን ማግኘት ይችሉ ዘንድ በድፍረት «ሐዋርያት ነን» ይሉ ነበር፡፡ ይህንንም በተመለከተ ሐዋርያው ጳውሎስ ሲጽፍ «... እንደ እነዚህ ያሉ ሰዎች የክርስቶስን ሐዋርያት እንዲመስሉ ራሳቸውን እየለወጡ፣ ውሸተኞች ሐዋርያትና ተንኰለኞች ሠራተኞች ናቸውና፡፡ ይህም ድንቅ አይደለም፤ ሰይጣን ራሱ የብርሃንን መልአክ እንዲመስል ራሱን ይለውጣልና፡፡ እንግዲህ አገልጋዮቹ (የሰይጣን አገልጋዮች) ደግሞ የጽድቅን አገልጋዮች እንዲመስሉ ራሳቸውን ቢለውጡ ታላቅ ነገር አይደለም፤ ፍጻሜያቸውም እንደ ሥራቸው ይሆናል» (2ቆሮ.11፡13-15) ብሏል፡፡ ከዚህም እንደምንረዳው እነዚህ ሰዎች «ሐዋርያት ነን» የሚሉ ብቻ ሳይሆኑ የክርስቶስን ሐዋርያት እንዲመስሉ ራሳቸውን የሚለውጡ ተንኰለኞች ሠራተኞች ነበሩ፡፡ በቆሮንቶስ በነበሩ አማኞች መካከል ብዙ ዓይነት መንፈሳዊ ውድቀት በመኖሩ ለእነዚህ ውሸተኞች ሐዋርያት የሐሰት ትምህርት የተጋለጡ ሰዎች እንደነበሩ ከ2ኛ ቆሮ.11 እንረዳለን፤ ሐዋርያው ጳውሎስ ግን እነዚህን ሰዎች የሰይጣን አገልጋዮች እንደሆኑ በመግለጥ ሥራቸውንም ሰይጣን የብርሃን መልአክ እንዲመስል ራሱን ከመለወጡ ጋር እያነጻጸረ ማንነታቸውን በመግለጥ በክፉ ትምህርታቸው የተታለሉትን ሁሉ በብርቱ ይወቅሳቸዋል፡፡

6. የአሁን ዘመን ሐዋርያነት (ሐዋርያ)

በዚህም ዘመን ያሉትም አብያተ ክርስቲያናት እንደ ቃሉ የጥንቷን ቤ/ክ አሰራር መሠረት በማድረግ የሐዋርያናት ጸጋ ያለባቸውን አገልጋዮችን በመለየት ማሰማራት ያስፈልጋል፡፡ አገልጋዮችም ራሳቸውንም ለእውነተኛ ጥሪና ለመሪዎችም መስጠት አለባቸው፡፡

የዚህ ጥናት ሙሉ ግንዛቤ፡- በአሁን ጊዜ ስለ ሐዋርያና የሐዋርያነት ጸጋ የተለያዩ አመለካከቶች እና ትግበራዎች ቢኖሩም ይህ ጥናት እንደሚከተለው ያምናል፣እንዲተገበርም ያበረታታል፡፡

1. ሐዋርያ ማለት “ለወንጌል ስብከትና ለቤተ ክርስቲያን ምስረታ ከእግዚአብሔር የተላከ” ነው የሚለውን ትርጉም በጽኑ ያምናል።
2. በ1ቆሮ 12:28-31 እና ኤፌ 4:11 መሠረት ዛሬም የሐዋርያነት የጸጋ ስጦታ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንዳለና አማኞችም ማመንና የተጠሩትም እራሳቸውን እንዲሰጡ እንደ ቃሉ መተግበር እንዳለበት
3. በእግዚአብሔርና በቤተ ክርስቲያን ምስክር ፊት የተጠራና የተመሰከረለት ሊሆን ይገባል (ሐዋ. ሥራ 13:1-3)
4. ሐዋርያነት እንደመጋብነት በአንድ ቦታ የመቀመጥ ጸጋ ሳይሆን እየዞረ ወንጌል ሰባኪ፣ጀማሪ፣መሪና አስተማሪ ሆኖ ህብረቶችንና አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናትን መሥራችና ተመልሶም የሚጎበኝ አገልጋይ ነው።
5. ለተጠያቅነት ራሱን የሚሰጥ ባሪያ፣ሌሎችን አክባሪና ከሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ጋር ጥሩ ህብረት ያለው መሆነ ይገባል።
6. በአሁኑ ዘመን በአብያተ ክርስቲያናት ባሉት በተለያዩ ኢ-መጽሐፍ ቅዱሳዊ አሰራሮችና ችግሮች ምክንያት ባይሾሙም ሐዋርያ ነኝ ወይም የሐዋርያነት ጸጋ አለን የሚሉ አገልጋዮች ሁሉ በግልጽ በወንጌል ስብከትና በቤ/ክን ተከላ በፍሬያቸው የተመሰከረላቸው ሊሆኑ ይገባል።

**ትኩረት**፡- በልዩ ልዩ የግል ጥቅሞች ላይ ሳይሆን በእግዚአብሔር ወንጌል ተልዕኮ ላይ መሆን አስፈላጊ ነው።

በዚህ ላይ ማወቅ የሚገባን ሌላው ነገር አልፎ አልፎ ቤተ ክርስቲያን ተከላ ወይም ምስረታ የተሳተፉ ወይም እየተሳተፉ ያሉ ሁሉ “ሐዋርያት” ወይም “ሐዋርያ” ሊሆኑም ላይሆኑም እንደሚችሉ ማወቅ ጥሩ ነው። ለምሳሌ አልፎ አልፎ የተነበየ ሁሉ ነብይ አይደለም። ይህ የሚጣረው በቤተ ክርስቲያን መሪዎችና በራሱም መሰጠት ነው። ትህትና እጅግ አስፈላጊ ነው። የመጽሐፍ ቅዱስ መመዘኛ ማለፍ አለበት። ትምህርቱ፣ትግበራውና ሥነ ምግባሩ እንደ ቃሉ መሆን አስፈላጊ ነው።

የመወያያ ጥያቄዎች

1. የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ ምንድ ነው? ሐዋርያ ማለት ምን ማለት ነው?
2. ዕብራዊያን 3:1 በማንበብ ማን ሐዋርያ እንደሆነ አብራሩ።
3. የዮሐ 7:28 እና 12፡49-50 ያለውን የክርስቶስን አገልግሎት ስናይ ከላይ “ሐዋርያ” ከሚለው የቃሉ ትርጉም ጋር እንዴት ይገናኛል?
4. ክርስቶስ በጸሎት የጠራቸው ሐዋርያት እነማን ናቸው (ማርቆስ 3:13-19፣ ሉቃስ 6:12-16)?
5. ሉቃስ 9:1-2 እና ማቴ 10:1-4 ስናነብ የሐዋርያትን አገልግሎት ስናይ ከ”ሐዋርያ” የቃሉ ትርጉም ጋር ምን ግንኙነት አለው?
6. ሐዋርያው ጳውሎስን የጠራው ማን ነው ለምን (ሐዋ. ሥራ 9:151ጢሞ 2፡ 7)፤በአገልግሎቱስ የዚህ ጥሪ ፍሬ ይታያል? እንዴት?
7. በኤፌ 4:11 እና በ1ቆሮ 12:28 መሠረት ለቤተ ክርስቲያናት ከተሰጡ ጸጋዎች መካከል አንዱ ምንድ ነው? አካፍሉ።
8. **ራዕይ 2:2 እና 2ቆሮ 2:13** በማንበብ የተረዳችሁትን አብራሩ።ይህ ችግር ዛሬም ይኖራል? ይብራራ።
9. በዛሬው ጥናት መሠረት አንድ አገልጋይ “ሐዋርያ” ነው ብሎ ለመመስከር ምን ምን ያስፈልገዋል ወይም መመዘኛው ምንድ ነው? እንዴትስ እንለየዋለን? ተወያዩ።

መ ደ ም ደ ሚ ያ፡-

በዚህ ዘመን ሐዋርያትና የሐዋርያነት ጸጋ በቤተ ክርስቲያን ይሰራልን? ለሚለው ጥያቄ በዚህ ጥናት መሠረት መልሱ አዎን ሲሆን፣ መሆንና መተግበር ያለበት ግን የእግዚአብሔር ቃል እንደሚያስተምረን ብቻ ነው።

ጥናት  ሁለት

## ነቢይ ወይም የነቢይነት ጸጋ

## የጥናቱ ርዕስ፡- የነቢያት ምንነትና አገልግሎታቸው ወይም ተግባራቸው

## የንባብ ክፍል ፡- ሐዋ. ሥራ 13:1-3፣1ቆሮ 12:4-8 ፣ኤፌ 4:11-13  ሌሎችም

**የጥናቱ ዓላማ**

1. የነቢይነት ምንነት እና አገልግሎትን እንደ እግዚአብሔር ቃል ለመቃኘት
2. የነቢይነት አገልግሎት በጥንቷ እና በአሁኗ ቤተ ክርስቲያን እድገት ላይ ያላቸውን አስተዋጾ ለማሳየት
3. እውነተኛ እና ሃሰተኛ ነቢያትን በቃሉ መሥፈርት መመዘን እንድንችል ለማስገንዘብ
4. በዚህ ዘመን በኢትዮጵያ ወንጌላዊያን አብያተ ክርስቲያናት ያለውን እንቅስቃሴ ሚዛናዊ በመሆነ መንገድ ለመፈተሽ

## I. መግቢያ

***በቤተ ክርስቲያን ታሪክ በአሁንም ዘመን ጭምር ከየትኛውም የጸጋ ስጦታ ይልቅ አብያተ ክርስቲያናት እየተቸገሩ ያሉት በትንቢት ስጦታ ወይም በነቢይነት ቢሮ ነው። ይህ ጸጋ ከብዙ ፈተናዎች ጋር የተያያዘ ነው። ምክንያቱም ከሰዎች የየዕለትና ዘላቂ የሥጋና መንፈሳዊ ችግሮች ጋር የተገናኘ ነው። በዛሬው ዘመን ደግሞ የበለጠ ሚዲያው አግዝፎታል። በ1ኛ መቶ ክፍለ ዘመንም መሪዎች ኃላፊነት ወስደው እንዳገለገሉ ዛሬም ቢሆን ቸል ልንል አይገባም።ይህ ችግር በአፍርካ የገነነ ሆኖ ይታያል። ይህ ማለት ደግሞ በእግዚአብሔር ቃል ያልተጻፈና አብያተ ክርስቲያናትም ያልተቀበሉት  ሆኖ ሳይሆን የአተረጓጎም፣የአያያዝና የአፈጻጸም ወይም አተገባበር ችግር ነው። ይህ ስጦታ በበሐዋ.ሥራ 13:1-3፣በኤፌ 4:11 እና በ1ቆሮ 12:4-8 እና በሌሎችም ክፍሎች ከተጻፉት ለክርስቶስ አካል መታነጽ ከተሰጡ የጸጋ ስጦታዎች አንዱ ነው። ለሰዎች መዳንም ይሁን መታነጽ ምክንያት እየሆነ ያለ ጸጋ ነው። ይህንን ጸጋ በትክክል መጠቀም እንድንችል በዚህ ጥናት የትንቢትንና የነቢይነትን የጸጋ ስጦታ ወይም ቢሮ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትርጉም፣ምንነት፣ አተገባበርና መለኪያውንም ጭምር እናያለን።***

## II. ነቢያት እና አገልግሎታቸው

- **ነቢይነት ትርጉምና ምንነት**

**1) በብሉይ ኪዳን**

- አንደኛው ሮኢ (Roeh) የሚል ሲሆን ትርጓሜውም  ባለ ራዕይ እና ወደ ፊት የሚሆነውን አስቀድሞ የሚያይ ማለት ነው።
- ኮዜህ ( Chozeh)ማለትም በራዕይ የሚያይ የሚመለከት፣የሚያስተውል ማለት ነው።
- ነቢይ (Na’bi) እግዚአብሔርን ወክሎ የእግዚአብሔርን ቃል የሚያውጅ ማለት ነው።

**2) በአዲስ ኪዳን**

- ነብይ ለሚለው ስም አዲስ ኪዳን ፕሮፌት (Prophet) የሚለውን የግሪክ ቃል ይጠቀማል።
- ትርጉሙ ወደፊት ሊመጣና ሊከሰት ስላለ ነገር አስቀድሞ የሚናገር ማለት ነው።

- ፕሮፌት (Prophet የሚለው ቃል በብሉይ ኪዳን እና በአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ 95 ጊዜ ያህል ተጠቅሶ እናገኘዋለን

3) ነቢይነት በተለያየ አጠራር

- ከእግዚአብሔር ተቀብሎ ለሕዝብ የሚናገር
- የእግዚአብሔር ሰው፡- **1ኛሳሙ.9:6**
- ባለ ራዕይ፡- **1ኛሳሙ.9:9**
- የእግዚአብሔር ባሪያ፡ **2ኛ ነገ.24:2**

**III. ነቢይነት በሁለቱም ኪዳኖች**

**1. በእግዚአብሔር ውሳኔ ስለሚፈጸሙ ድርጊቶች**

1) ስለ መንግሥት፣
2) ስለ ሰዎች
3) ስለ ኃጢአት የሚናገሩ

2. ወደፊት ስለሚሆኑት ድርጊቶች የእግዚአብሔር ቃል ምሳሌ ወይም በድርጊት ይገልጡ ነበር (**ኢሳ. 5:1-7፣ ኤር 19፡1-9 1ሳሙ 10:5-10፣ 1ነገስ 22:8--10**

3. በተለይም በብሉይ ኪዳን ለነቢያት ትምህርት ቤትና ደቀ መዛሙርት ነበሯቸው፡- **1ኛሳሙ.19:20፣ 2ኛነገ. 2:3፣ ኢሳ. 8:16**

- የነቢያት ትንቢት የጻፉ ይመስላል
- ራሳቸው ነቢያት የታሪክ መጽሓፍትን ጽፈዋል፡- **2ኛዜና 9:29፣ 32:32**
- የእግዚአብሔር ቃል ያስተላልፉ ነበር፡- **1ኛነገ.13:11-25**

**4. የብሉይ ኪዳን ነቢያት አገልግሎት ትኩረት**

- አስተምህሯቸውና ዓላማቸው የሰራዊት አምላክ እግዚአብሔርን በመወከል ማገልገል፣ሕጉን ማስተማርና መለኮታዊ ምሪት መስጠት ነበር፣
- ሰዎች ለሚያስፈልጋቸው አካላዊ ፣አእምራዊ እና መንፈሳዊ ፍላጎት ወይም ችግሮች መተንበይ፣ተአምራቶችን ከእግዚአብሔር ዘንድ እንዲወርድ ከእግዚአብሄር ጋር መገናኘትና ማገልገል
- ሕዝቡን መምከር፣መገሰጽና ሕጉን ማስጠበቅ፣
- ስለ መጻኢ ዘመን (ስለሚመጣው ዘመን) አስቀድሞ መናገር

**5. የአዲስ ኪዳን ነቢያት አገልግሎት ትኩረት:- የሐዋርያት መጽሐፍ ሐዋ. ሥራ .13:1-3 ኤፌ 4:11-13**

- ከእግዚአብሔር ድምጽና ምሪት መስማት
- ኢየሱስ ክርስቶስን ማዕከል አድርገው የሚያገለግሉ
- የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች

- ከአንድ አጥቢያ የወጡ ነገር ግን በአንድ አጥቢያ ብቻ የማይወሰኑ
- ቤተ ክርስቲያን ተከላ እና እድገት ላይ ከሌሎች ጋር አብረው የሚሠሩ
- ቃሉን በሥልጣን እና በጥልቀት የሚያስተምሩ
- በእግዚአብሔር ተጠርተው በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ጥሪያቸው ተረጋግጠው የሚሾሙ

**IV. የትንቢት ተናጋሪዎች እና የነቢያት አገልግሎት**

1. **ትንቢት የተናገረ ሁሉ ነብይ አይደለም ነገር ግን ነብይ ሁሉ ግን ትንቢት ሊናገር ይችላል ፡- 1ኛቆሮ.12:4-11**

- አልፎ አልፎ ወይም ለአንድ ጊዜ ብቻ ትንቢት የተናገሩ
  - የእስራኤል ሽማግሌዎች **ዘኁ.11:25**
  - ኤልዳድና ሞዳድ **ዘኁ.10:26**
  - ሳኦል **1ኛሳሙ.19:20**
  - በአዲስ ኪዳን ኤልሳቤጥ **ሉቃ.1:42-45**፣ ማሪያም **ሉቃ.1:45-55** ዘካሪያስ **ሉቃ.1:66-79** እና ስምዖን **ሉቃ.2:25-35**

2. **ነቢይነት ትንቢት ከመናገር ባለፈ ስለ መጪው ዘመን**

- **መደበኛ ጸጋ ወይም ለአንድ ጊዜና አልፎ አልፎ የሚከሰት ያልሆነ**
- የሚናገሩና የሚያስተምሩ፣
- የሚገስጹ… የብሉይ ኪዳን ታላላቅ እና ታናናሽ ነብያቶች ፣ **ሐዋ.11:27፣ 15:32**

**V. የሀሰተኛ ነቢያትን መለያ**

- **በመለኮታዊ ስልጣን ሳይሆን በራሳቸው አሳብ፣ ስሜት እና ፍላጎት መናገር፡-** ኤርሚያስ 23፡16፥21፡25 ሕዝቂኤል 12፡2
  - ለሰዎች ስሜትና ፍላጎት (ት.**ኤር 6፡14፤28፡17 ት.ሕዝ 13፡1)**
  - ለራሳቸው ክብር እና ተቀባይነት ለማግኘት:-( **1 ነገስት 22፡8፣ 2ኛ ጢሞ 4፡3-4)**
  - በድነት ጉዳይ ላይ የኢየሱስ ማንነት እና ጌትነትም ይክዳሉ እንዲሁም በመስቀል ላይ የተከፈለውን ሥራም ይክዳሉ (**2ጴጥ 2፡1፣ 1 ዮሐ 4፡2-3)**

1. **መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነት እና የቃሉን ስልጣን መካድ**
   - የመጽሐፍ ቅዱስን ስልጣን መናቅ
   - በቅዱሳን መካከል ልዩነትን መፍጠር (**ኤርሚያስ 23፡2፤14 ፣ 2ጴጥሮስ 2፡2)**
   - በተቻላቸው መጠን ሰዎችን ከእውነተኛ ወንጌል ለማራቅ መጣር (**የሐዋ. ሥራ 13፡8)**
   - አማኞችን በትምህርታቸው ለማሳሳት ጥረት ማድረግ (**ማርቆስ 13፡22፣ 1ኛ ጢሞ 4፡6፣ 2ኛጢሞ4፡6፣ 2ኛጢሞ 4፡3 ቲቶ1፡9፤2፡1)**
2. **ኢ-መጽሐፍ ቅዱሳዊ በሆነ ባህርያት እና ጠባይ ማሳየት**

- ትዕቢት ፦**2ኛጴጥሮስ 2፡1** ስስትነት፦ (ት.**ኤር 8፡1 ቲቶ 1፡11 2ኛጴጥሮስ 2፡3፡14)**
- ዓመጸኝነት እና የኃጢአት ልምምድ ፦ (**ኤርሚያስ 23፡11፥14፤ 2ኛጴጥሮስ 2፡14)**
- *ሥጋዊነት* (**2 ጴጥ 2፡1 ቁ.12 ፤3፡3)**
- በድካምና በጥፋት ውስጥ የሚነዱትን ያስታሉ (**2ጢሞ.3፡6-7፣ 2ኛ ጴጥ 2፡14፤13)**
- እግዚአብሔር እናውቃለን ይላሉ ነገር ግን በሥራቸው የሚክዱ፦ (**ማቴዎስ 7፡2-23፣ 2ጢሞ 3፡5፣ቲቶ 1፡16)**
- *ሥ*ልጣንን ለሥጋቸው ፈቃድና ደስታ ማዋልና ለማንም አለመታዘዝ (**2 ጴጥሮስ 2፡10)**

3. **ከእግዚአብሔር አምላክ ውጪ አምልኮ እና ስግደት መስጠት ወይም ጣኦትን ማምለክ፦ ዘዳ.13:1-8**

***የመወያያ ጥያቄዎች***

1. ***የዚህ ጥናት ዓላማው ምንድ ነው? ከመግቢያ ጹሑፍስ ምን ተረዳችሁ?ተወያዩ።***
2. ***ትንቢትና ነቢይነት ማለት ምን ማለት ነው?***
3. **1ሳሙ 10:10-11፣ 1ሳሙ 19:20፣ 1ነገስ 18:4-13,18:22፣ሐዋ.** *ሥራ* **11›28፣ 21:10** ***መሠረት በብሉይም ይሁን በአዲስ ኪዳን ነቢያትና የነቢይነት አገልግሎት ነበረ? ተወያዩ።***
4. የብሉይ ኪዳን እና የአዲስ ኪዳን ዘመን ነቢያት አንድነታቸው ምንድ ነው? ማን የሚሰጣቸው? የማን አፍና ወክል ናቸው? ስለዚህ ተጠያቅነታቸውስ?
5. **1ቆሮ 12:4-10፣ 1ቆሮ 14:29-39፣ ኤፌ 4:11** ***በማንበብ ምን እንደተረዳችሁ አካፍሉ።***
6. **1ቆሮ 13:1-3** ***በማንበብ ከትንቢትና ከነቢይነት አገልግሎት ጋር ምን ግንኙነት አለው? የእውነተኛ ነብይ መለኪያ ልሆን ይሽላል? ስለዚህ ምን እናድርግ?***
7. 2ጴጥ 2:2፣ 1ጢሞ 4:1 **በማንበብ** የሃሰተኞች መለያ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምልክታቸውን በመጥቀስ ተወያዩ
8. 1ዮሐ 4:1፣ 1ተስሎንቄ 5:20-21 በነብይ አገልግሎት እና በትንቢት መልዕክት የቤተ ክርስቲያን እና የአማኞችን ድርሻ እንደ ቃሉ ይወያዩ

በአሁን ዘመን በሃበሻው አብያተ ክርስቲያናት ያለውን ስለ ትንቢትና የነቢይነት ቢሮ ተግዳሮትና መፍቴሔዎች በማንሳት ተነጋገሩ። እኛስ ከምን እንጠበቅ? ሚዛን የጠበቀ ውይይት እንወያያለን።

***መ ደ ም ደ ሚ ያ***

እንግዲህ የነቢይነት አገልግሎት በብሉይ ኪዳን ሆነ በአዲስ ኪዳን የነበረ አገልግሎት እንደ ሆነ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነት ላይ መግባባት ላይ እንደ ደረሰን እርግጠኞች። የነቢይነትን አገልግሎት እንደሚገባ በመረዳት በዚህ ዘመን፣ በወንጌላዊያን አብያተ ክርስቲያናት እንዲሁም በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያናችን እንዲገለጡ መጸለይ ያስፈልጋል። በተለያየ መንገድ ማለትም በአካል እና በሚዲያ አገልግሎታቸውን እየተጠቀምን ያለንባቸው ‘ነቢያት’ የሚባሉትን ሕይወታቸውን፣ መልዕክታቸውን እና አገልግሎታቸውን እንደ እግዚአብሔር ቃል የመመርመር፣ የመፈተን እና መልካም የሆነውን የመያዝ፣ ከክፉ አሳብ እና ሥራቸው ጋር አለመተባበር ይገባናል (**ዘዳ.13:1-8፣ 1ኛተሰ.5:20-22)።**

**ጥናት ሶስት**

**ርዕስ፡- የማስተማር ወይንም የአስተማሪነት ጸጋ**

**የንባብ ክፍል፡- መነሻው የሐዋ ሥራ 13:1-3 እና ሌሎችም**

**ዓላማ፡-**

**በአስተማሪነት ጸጋ ዙሪያ የእግዚአብሔር ቃል የሚያስተምረውን እውነት ለማስጨበጥ ያለመ ይሆናል፡-**

**መግቢያ፡-**

ከዚህ ቀደም በነበረን የሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 13 ጥናት ላይ በአንጾኪያ ስለነበረችው አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ተመልክተናል። በዚህች አጥቢያ ቤተክርስቲያን በሚገኙ አማኞች መካከል መንፈስ ቅዱስ በሰጣቸው በነቢይነትና በአስተማሪነት ጸጋ የሚያገለግሉ እንደነበር ተገልጾል። በዚህም የነቢይነትና የአስተማሪነት ጸጋ ይህች አጥቢያ ቤተክርስቲያን ትታነጽ ትበረታ ነበር። በተለይም ያላመኑት በወንጌል እየተማረኩ ያመኑት ደግሞ በእምነት እንዲታነጹ እግዚአብሔር ነቢያትንና አስተማሪዎችን ተጠቅሞባቸዋል። በተጨማሪም የነቢይነትና የአስተማሪነት ጸጋ ከአንጾኪያ ቤተክርስቲያን መታነጽ ባለፈም ለወንጌል ሥራ ሚሲዮናዊያንን ወዳልዳኑት ለመላክ ያበረከቱት ከፍተኛ ሚና የሚዘነጋ አይደለም። ይሁን እንጂ በዚህ ባለንበት ዘመን በምትገኝ ቤተክርስቲያን እነዚህን የጸጋ ስጦታዎች ተገቢውን ትኩረት እንዳልተሰጣቸው መረዳት የሚያዳግት አይሆንም። በተለይም የአተማሪነት ስጦታ በተለያዩ ምክንያቶች በአብያተ ክርስቲያን ችላ ሲባል ይታያል። ስለዚህ በዛሬ ጥናታችን ትኩረታችን የሚሆነው በብሉይና በአዲስ ኪዳን በአስተማሪነት ወይንም በመምህርነት የጸጋ ስጦታ ዙሪያ የእግዚአስብሔር ቃል በሚያስተምረው ላይ ይሆናል።

የንባብ ክፍሎች አጭር ማብራሪያ፡-

I. **አስተማሪ (መምህር) የቃሉ ጥሬ ቃል ፍቺ፡-**

አስተማሪ ማለት ትምህርትን ወይም አስተምህሮን፣ እውቀትን፣ ጥበብን፣ ለማሳወቅ፣ ለመግለጥ፣ ለማስተላለፍ፣ ለማስረዳት፣ ለማሰልጠን፣ ለማስተማር፣ ለመምከር፣ ለመገሰጽና፣ ለማበረታታት ባለሙያ ወይንም የተካነ ወይም የተቀባ ነው፡፡

II. **አስተማሪነት በመወለድ የሚገኝ ችሎታ ወይንስ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ነው?**

እግዚአብሔን ለእያንዳዱ ሰው በሚወለድበት ጊዜ የተፈጥሮ ስጦታዎችንና ችሎታዎችን ሰጥቶአል። አንድ ሰው በክርስቶስ ኢየሱስ አምኖ አዲስ ፍጥረት ወይንም ዳግመኛ ሲወለድ መንፈስ ቅዱስ የሚሰጠው የጸጋ ስጦታ ይቀበላል። ወይንም መንፈስ ቅዱስ ሰው በተፈጥሮ ያገኘውን ችሎታ ወይንም ስጦታ አሳድጎ ከእግዚአብሔር ፈቃድ አኳያ ሊጠቀምባቸው ይችላል። እንደዚሁም የዳነው ሰው በትምህርትና በስልጠና ያካበተውንም ችሎታ መንፈስ ቅዱስ ለክብሩ ከእግዚአብሔር ፈቃድ አኳያ ሊጠቀምበት ይችላል። ለዚህ ምሳሌ መጥቀስ ቢያስፈልግ በሐዋ. ሥራ 18፡24-26 “ በወገኑም የእስክንድርያ ሰው የሆነ ነገር አዋቂ የነበረ አጵሎስ የሚሉት አንድ አይሁዳዊ ሰው ወደ ኤፌሶን ወረደ፤ እርሱም በመጻሕፍት እውቀት የበረታ ነበር። እርሱ የጌታን መንገድ የተማረ ነበረ፥” ይላል።ስናጠቃልለው፤ እስከ አሁን ባነሳናቸውና ባልተማሩት የሐዋርያቱ ህይወት ከተገለጠው እውነት በመነሳት፤ በመጽሐፍ ቅዱስ የአስተማሪነት ጸጋ ከተፈጥሮዊ ችሎታ በላይ የሆነ መንፈስ ቅዱስ የሚሰጠው ስጦታ እንደሆነ ያስረዳል።

- ማስተማር በብሉይ ኪዳን ዋና ነገር ነበር

- **በብሉይ ኪዳን እስራኤላዊያን ልጆቻቸውን እንዲያስተምሩ ታዘዋል (ዘዳ 11:19፣ 6:1)። እንዲሁም ደግሞ ዘዳ 19:31 ላይ ሕዝቡንም እንዲያስተምሯቸው ያዛል።**
- **በዕዝራ 7:10 ላይ እንደሚከተለው ይላል "ዕዝራ መላ ሕይወቱን የእግዚአብሔርን ሕግ በማጥናትና በተግባር በመተርጐም፥ እንዲሁም የእግዚአብሔርን ትእዛዞች፥ ሕጎችና ሥርዓቶች ለመላው የእስራኤል ሕዝብ በማስተማር ያውለው ነበር።" በዕዝራ 7:25 ደግሞ ዕዝራም እንዲያስተምር ታዟል። በነህምያ 8:8 ታሪክ መሠረት ነህምያ ሕዝቡን አስተባብሮ የፈረሰውን የኢየሩሳሌም ቅጥር ለማደስ ሲሰራ፤ በሌላ ጎን ዕዝራ እግዚአብሔርን ማወቅ እየገለጠ በማስተማር በህዝቡ መንፈሳዊ ህይወት ተሃድሶ ዙሪያ ይተጋ እንደነበር እንመለከታለን።**

- **አስተማሪነት የእግዚአብሄር አብ ፣ የወልድና ፣የመንፈስ ቅዱስ (ስላሴ) የሦስቱም የጋራ ባህሪ እንደሆነ ከእግዚአብሔር ቃል እንረዳለን። የእግዚአብሔርን አስተማሪነት ከዘፍጥረት እስከ ራዕይ ያለውን ሁሉ ለመመልከት ሁኔታው የማይፈቅድልን ስለሆነ የሚቀጥሉትን ጥቂት ጥቅሶችን ብቻ እናነሳለን።በኢሳ 48:17 እንዲህ ይላል "ታዳጊህ፥ የእስራኤል ቅዱስ፥ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ እኔ የሚረባህን ነገር የማስተምርህ በምትሄድባትም መንገድ የምመራህ አምላክህ እግዚአብሔር ነኝ"። ይህ ከላይ የተጠቀሰው ጥቅስ የእስራኤል ቅዱስ እግዚአብሔር ለህዝቡ የሚረባውን ነገር የሚያስተምር በሚሄድበትም መንገድ የሚመራው እንደሆነ ይገልጻል። በተጨማሪም መዝ 25፥4-13 መዝሙረኛው እግዚአብሔር "አስተምርሃለሁ በምትሄድበትም መንገድ እመራሃለሁ፤ ዓይኖቼን በአንተ ላይ አጠናለሁ" ስለሚል እግዚአብሔር በህይወቱ ጎዳና እንዲመራውና እንዲያስተምረው ሲማጸን እንመለከታለን።**
- **ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አስተማሪ ነበር (በማቴ. 5፥ 1- ሉቃ 24፥ 25-32)**

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም በወንጌላት ውስጥ ተደጋግሞ "መምህር" ተብሎ ተጠቅሷል። እንዲሁም በማቴ 5:1 "ሕዝቡንም አይቶ ወደ ተራራ ወጣ፤ በተቀመጠም ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ወደ እርሱ ቀረቡ፤ አፉንም ከፍቶ አስተማራቸው" ይላል። በማር 2፥13, 11፥ 17 ላይ በባህር አጠገብ፤ ብዙ ሕዝብ ወደ እርሱ ተሰብስበው ሲያስተምራቸው እንደነበርም እንመለከታለን። እንዲሁም ጥያቄ ተጠይቆ ማብራሪያ በሚሰጥበት ጊዜ ትምህርቱን የሚጀምረው "እንዲህ ሲባል ሰምታችኋል እኔ ግን እላችኋለሁ" በሚለው አባባሉ ነበር። ለደቀ መዛሙርትም ሆነ ለሚሰሙት ከእኔ ተማሩ ይላቸው እንደ ነበር እናያለን። ጌታም ማስተማሩንም በጨረሰ ጊዜ ትምህርቱን የሰሙት ሕዝብ ሁሉ በትምህርቱ ይገረሙ እንደነበር በተደጋጋሚ ስፍራ። ደቀ መዛሙርትም ይሁን ሌሎች "መምህር" "ረቡኒ" ይሉት ነበር (ዮሐ 13:13፣ 11:28፣ 20:16)። በአጭሩ ክርስቶስ በአገልግሎቱ በብዙ ያስተምር ነበር።

- ***መንፈስ ቅዱስ አስተማሪ ነው***

የዮሐ 14:26፣ 16:13 በዚህ ክፍል *መንፈስ ቅዱስ* አስተማሪ እንደሆነ ያሳየናል። እንዲሁም ሐዋርያው ዮሐንስ የሀሰት አስተማሪዎችን አሳሳች ትምህርት በተመለከተ በትክክል ካዳመጥነው በውስጣችን ያለው መንፈስ ቅዱስ የተሻለ አስተማሪ እንደሆነ በሚቀጥለውም ጥቅስ ያብራራል "እናንተስ ከእርሱ የተቀበላችሁት ቅባት በእናንተ ይኖራል፥ ማንም ሊያስተምራችሁ አያስፈልጋችሁም፤ ነገር ግን የእርሱ ቅባት ስለ ሁሉ እንደሚያስተምራችሁ፥ እውነተኛም እንደ ሆነ ውሸትም እንዳልሆነ፥ እናንተንም እንዳስተማራችሁ፥ በእርሱ ኑሩ (1 ዮሐ 2፥26-27)።" ይህ ማለት በማስተማሪ የተቀቡ አገልጋዮች አያስፈልጋችሁም ማለት አይደለም።

- በታላቁ ተልዕኮ ዋና መልዕክት አንዱ ማስተማር ነው

በማቴ 28፥19-20 "እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፥ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፤ እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ።" ጌታ የምድር አገልግሎቱን ጨርሶ ወደ ሰማይ ከማረጉ በፊት ለሐዋርያቱ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሊፈጽሙት ስለሚገባው የማስተማር አገልግሎት አደራ ሲሰጥቸው እንመለከታለን። በዚህም መሠረት ሐዋርያቱም መንፈስ ቅዱስን ከተቀበሉና ከተሞሉ በኃላ የእግዚአብሔርን ቃል በግልጥነት ያስተምሩ ነበር፦ "ቃሉንም የተቀበሉ ተጠመቁ፥ በዚያም ቀን ሦስት ሺህ የሚያህል ነፍስ ተጨመሩ፤በሐዋርያትም ትምህርትና በኅብረት እንጀራውንም በመቍረስ በየጸሎቱም ይተጉ ነበር" (ሐዋ ሥራ 2:42)።"ጴጥሮስና ዮሐንስም በግልጥ እንደ ተናገሩ ባዩ ጊዜ፥ መጽሐፍን የማያውቁና ያልተማሩ  ሰዎች እንደ ሆኑ አስተውለው አደነቁ፥ ከኢየሱስም ጋር እንደ ነበሩ አወቁአቸው" (ሐዋ ሥራ 4:13)። ጌታ የማስተማር ጸጋ ሰጥቷቸው ነበር።

III. የማስተማር ጸጋ በመልዕክቶች (ኤፌ 4፥11-13 ሮሜ 12፥6-9)

ሐዋርያው ጳውሎስ ከላይ በተጠቀሱ ክፍሎች ለቅዱሳን በመንፈስ ቅዱስ የተሰጣቸውን የተለያዩ የጸጋ ስጦታዎች እየዘረዘረ ሲጽፍላቸው፤ አስተማሪነትም አንዱ መንፈስ ቅዱስ የሚሰጠው የጸጋ ስጦታ እንደሆነ በግልጽ አስቀምጦታል፦ "እርሱም አንዳንዶቹ ሐዋርያት፥ ሌሎቹም ነቢያት፥ ሌሎቹም ወንጌልን ሰባኪዎች፥ ሌሎቹም እረኞችና አስተማሪዎች እንዲሆኑ ሰጠ፤ ሁላችን የእግዚአብሔርን ልጅ በማመንና በማወቅ ወደሚገኝ አንድነት፥ ሙሉ ሰውም ወደ መሆን፥ የክርስቶስም ሙላቱ ወደሚሆን ወደ ሙላቱ ልክ እስክንደርስ ድረስ፥ ቅዱሳን አገልግሎትን ለመሥራትና ለክርስቶስ አካል ሕንጻ ፍጹማን ይሆኑ ዘንድ።" እንዲሁም በሮሜ 12:6-9 ባለው ክፍል እንደሚከተለው ይላል " እንደ ተሰጠንም ጸጋ ልዩ ልዩ ስጦታ አለን፤ ትንቢት ቢሆን እንደ እምነታችን መጠን ትንቢት እንናገር፤ አገልግሎት ቢሆን በአገልግሎታችን እንትጋ፤ የሚያስተምርም ቢሆን በማስተማሩ ይትጋ፤"

በ2 ጢሞ 3፥14-17 ጢሞቴዎስን የሚያስተምሩ አገልጋዮች እንደነበሩና ማስተማርም በሰው ሕይወት ለውጥ የሚያመጣ ጸጋ እንደሆነ ያስረዳል፦ "አንተ ግን በተማርህበትና በተረዳህበት ነገር ጸንተህ ኑር፥ ከማን እንደ ተማርኸው ታውቃለህና፤ ከሕጻንነትህም ጀምረህ ክርስቶስ ኢየሱስን በማመን፤ መዳን የሚገኝበትን ጥበብ ሊሰጡህ የሚችሉትን ቅዱሳን መጻሕፍትን አውቀሃል። የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ፤ የእግዚአብሔር መንፍስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሣጽ ልብንም ለማቅናት በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል።

IV. በመጨረሻው ዘመን ቤተ ክርስቲያን የሚጋረጥባት አደጋና መፍትሄው፦

1 ጢሞ. 4፥1-6 በእነዚህ ቁጥሮች በመጨረሻ ዘመን ስለሚመጣው ክፉ ትምህርት ይናገርና ያንንም ትምርህት ለመቋቋም በሚቀጥሉት ጥቅሶች ቤተ ክርስቲያንን ለመጠበቅ ማስተማር እጅግ አስፈላጊ እንደሆነ አስረዳል። ቀጥለው ያሉትን ክፍሎች አንበቡ፦ በቁ.11-12 "ይህን እዘዝና አስተምር። በቃልና በኑሮ በፍቅርም በእምነትም በንጽሕናም ለሚያምኑቱ ምሳሌ ሁን እንጂ፥ ማንም ታናሽነትህን አይናቀው።"

1 ጢሞ. 6፥ 3-6 "እነዚህን አስተምርና ምከር። ማንም ልዩ ትምህርት የሚያስተምር ከጌታችንም ከኢየሱስ ክርስቶስ በሆነው ጤናማ ቃልና እግዚአብሔርን ለመምሰል በሚስማማ ትምህርት የማይጠጋ ቢሆን፥ በትዕቢት ተነፍቶአል አንዳችም አያውቅም፥

2 ጢሞ. 4፥1-4 “በእግዚአብሔር ፊት በሕያዋንና በሙታንም ሊፈርድ ባለው በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ፊት፥ በመገለጡና በመንግሥቱም እመክርሃለሁ፤ ቃሉን ስበክ፥በጊዜውም አለጊዜውም ጽና፥ ፈጽመህ እየታገስህና እያስተማርህ፥ ዝለፍና ገስጽ ምከርም። ሕይወት የሚገኝበትን ትምህርት የማይታገሡበት ዘመን ይመጣልና፤ ነገር ግን ጆሮቻውን የሚያሳክክ ስለ ሆነ፥ እንደ ገዛ ምኞታቸው ለራሳቸው አስተማሪዎችን ያከማቻሉ። እውነትንም ከመስማት ጆሮቻውን የመልሳሉ፥ ወደ ተረትም ፈቀቅ ይላሉ።”

V. በዛሬ ዘመንስ ቤተ ክርስቲያን የአስተማሪነት ጸጋ ምን ይመስላል?

በሐዋ. 2፥ 41-42 እና በሐዋ. 13፥1-3 እንደተተቀሰችው እንደ ጥንቱ ሐዋርያት ዘመን ቤተ ክርስቲያን የዛሬውም ቤተ ክርስቲያን ለአስተማሪነት ጸጋ ተግታ መጸለይና በሥራም መተግበር አለባት።ችላ ማለትም የለባትም። ይህ ጸጋ አማኞችን ከተለያዩ የሐሰት ትምህርቶች ራሳቸውን እንዲጠብቁ ይረዳል። እንዲሁም ክርስቶስን የሚያስከብር የደቀ መዝሙር ሕይወት እንዲኖሩ ይረዳቸዋል። በነገራችን ላይ ልክ እንደ ትንቢትና የነቢይነት ቢሮ የማስተማር ጸጋና መደበኛ የአስተማሪነት አገልግሎት ይለያያል። የአስተማሪነት ቢሮ በኤፌ 4:11 የተጠቀሰ ሲሆን ሌሎቹ በተለያዩ ጊዜያት አልፎ አልፎ የሚያስተምሩ ይኖራሉ። ማንኛውም ጸጋ ደረጃና እድገት የለውም።

*የመወያያ ጥያቄዎች:-*

1.ከላይ በተሰጠው ማብራሪያ መሰረት ስለአስተማሪነት ወይንም መምህርነት የተሰጠውን ትርጉምና ማብራሪያ ተወያዩ?

2.በኢሳ 48፥17፣ከመዝ 25፥4-13 በማንበብ ስለ ማስተማር ምን ተረዳችሁ። አካፍሉ።

3.ማቴ 5:1-2፣ ዮሐ 13:13፣ 11:28፣ 20:16 ስናነብ ጌታ ኢየሱስ በምድር ላይ በምን አገልግሎት ያገለግል እንደነበረ ተወያዩ።

4.ዕዝ 7፥10 በማንበብ ስለ ማስተማር ወይም ስለ አስተማሪነት ጸጋ አብራሩ? ዕዝራ ምን ምን እንዳደረገ ተነጋገሩ።

5.የዮሐ 14:26፣ 16:13 እና 1 ዮሐ 2፥ 26- 27 መሠረት ስለ መንፈስ ቅዱስ አስተማሪነት ምን እንደሚል ተነገሩ።

6.በማቴ. 28፥19-20 አማኞች በዚህ በታላቁ ተልዕኮ ጥቅስ የታዘዙትን ትዕዛዝ በዝርዝር ተወያዩ? ከሐዋ ሥራ 2:42 ከተጠቀሰው ጋር ምን ግንኙነት አለው?

7.በኤፌ. 4፥11-13የሐዋ. ሥራ 13፥1-5 በማንበብ እግዚአብሔር የአስተማሪነትን ጸጋ የሰጠው ለማን ነው? የተሰጠበት ዓላማውስ ምንድን ነው?

8.በ2ጢሞ. 3፥14-17 በዚህ ክፍል በማስተማር ጸጋ የሚገኘውን ፋይዳ የተዘረዘረው እንዴት ነው? ትኩረቱስ ምን ላይ ነው?

9.በ1ጢሞ. 4፥1-3 በመጨረሻው ዘመን ቤተክርስቲያን የሚጋረጠባት አደጋ ምንድን ነው? በመፍትሄነት ያቀረበውስ ትእዛዝስ በ1ጢሞ. 4፥6-13 ምንድን ነው? ተወያዩ።

10.በአሁን ዘመን ቤተ ክርስቲያን የማስተማር ጸጋ አለ ወይስ የለም?

*መ ደ ም ደ ሚ ያ:-*

ከዚህ በላይ በነበረው ጥናት እግዚአብሔር ለቤተክርስቲያን ከሰጠው ስጦታ መካከል አንዱ የአስተማሪነት ጸጋ እንደሆነ ለማየት ሞክረናል። ይህንንም የጸጋ ስጦታ ለቤተክርስቲያን የሰጠበት አላማ በማያሻማ መልኩ ለቤተክርስቲያን

መታነጽ እንደሆነ በግልጽ ተቀምጧል። ምክኒያቱም እንደ ክርስቶስ ትምህርት ሳይሆን ፤ በሌሎች ልዩ ልዩ እንግዳ የትምህርትና በሰዎች ረቂቅ ተንኮልና ማታለል ወዲህና ወዲያ እየተንሳፈፈች በመጣው ነፋስ እንዳንወሰድ ነው። በመሆኑም እምነታችን በእውቀትና በመረዳት ባለጠግነት ሁሉ እንድንደርስ፤ እንደ ክርስቶስ ትምህርት በጤናማው የእግዚአብሔር ቃል አስተምሮ በነቢያቱና በሐዋርያቱ መሰረት ላይ እንዲሆን ያደረገዋል። ስለዚህ በአስተማሪነት ጸጋ እግዚአብሔር ጸጋ የሰጣቸውንና ማስተማር የሚችሉትን ቤተክርስቲያን ለይታ ማሰርማራት እንድትችል፤ እንዲሁም አሁን በማስተማር ጸጋ እየተጉ ያሉትንም ይበልጥ ጌታ እንዲረዳ ለአገልጋዮቹና ለአገልግሎት ክፍሉ ልንጸልይላቸው ይገባል።

## ጥናት አራት

**ርዕስ፡-** የአንጾኪያ ቤ/ክንና ወደ ቆጵሮስ ደሴት የወንጌል ተልዕኮ

**የምንባብ ክፍል፡-** ሐዋ 13: 1-12

**ዓላማ፡-** የአንድ አጥቢያ ቤ/ክ ቀዳሚ ጥሪና ተልዕኮ ምን እንደሆነ ማስገንዘብ

***መግቢያ፡-***

ከዚህ በፊት በነበረን በሐዋ. ሥራ ምዕራፍ 12 ጥናት ማለትም በክፍል አንድ ጥናት ላይ ንጉስ ሄሮድስ በሐዋርያቱ ላይ መከራና ስደት አስነስቶ ሐዋርያው ያዕቆብን አሰይፎ በማስገደልና ሐዋርያው ጴጥሮስንም ወደ ወኅኒ በማስገባት በቤተክርስቲያን ላይ ብዙ ስደት አስነስቶ እንደነበር ተመልክተናል።

በዛሬው ጥናታችን ደግሞ ጌታ ኢየሱስ በሐዋ.ሥራ 1:8 ትዕዛዝ መሰረት ሐዋርያቱን ከኢየሩሳሌም ጀምሮ እስከ ዓለም ዳርቻ ድረስ ምስክሮቹ እንዲሆኑ ባዘዘው መሰረት የአንጾኪያ ቤ/ክ ሰዎችን ለሚስዮናዊነት ወይም ለዓለም አቀፍ የወንጌል መልዕክተኝነት በመንፈስ ቅዱስ እንዴት እንደለየችና እንደላከች እግዚአብሔርም ከተላኩት ጋር እንዴት እንደሰራ በመመልከት ዛሬም የአንድ አጥቢያ ቤ/ክርስቲያን ዋና ተልዕኮ እናያለን።

***ማስታወሻ፡-***

ከቤተ ክርስቲያን ታሪክ እንድምንረዳው የዚህ ጥናት ሙሉ ታሪክ ከ48-49 ዓ/ም ባለው ጊዜ የሆነውን የመጀመሪያውን የሚስዮናውያን የወንጌል ጉዞ ታሪክ ይነግረናል። መሉ ታሪኩም በሐዋ 13-14 ተጽፎ ይገኛል። ይህም በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ሐዋርያው ጳውሎስ ወደ ሮም የሄደበት የመጨረሻው ጉዞ ሲጨመር በድምሩ አራት ትልልቅ ጉዞዎችን አድርጓል። እንዲሁም በተጨማሪም ሌሎችም በአንጾኪያ ስም የሚጠሩ ከተሞች ስላሉ ይህችኛዋ አንጾኪያ የሶሪይዋ አንጾኪያ እንደሆነች ልብ ማለት አለብን (ይህ አንጾኪያ አሁን በደቡባዊ ቱርክ የሚገኝ ከተማ ነው)። ለምሳሌ የጵስዲያው አንጾኪያ ሌላኛው አንጾኪያ ነው (ሐዋ. ሥራ 13:14።

### የክፍሉ አጭር ትንታኔ

### ሐዋ. ሥራ 13:1-3 ወንጌል በሶርያው አንጾኪያ

ሐዋ. ሥራ 11:19-30 እንደሚነግረን በሶርያ ትገኝ የነበረችው የአንጾኪያ ቤ/ክ የመጀመሪያዋ ግልጽ የአህዛብ ቤተ ክርስቲያን በመሆን ትታወቃለች። ለዚህች ቤ/ክ እድገት የበርናባስና የሳዖል አገልግሎት ታላቅ ነበር። አንድ ዓመት ሙሉ እንዳደራጁና እንዳስተማሩም ክፍሉ ይነግረናል። ይህች ከተማ አማኞች ለመጀመሪያ ጊዜ "ክርስቲያን" የተባሉባት ቦታ ናት (ሐዋ. ሥራ 11:26)። ይህች አንጾኪያ በአሁኑ ጊዜ በደቡባዊ ቱርክ ትገኛለች። የአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን ሚስዮናዊትና እርዳታም የምትለግስ ቤ/ክ ስትሆን ልዩ ልዩ ጸጋ ያላቸው አገልጋዮችም እንደነበሩባት ከክፍሉ እንረዳለን (ሐዋ. ሥራ 13:1-3)።

*ሐዋ. ሥራ 13፡1-3 የአንጾኪያ ቤ/ክ መሪዎች መንፈሳዊነት*

ከላይ የተጠቀሱትን ቁጥሮች ስናነብ የአንጾኪያ ቤ/ክ የመሪዎች ስብጥር ነቢያትንና መምህራንን ያካተተ እንደ ነበር ነው፡፡ ለእግዚአብሔር መንግስት ሥራ ተጠርቶ የወጣ አንድ አምላክ ፤ አንድ መንፈስና አንድ ጌታ ያለው ሕዝብ ወይም ቤተ

ክርስቲያን ነበር፡፡ የቤተ ክርስቲያንቷ መሪዎች የጸሎት ህይወትና የታላቁ ተልዕኮ ልብ ያላቸው መሪዎች ናቸው። ስለዚህም ይጾሙ፣ይጸልዩና የመንፈስ ቅዱስን ድምጽ ይሰሙ ነበር። የተሰጡ የመሪዎች ሕይወት ይህን ይመስላል።

**ሐዋ. *ሥራ* 13:4-6 ወንጌል በቆጵሮስና አካባቢዋ፡-**

ቆጵሮስ በ**ሜዴቴራኒያን** ባህር የምትገኝ ደሴት ስትሆን ለበርናባስ የትውልድ ሀገሩ እንደሆነችም ትታወቃለች (ሐዋ. *ሥራ* 4:36)። ይህች ሀገር **በርናባስና ሳውል ከአንጾኪያ ለመጀመሪያ ጊዜ ለሚስዮናዊነት (ለወንጌል ተልዕኮ) የተላኩባት ደሴት ናት። በዚህ ጉዞ ዮሐንስ የተባለው ማርቆስ (የማርቆስ ወንጌል ጸሐፊ) አብሮአቸው እንደነበረ ይታወቃል (ሐዋ. *ሥራ* 12:25)። በሐዋ.*ሥራ* 13፡4-6 ላይ የተጠቀሱ ቦታዎች ማለትም** ሴሌውቅያ፣ስልማናና ጳፉ በቆጵሮስ ደሴት የሚገኙ ቦታዎች ናቸው (በአዲሱ መደበኛ ትርጉም የማጥኛ መጽሐፍ ቅዱስ ካርታ መመልከት ትችላላችሁ) ። **ከእስጢፋኖስ ሞት በኋላ በተነሳው ስደት ምክንያት ሐዋርያቱና ደቀ መዛሙርቱ ወንጌልን በብዙ ቦታዎች እየሰበኩ አንጾኪያ** ከተማ ደርሰዋል። የአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን ደግሞ በላከቻቸው ሚስዮናውያን ባደረጉት የወንጌል ጉዞዎች አማካይነት ብዙ አብያተ ክርስቲያናት በቆጵሮስና በአከባቢው ሊተከሉ በቅተዋል።

**ሐዋ 13:6-12 የወንጌል ድል በሰይጣን ተንኮል ላይ**

**በቆጵሮስ ሀገር የወንጌል ጠላት የሆነው ሰይጣን** ጠንቋዩን ኤልማስን በመጠቀም የሚስዮናዊያንን አገልግሎት ለማደናቀፍ ሲሞክር እናያለን።ይህ ደግሞ ምንም እንኳን ከሰማይ ተልዕኮ ቢኖረንም ሰይጣን ተልዕኮአችንን ለማሰናከል ሰዎች ወደ ድነት እንዳይመጡ የጌታን መንገድ የሚያጣምም መሆኑን ያሳየናል። በተጨማሪም ከላይ በሐዋ.*ሥራ* 13:10 ላይ ሐዋርያው ጳውሎስ ስለ ሠይጣን ባህርይ ወይም ማንነት አብራርቷል። ሐዋርያው ጳውሎስም (13፡11-12) የሰይጣንን ተንኮሉንና ክፋቱን በመረዳት የጌታን ቁጣ አውርዶበታል። ከላይ እንደተጠቀሰው የቆጵሮስ የወንጌል ተልዕኮ ከሚስዮናዊያኑ የወንጌል አራት ጉዞዎች የመጀመሪያው እንደሆነ ብዙዎች ያምናሉ። በዚህ ከተማ ታዋቂው የሀገሩ ገዥ ጌታን እንዳመነም ክፍሉ ይነግረናል።

**የመወያያ ጥያቄዎች**

1. በሶሪያ ስለምትገኘው አንጾኪያ በባለፉት ጥናቶች በተለያዩ መልኩ ያየን ቢሆንም የሐዋ. *ሥራ* 11:19-30ን በማንበብ ስለ አንጾኪያ ቤ/ክን የተረዳችሁትን ተወያዩ።
2. ሐዋ 13:1 በአንጾኪያ ቤ/ክ አገልግሎትና አመራር ውስጥ የነበረው ስብጥር ምን ይመስል ነበር? ከዚህ ምን እንማራለን?
3. በሐዋ.*ሥራ* 13:1-2 መሰረት መንፈስ ቅዱስ ወደ መሪዎቹ ያመጣው መልዕክትና የወሰዱትስ እርምጃ ምን ነበር? ለዚህ ድምጽ መምጣት የመሪዎቹ ድርሻስ ምን ነበር?
4. ሐዋ. *ሥራ* 13:1-3 በማንበብ የአንጾኪያ ቤ/ክ ጸጋቸውንና ማንነታቸውንም አብራሩ።

5. በዚህ ክፍል መሰረት የአንጾኪያ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የተወጠችው ኃላፊነት ምንድር ነው? ይህስ የመጀመሪያው የወንጌል ጉዞ የሆነው መቼ ነበር?
6. በሐዋ. ሥራ 13:4 መሠረት በመንፈስ ቅዱስ መሪነት ከለዩዋቸውና ከጸለዩላቸው በኋላ፡ በርናባስና ጳውሎስ ለወንጌል ሥራ የተላኩት የት ነበር? ስለ ቆጵሮስ የምታውቀትን ነገር ተነጋገሩ።
7. ከቁጥ. 4-9 መሰረት የሚስዮናዊያኑ ቡድን በቆጵሮስ ደሴት ከተሞች የወንጌል አገልግሎት የገጠማቸው ተግዳሮትና ውጤት ምን ነበር? እንዴትስ ተወጡት?
8. ከሐዋ.13፡10 ምን እንማራለን?
9. ከዛሬ ጥናት ስለ አጥቢያ ቤተክርስቲያን የወንጌል ተልዕኮ ምን እንማራለን? እኛስ በዚህ ተልዕኮ ምን ኃላፊነት አለብን?
10. ለማስታወስ ያህል፡- ከዚህ በፊት እንዳሳሰብነው እያንዳንዱ ቡድን በግልም ይሁን በጋራ ከመሪዎቻችን ጋር በመመካከር የተለያዩ እቅዶችን በማውጣት በዚህ የሐዋርያት ሥራ ጥናት ጊዜ ሁሉ ይህንን ታላቁን ተልዕኮ ልንወጣ ይገባል።

## **ማ ጠ ቃ ለ ያ**

በዚህ ጥናት ሰዎችን ከጨለማ ዓለም ለማውጣትና የታላቁን ተልዕኮ ትዕዛዝ ለመፈጸም የቤ/ክ ድርሻ ትልቅ እንደሆነ በሐዋ.ሥራ 13:1-3 ባለው ክፍል ከአንጾኪያ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አይተናል። የወንጌል ስራ በዚህ መልኩ እንደ ዱላ ቅብብል ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲተላለፍ ዛሬ እኛ ጋ ደርሷል። በመሆኑም የዚህ የዘመናችን የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንም ይህንን አገልጋዮችን የመለየትና እግዚአብሔር ለጠራቸው ስራ የማሰማራት ድርሻዋን እንድትፈጽም ይገባል። እንዲሁም አማኞች በግልም ይሁን በቡድን ወንጌልን ላልዳኑ ሰዎች የመናገር የፍቅር ኃላፊነት አለብን።

## ጥናት አምስት

**ርዕስ፡-** *የድነት ታሪክ ሁሉን አቀፍ ነው*

**የምንባብ ክፍል፡-** *ሐዋ. ሥራ* 13:13-52

***ዓላማ፡-*** ከሶሪያ አንጾኪያ የተላኩት **የመጀመሪያው የሚስዮናዊያን ጉዞ ከቆጵሮስ በመቀጠል** ወንጌል እንዴት ወደ ደቡባዊ እስያ እንደደረሰና ወንጌልም የተለያዩ ተግዳሮቶችን እያለፈ እንዴት መስፋፋቱን እንደቀጠለ ማየት፡-

***መግቢያ፡-***

ባለፈው ጥናት የአንጾኪያ አጥቢያ ቤ/ክ ለወንጌል ተልዕኮ ስለነበራት ቆራጥ ዓላማና ተግባር አይተናል። በተጨማሪም መንፈስ ቅዱስ ሰዎችን ለወንጌል ተልዕኮ እንዴት እንደሚለይና አብሮአቸው እንደሚሰራ ከበርናባስና ከሳውል/ጳውሎስ/ ለአገልግሎት መለየት ጋር አያይዘን ተመልክተን ነበር ። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ ከአንጾኪያ የተነሱት በርናባስና ጳውሎስ በጵንፍልያ፣በጴርጌንና በጵስዲያ አውራጃዎችና ከተሞች እግዚአብሔር በገባው ቃል ኪዳን መሰረት አዳኝ የሆነውን ኢየሱስን ክርስቶስን በምኩራቦች እንዴት እንደገለጡ **እናያለን፡፡ምኩራብ ማለት የአይሁዶች የአምልኮ፣ የትምህርትና የማህበራዊ ኑሮ *ሥርዓቶችን* መማሪያና መተግበሪያም ቦታ ነው። አንድ ምኩራብ ለመጀመር ቢያንስ 10 ወንዶች ሊገኙ ይገባል።**

**የክፍሉ አጭር ትንታኔ**

**ሐዋ 13:13-15 የወንጌል መልዕክተኞች በምኩራብ በጵስዲያ አንጾኪያ ክርስቶስን ሰበኩ**

ከሶሪያ አንጾኪያ የተላኩ የወንጌል መልዕክተኞች ከቆጵሮስ በጵስዲያ በምትገኘው አንጾኪያ ሲደርሱ በመጀመሪያ ያደረጉት ወደ ምኩራብ ሄደው ስለ ድነት ቃል ኪዳን ታሪክ መናገር ነበር። በመግቢያ እንደተብራራው ምኩራብ የሚባለው አይሁዶች ለማህበራዊ፣ለትምህርትና ለሃይማኖታዊ ጉዳዮች የሚሰበሰቡበት ቦታ ነው። ስለሆነም ስለ ወንጌል በምኩራብ ለመነጋገር ከባድ አይሆንም። ምክንያቱም የወንጌል መልዕክተኞቹ አይሁዳዊያንና የአይሁድን ኃይማኖት ታሪክ የሚያውቁ በመሆናቸው ነው። በተለይም ብሉይ ኪዳንን የሚያውቁ ስለሆኑ ለመልእክቱ ሙሉ በሙሉ እንግዶች አይሆኑም። የሐዋ. ሥራ 13:15 ይህን ያስረግጣል። ለምሳሌ በኦርቶዶክስና በካቶሊክ የሃይማኖት ድርጅት ልምድ ላላቸው ሰዎች ስለ መጽሐፍ ቅዱስ መናገር እንግዳ አይሆንም።

**ሐዋ 13:16 – 41 *የድነት ታሪክ***

ይህ ክፍል በትረካው የሚነግረን እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ሁሉ ስላዘጋጀው በረከት ነው። ድነት የሚገኘው በክርስቶስ ብቻ እንደሆነ በግልጽ ያስረዳል። ሐዋርያው ጳውሎስ በዚህ ክፍል አስደናቂ የሆነውን የድነት ቃል ኪዳን ታሪክ ለአይሁዶች በሚገርም ሁኔታ ይተርክላቸዋል። አንድ አማኝ ድነትን መተረክ መቻል አለበት።

**ሐዋ 13፡42-52 *ተቀባዮችና ተቃዋሚዎች፡-***

በዚህ ክፍል እንደምንረዳው በዚህ ከተማ ወንጌሉን የሰሙት አይሁዶችና አይሁድ ያልሆኑ ብዙዎችም ይህንን የመዳንን ኃይል ሲቀበሉ ሌሎች ደግሞ ከመቀበል ይልቅ በቅናት ተነሳስተው ሲያሳድዷቸው እናያለን። ይህ ደግሞ የሚያሳየን ወንጌል ስንሰብክ የወንጌልን ኃይል የሚያምኑ ሊኖሩ እንደሚችሉና በተመሳሳይ ጊዜም ተቃዋሚዎችና አሳዳጆችም ሊነሱብን እንደሚችሉ ነው።

**የመወያያ ጥያቄዎች**

1. ሐዋ. ሥራ 13:13-15 በርናባስና ጳውሎስ ከቆጵሮስ ደሴት ተነስተው በጲስድያ ወዳለችው ሌላዋ አንጾኪያ ሄደው ምን አደረጉ? የተከፈተላቸውስ አገልግሎት ምን ነበር?
2. ምኩራብ ምንድ ነው? የወንጌል መልዕክተኞቹ ወደ አንድ ሥፍራ ስደርሱ አስቀድመው ወደ ምኩራብ ይሄዱ የነበሩት ለምንድ ነው? አብራሩ።
3. ከቁ.16-20 መሠረት ሐዋርያው የተናገራቸው ነገሮች ምን ለማስተላለፍ ፈልጎ እንደሆነ ተወያዩ? ይብራራ
4. በሐዋ. ሥራ 13:24-25 መሠረት ኢየሱስ ከመምጣቱ በፊት መጥምቁ ዮሐንስ ስለ ኢየሱስ የሰጠው ምስክርነት ምን ነበር? የንስሀ ጥሪውን ለተቀበሉ ሰዎች ይህ መልዕክት ምን ጠቀሜታ ያለው ይመስልሀል/ሻል?
5. ከቁ. 26-27 በማንበብ የተረዳችሁትን አካፍሉ። በዚህ ክፍል የአይሁዶች ችግራቸው ምን ነበር?
6. ሐዋ. ሥራ 13:25-31 ባለው ክፍል በጵስዲያ በምትገኘው አንጾኪያ ከሐዋርያው ስብከት ምን እንደተረዳችሁ አካፍሉ።
7. ሐዋ. ሥራ 13:32-41 ስናነብ ከሐዋርያው የድነት ትረካ ውስጥ ስለ "ክርስቶስ" የተረዳችሁትን አካፍሉ።
8. ባጠቃላይ ከዚህ የንባብ ክፍል ያስተዋላችኋቸውን ሌሎች ነግሮች ካሉ በአጭሩ አካፍሉ።
9. ለሚቀጥለው ሳምንት ይህንን አስደናቂ ወንጌል በተለያዩ መንገዶች በመመስከር ያጋጠመንን ነገሮች ይዘን በመምጣት በምስክርነት ጥናታችንን እንጀምራለን።

**ማጠቃለያ**

እግዚአብሔር አብ ከዘመናት በፊት በነቢያት የተናገረውና በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል የፈጸመው ታላቅ የድነት ስራ ከሐዋርያት ጊዜ ጀምሮ የብዙዎችን ልብ በፍቅር ማርኳል። በዚህ ጥናት እንደተማርነው ባለንበት ከተማና መንደር ሁሉ ተግዳሮቶችን እየተቋቋምን ቃሉን በመውደድ ፣ በመታዘዝ እና በመመስከር ብንኖር፤ ይህ የእውነት ቃል የብዙዎችን ልብ የሚማርከ መሆኑን ነው፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትናም ዛሬም እስከ ለዘለ ዓለምም ጌታ ነው።

## ጥናት ስድስት

**ርዕስ፡-** ወንጌል ደርቤንና ልስጥራን በተባሉት የኢቆንዮንና ሊቃኦንያ ከተሞች

**የምንባብ ክፍል፡-** ሐዋ 14:1-20

**ዓላማ**፡- ወንጌል ብዙ ተቃውሞ ቢኖርበትም ቃሉ በተግዳሮት ውስጥ ተሰብኮ ፍሬያማ እንደሚሆን ማሳየት፡፡

**መግቢያ፡-**

ሚስዮናዊያኑ ወይም የወንጌል መልዕክተኞቹ በመጀመሪያው የወንጌል ጉዞ በቆጵሮስ ከተሞች፣በጴርጌና፣በጵስዲያው አንጾኪያ ብዙ ፍሬ እንዳገኙ አይተናል። በዚህ ጥናት ደግሞ በኢቆንዮንና በሊቃኦንያ ከተሞች (ደርቤንና ልስጥራን) ወንጌል እንዴት እንደተስፋፋ እናያለን።

**የክፍሉ አጭር ትንታኔ**

**ሐዋ 14:1-7** ወንጌል በኢቆንዮን ከተማ

እነዚህ ቁጥሮች በኢቆንዮን ከተማ ሁለት ነገሮች እንደተከናወኑ ያመላክቱናል። ይኸውም በወንጌል መልዕክተኞቹ ስብከት ብዙዎች አይሁዶችና ግሪኮች ሲድኑ ሌሎች ደግሞ በተቃዋሚነት ጎራ ተሰልፈዋል።እንደተለመደው በምኩራብ ስብከታቸውም ብዙዎች ወደ ክርስቶስ መጥተዋል።

**ሐዋ 14:8-14 ምልክትና ድንቅ በሊቃኦንያ ከተማ (ልስጥራን)**

በዚህ ክፍል የተአምራትን ጥቅም፣ ተግዳሮትና ዓላማውን በግልጽ እናያለን። የተአምራት ዋናው ዓላማው በዚህ ምድር ላይ ሰዎች ለምድራዊ ነገር ከሚያገኙት ጥቅም አልፎ ለዘላለም ህይወት የማግኛ ምልክትና እድል ነው። በልስጥራን ከተማ ከመወለዱ ጀምሮ አንካሳ የነበረ ሰው ለመፈወስ እምነት እንደነበረው ክፍሉ ይነግረናል። የተአምራቱ አሉታዊ ነገር ሕዝቡ ሐዋርያቱን እንደ አማልክት መቁጠራቸው ነበር። ነገር ግን ሐዋርያቱ የገጠማቸውን ተግዳሮት አልፈው ማለትም ከተአምራት ይልቅ ተአምራት አድራጊውን ማስተዋወቅን ትኩረት ሰጥተዋል። እንዲሁም ሐዋርያቱ ተአምራቱን ለወንጌል ስብከት መነጋገሪያ ምልክት አድርገው ተጠቅመውበታል።

**ሐዋ 14:15-17 ስለ ታምራት አድራጊና ስለ ድነት ሰጪ ማንነት**

በቁ.14 መሠረት በተከሰተው ተአምራት አማካይነት ሐዋርያት በሰዎች ክብር ከሚገኘው ክብር ራሳቸውም እንዳዳኑ በግልጽ እናያለን። ሥጋዊነት ክብርን እንደሚፈልግ ሁላችንም እናውቃለን።

የስብከቱ ዋና ነገር ቁጥር 15 ላይ እንደሚከተለው ይነበባል፡- “እናንተም ደግሞ ከዚህ ከንቱ ነገር ርቃችሁ ፤ሰማይንና ምድርን፣ ባሕርንም በውስጣቸውም የሚኖሩትን ሁሉ ወደ ፈጠረ ወደ ሕያው እግዚአብሔር እንድትመለሱ ወንጌልን እንሰብክላችኋለን።” እንዲሁ በቁ.16 ላይ የለው ሀሳብ ይህ አምላክ በቸርነቱ ተፈጥሮን ለሁሉም መለገሱን መልካምነቱን ያሳያል።

**ሐዋ 14:19-20 ስለ ወንጌል በህይወታቸው የመጣ ከባድ ስደት**

አይሁዶች ከአንጾኪያና ኢቆንዮን ወደ ልስጥራን መጥተው ማሳደድ ብቻ ሳይሆን ሐዋርያው ጳውሎስን ደብድበውት ሞቷል ብለው ጎትተው ጥለውት ሲሄዱ እናያለን። እግዚአብሔር ግን ሥራውን አልጨረሰምና ሐዋርያው ተነስቶ ከበርናባስ ጋር ወደ ደርቤን ሄደ፤ የሐዋ. ሥራ 14፡20 ስናይ ሞተ ከተባለበት "ደቀ መዛሙርት ከብበውት እንዳሉ ተነሣ፤ ወደ ከተማም ገባ። በማግስቱም ከበርናባስ ጋር ወደ ደርቤን ሄዱ" ይላል። እግዚአብሔር በሚስዮናውያንም በራሳቸውም ሕይወት ተአምራትን ያደርግ ነበር።

***የመወያያ ጥያቄዎች***

1. በሐዋ ሥራ 14:1-5 መሠረት ስለ ወንጌል አሰባበክ ዘዴ፣ድፍረት፣ውጤትና ስደት የተረዳችሁትን አብራሩ።
2. የሐዋ ሥራ 14:6-7 በማንበብ የተረዳችሁትን ነገር ለቡድናችሁ አካፈሉ።
3. ከቁ.8-14 ክፍል በማንበብ፤ በልስጥራን ከተማ እግዚአብሔር አንካሳውን ለምን የፈወሰ ይመስላችኋል (ክፍሉ እንደሚገባ ይነበብ)? ለፈውሱ አንካሳው ድርሻ ያለው ይመስላችኋሃል?
4. በሐዋ.ሥራ 14፡15-18 መሰረት የሐዋርያቱ ዋና የስብከት መልዕክት ምን ነበር (ቁ.15 ትኩረት ይሰጥ)? ተወያዩ።
5. 14:19-20 በማንበብ በልስጥራን ስለ ተነሳባቸው ስደት ተወያዩ።
6. ባጠቃላይ ከዚህ የንባብ ክፍል ውስጥ በእነዚህ የመወያያ ጥያቄዎች ያልተነሱ ነገሮች ያስተዋላችሁት ነገሮች ካሉ በአጭሩ አካፍሉ።
7. በዚህ ከተማ ሚስዮናውያኑ የገጠማቸወ ፈተናዎች ዛሬም አለ ብላችሁ ታስባላችሁ? ምን? ፈተናውን እንዴት ልናልፍ እንችላለን?

***መ ደ ም ደ ሚ ያ፡-***

የድነት ቃል ኪዳን ባለቤት እግዚአብሔር በሉዓላዊነቱ ይህን የመንግስቱ ስራ በሚወደው መንገድ እያስፈጸመ ይገኛል። እኛ ወንጌል ለመመስከር ከተዘጋጀን ጌታ በማቴ 28:19-20 አብሮን ሊሰራ ቃል ስለገባ ፤በዛሬው ጥናት በልስጥራን ከተማ እንዳደረገው ተአምራት ያለ ሌላ ነገር በማድረግ ክብሩን ያሳየናል። እንዲሁም ስደት ቢኖርም ያለ ጌታ ፈቃድ አንዳች ነገር እንደማይሆን እንረዳለን።

## ጥናት ሰባት

**ርዕስ፡-በክርስቶስ** የዳኑትን ወይም የተተከሉትን አብያተ ክርስቲያናትን የመጎብኘት፣የማበረታታትና የማጠናከር ኃላፊነት

**የምንባብ ክፍል፡-** ሐዋ 14:21-28

**ዓላማ፡-** ወንጌል መስበክ ብቻ ሳይሆን የዳኑትን ሰዎች በክርስቶስ እንዲጠነክሩና ደቀ መዛሙርት እንዲሆኑ ማድረግ የአገልጋዮች ወይም የቤ/ክን ኃላፊነት መሆኑን ማስገንዘብ፡-

**መግቢያ፡-**

የዚህ ጥናት የንባብ ክፍል አጭር ቢሆንም፤ ስለ እውነተኛ ቤ/ክን ተከላ አገልግሎት በጣም መሠረታዊ መርሆችን ስለሚያሳየን በትኩረት እናየዋለን። አዳዲስ ቤ/ክናትን መመስረት ወይም ወንጌልን በልዩ ልዩ ከተሞችና አከባቢዎች መስበክ በራሱ ብቻውን በቂ ነው? በቂ እንዳልሆነና ምን እንደሚያስፈልግ በዚህ ጥናት እናያለን። ይህ ደግሞ በሚቀጥሉትም የሚስዮናዊያን (የወንጌል መልዕክተኞች) ጉዞዎችም ተደጋግሞ ይታያል።

### የክፍሉ አጭር ትንታኔ

**ሐዋ 14:21** ይህ ቁጥር ሁለት ነገሮችን ይዞ እናገኛለን። የመጀመሪያው በደርቤን ከተማ ወንጌል እንደተመሰከረና ደቀ መዛሙርትንም እንዳፈሩ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ወንጌል የተሰበከባቸውን ከተሞች መልሰው ሲጎበኙና ሲያጠናክሩ እናያለን። ይህ ደግሞ እግዚአብሔር የሰጣቸው አዲስ አሰራር ነው።

**ሐዋ. ሥራ 14:22 ክትትል፡-** ከመጀመሪያው የወንጌል ስብከት በኋላ በእምነታቸው ጸንተው እንዲኖሩ ማበረታታትና መምከር ወሳኝ ነው። በቤ/ክን ተከላ ክትትልና አገልግሎት ውስጥ የደቀ መዝሙርነት ሥልጠና ሂደት እጅግ ወሳኝ ነው። በቁ.22 "ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ለመግባት በብዙ መከራ ማለፍ አለብን" ከሚለው ቃል ልንረዳ የምንችለው በወንጌል ድነት ሂደት ውስጥ ምን ተግዳሮት ሊኖር እንደሚችል ነው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዮሐንስ ወንጌል 16:33 በዚህ ዓለም ሳሉ መከራ እንዳለባቸው ለደቀ መዛሙርቱ ነግሯቸዋል። የወንጌል እውነት ተአምራቱንም መከራውንም ያጠቃልላል።

**ሐዋ. ሥራ 14:23-25 አስተዳደርን መደራጀት፡-** በዚህ ቁጥር ሌላውን ለቤተ ክርስቲያን ዘላቂ ህልውና እድገት የሚያስፈልገውን ነገር ይነግረናል። ይህም ለቤ/ክ ዕድገት የአስተዳደር መዋቅር አስፈላጊ እንደሆነና **የወንጌል መልዕክተኞችም ለዚህ ትግበራ በአካባቢው ላሉት አብያተ ክርስቲያናት ሽማግሌዎችን ከሾሙ በኋላ በጾምና በጸሎት ለእግዚአብሔር አደራ እንደሰጡ ይነግረናል።**

**ሐዋ 14፡26-27 ኃላፊነት ለእግዚአብሔርም ለሰዎችም አለብን**

የወንጌል ቡድኑ የመጀመሪያውን የወንጌል ጉዞ ማለትም ስብከቱንና አደረጃጀቱን ከጨረሱ በኋላ ወደ ተላኩበት ወደ ሶሪያው አንጾኪያ ሄደው ለቤተ ክርስቲያን ወይም ለመሪዎች ሪፖርት እንዳደረጉና በዚያም የተወሰነ ጊዜ እንደቆዩ ያስረዳናል። እግዚአብሔር በጠራን ቦታ ሁሉ አብሮ ለሚሰሩትና ለእግዚአሔርም ተጠያቂነት አለብን። እኔን እግዚአብሔር ከተጠቀመኝ ለመሪዎች መገዛት አያስፈልግም አይባልም።

ቁ.27 ላይ ሌላ በጣም አስፈላጊ ነገር ይናገራል። ይኸውም እግዚአብሔር የአህዛብን ልብ ለወንጌል እንደከፈተላቸው ነው። በተረፈው በቁ.28 መሠረት ሚስዮናውያኑ ለአንድ ዓመት ያህል በአንጾኪያ እንደቆዩ ብዙዎች ይስማማሉ (ሐዋ 15:35) ።

### የመወያያ ጥያቄዎች

1. የሐዋ. ሥራ 14:20-21 ስናነብ እስካሁን ካየናቸው ነገሮች ለየት ያለ ነገር ምንድ ነው?

2. በዚህ ክፍል “ደቀ መዝሙር” የሚል ቃል ተደጋግሞ እናገኛለን። ደቀ መዝሙር ማለት ምን ማለት ነው? ደቀ መዝሙርነት ለክርስትና ህይወት ምን ጠቀሜታ አለው?
3. ደቀ መዝሙር ልንሆን እንዴት እንችላለን? ደቀ መዝሙር የመሆናችን መለኪያዎቹስ ምንድ ናቸው?
4. መንፈሳዊ ፍሬ ማለት ምን ማለት ነው ከደቀ መዝሙር ህይወት ጋር ምን ግንኙነት አለው?
5. የቁጥር 22 አስፈላጊነቱ ምንድ ነው? የዚህ ቁጥር መልዕክት ከማቴ 28:19-20 ጋር ምን ግንኙነት አለው?
6. በሐዋ. ሥራ 14:23 መሠረት የወንጌል መልዕክተኞቹ ባላፉት ምዕራፎች ያላደረጉትን በዚህ ክፍል አዲስ ነገር ምን እንዳደረጉ ይናገራል? ተወያዩ። ከቲቶ 1:5 ጋር ምን ግንኙነት አለው?
7. ሐዋ. ሥራ 14:26-28 ስናነብ ሚስዮናውያኑ የመጀመሪያውን የወንጌል ጉዞ ጨርሰው ወደ ሶርያው አንጾኪያ ተመልሰው ምን አደረጉ? ይህ ለዚህ ዘመን አገልጋዮችና ቤ/ክ ምን ያስተምረናል?
8. በግልም ይሁን በህብረት ስለተሰጠን ወንጌል ጥሪ ከዛሬው ጥናት ምን ተማርን? አካፍሉ። ምን እናድርግ?

**መ ደ ም ደ ሚ ያ፡-**

በማቴ 28:18-20 መሠረት የእኛ ወይም የቤ/ክ ተልዕኮ አዳዲስ አብያተ ክርስቲያናትን መትከል ብቻ ሳይሆን ያመኑትን በጌታ ማጠንከርና ማደራጀትም ጭምር ነው። ይህ ማለት ደግሞ ደቀ መዝሙር ማድረግ ማለት ነው። እንዲሁም በአገልግሎታችን ለእግዚአብሔርና ለሰዎችም (ለተጠራንበት ቤ/ክን) ተጠያቂነት ያለብን መሆኑን እንገነዘባለን።

## ጥናት ስምንት

**ርዕስ፡-**ልዩነትን መፍታት

**የንባቡ ክፍል፡-**የሐዋርያት ሥራ 15:1-41

**ዓላማ፡-**

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የአስተምህሮ ልዩነትና ልዩነቱንም የመፍታት ልዩ ልዩ አካሄድና ኃላፊነት ሊኖር እንደሚችል አውቀን፥ ልዩነቱ ወደ ብዙ ክርክርና ጥል ሳያመራ፡ በጥበብና ዓላማ መር በሆነ መልኩ መፍታት እንዳለብን ማሳየት:-

**መግቢያ፡-**

ቤተ ክርስቲያን በዘርና በባህል የተለያዩ ነገር ግን በጌታ ያላቸው እምነት አንድ ያደረጋቸው ሰዎች ስብስብ ናት። አንድ ካደረገን እምነት ሊያርቅ የሚፈልግ ሲመጣ፥ በመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ መሠረት ላይ በመቆም በአንድነት ልንቃወም ይገባል። በእምነትና በወንጌል ጥሪ አንድ መሆን ማለት፥ የአሠራር ልዩነት አይኖርም ማለት አይደለም። የአሠራር ልዩነት ሲመጣ፥ አንድ ላይ ሆኖ ከመጣላት፥ በሰላም ተለያይቶ የእግዚአብሔር መንግሥትን ሥራ በየፊናችን መሥራት ይበጃል። ይህንን በተመለከተ ወንጌልን በማሰራጨት ሂደት ውስጥ ሐዋርያት ያጋጠማቸውን የአስተምህሮም ይሁን ሌሎች ልዩነቶችን የመፍታትን መርሆች በዚህ ጥናት እናያለን።

**የክፍሉ አጭር ትንታኔ**

ሐዋ. ሥራ 15፡1-2 ከኢየሩሳሌም የመጡ አንዳንድ አይሁዳዊ አማኞች፥ በአንጾኪያ ቤተክርስቲያን ያሉትን አህዛብ አማኞች፥ ለመዳን እንደ ሙሴ ህግ መገረዝን እንዲጨምሩ አስተማሩአቸው። ይህ ትምህርት በጳውሎስና በበርናባስ ተቀባይነት ስላልነበረው ክርክርና ጠብ አስነሳ። ክርክሩ ወደ ከረረ ጥል ሲያመራ፥ በአንጾኪያ ያለችው ቤተ ክርስቲያን ጳውሎስንና በርናባስን ከሌሎች ወንድሞች ጋር ሆነው ወደ ኢየሩሳሌም እንዲሄዱና በዛ ያለችው ቤተክርስቲያንና መሪዎችን እንዲያማክሩ ተላኩ። ከዚህ ነገር እነ ሐዋርያው ጳውሎስ ለቤተ ክርስቲያንና ለመሪዎች ያላቸውን አክብሮት ያሳያል።የአንጾኪያ መሪዎችም ጥበበኞች ናቸው።

**ቁጥር 3-4** እነ ጳውሎስ በመንገዳቸው ባገኙአችው አብያተ ክርስቲያናትና በኢየሩሳሌም ባለችው ቤተ ክርስቲያን ዘንድ መልካም አቀባበል ነበራቸው። እነ ሐዋርያው ጳውሎስ ቤተ ክርስቲያንን እንዳከበሩ፥ በሄዱበት ሁሉ ቤተ ክርስቲያንም ታከብራቸው ነበር።

ሐዋ. ሥራ 15፡5-12 በአንጾኪያ የነበረው ክርክር በኢየሩሳሌምም ቀጠለ። በዚያም አንዳንድ ፈርሳዊያን አማኞች የሙሴ ሕግና መገረዝ አስፈላጊ እንደሆነ ተናገሩ። ቢሆንም ከብዙ ክርክር በኋላ፥ ሐዋርያው ጴጥሮስ እግዚአብሔር ያሳየውንና የተናገረውን ነገር የመፍትሄው መጀመሪያ አድርጎ አካፈለ። ይህንን በሐዋ 9፡32-11፡18 ያየነውን ታሪክ ጴጥሮስ ለቤተ ክርስቲያን ያስታውሳል። ሌሎች አይሁዳዊ አማኞች በነበሩበት፥ ጴጥሮስ በአይኑ ያየውን በአህዛብ መካከል እግዚአብሔር የሰራውን ሥራ ይናገራል። አህዛብ አምነው፥ እግዚአብሔር ልባቸውን እንዳነጻ፤ አንጽቶ ደግሞ መንፈስ ቅዱስን እንደ ሰጣቸው ይናገራል። ይህም የአይን ምስክርነት ሕዝቡን ሁሉ ዝም አሰኘ። የጴጥሮስንም ምስክርነት የሚደግፍ ሌላ ምስክርነት ጳውሎስና በርናባስ ተናገሩ።

ቁጥር 13-18 በጊዜው የኢየሱስ ክርስቶስ ወንድም ያዕቆብ የኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን ዋና መሪ ነበር። እርሱም የሁሉንም ቃል ከሰማ በኋላ የራሱን ምላሽና ድምዳሜ ሲሰጥ እናያለን። ሁሉን ከሰማ በኋላ ማሰሪያ የሆነለት፥ የእግዚአብሔር ቃል ነው። የጴጥሮስን ምስክርነት በእግዚአብሔር ቃል ሲፈትን፥ እንደ እግዚአብሔር ቃል ሆኖ አገኘው።

ቁጥር 19-21 ሐዋርያው ያዕቆብም የአህዛብ አማኞች በብሉይ ኪዳን ከታዘዙት ትዕዛዛት አራቱን ብቻ እንዲጠብቁ ተናገረ። ከእነዚህ ከአራቱ ሌላ በምንም ነገር እንዳያስቸግሩአቸው፥ በየቦታው ላሉ አማኞች ደብዳቤ እንዲጻፍ ያዛል። የደብዳቤው ዋና ዓላማው፥ የሙሴን ህግ የሚያስተምሩ አይሁዳዊ አማኖች የአህዛብ አማኞችን እንዳያስቸግሩ ነው።

**ቁጥር 22-30** ሐዋርያት የጻፉትን ደብዳቤት በተመረጡ ሰዎች ላኩ። እንዲሁም ጳውሎስና ሲላስን አብረው በመላክ በሐዋርያት እውቅና ያላቸው አገልጋዮች እነ ሐዋርያው ጳውሎስ እንጂ በቁጥር 24 “ያላዘዝናቸው ሰዎች” ያሉአቸው፥ እንዳልሆኑ ተናገሩ፦ “ስለዚህ ወደ እግዚአብሔር የተመለሱትን አሕዛብ እንዳናስጨንቃቸው ይህ የእኔ ብያኔ ነው። 20 ይልቁን በጣዖት ከረከሰ ነገር፣ ከዝሙት ርኩሰት፣ ታንቆ የሞተ እንስሳ ሥጋ ከመብላትና ደም ከመመገብ እንዲርቁ ልንጽፍላቸው ይገባል፤” (ሐዋ. ሥራ 15:19-20):: የአይሁና የአህዛብ አማኞች አንድ ላይ ህብረት ማድረግ እንዲችሉ አንድ አምላክ መምለክ እንዲችሉ የሚከተሉትን ነገሮች መጠበቅ እንዳለባቸው ታዘዋል። ዋና ነገሩ መዳን የሙሴ ህግ በመጠበቅ ሳይሆን በ ክርስቶስ ጸጋ ነው። የትዕዛዝቱ አጭር ማብራሪያ፦

1. <u>ለጣዖት የተሠዋ ሥጋ አለመብላት፦</u> አሕዛብ በግ ወይም በሬ ወደ ቤተ ጣዖት መውሰድ፥ ለቤተ ጣዖቱ አምላክ አሳልፎ መስጠትና ማረድ ልማዱ ነበራቸው። ከሥጋው የተወሰነው ለጣዖቱ መሥዋዕት ሆኖ ሲቃጠል፥ የቀረው ወደ ቤት ተወስዶ ይበላል ወይም ሥጋ ቤት ተወስዶ ይሸጣል። የአይሁድ ክርስቲያኖች እንዲህ ዓይነት ሥጋ መብላት በጣዖት አምልኮ ላይ እንደ መሳተፍ ስለሚቆጥሩት፥ ከገበያ ሥጋ የሚገዙ አሕዛብ ክርስቲያኖችን ለመቀበል ይቸገሩ ነበር። ስለሆነም፥ ያዕቆብ ከአይሁድ ክርስቲያኖች ጋር ለመተባበር ይችሉ ዘንድ አሕዛብ ክርስቲያኖች ይህን ሥጋ እንዳይበሉ ጠየቀ። ጳውሎስ ወደ በኋላ ይህንን ጉዳይ በተመለከተ የበለጠ ግልጽ ማብራሪያዎችን ሰጥቷል (1ኛ ቆሮ. ምዕራፍ 8፤9፤10 ሮሜ ምዕራፍ 14፣ 15)።
2. ዝሙት፦ እግዚአብሔር በየትኛውም ዘመን ከሚኖር ሕዝቡ የሚጠብቃቸው ሁሉን አቀፍ ትእዛዛት አሉ። ዝሙት የአሕዛብ ሕይወትና አምልኮ አካል ስለነበር፣ ያዕቆብ አሕዛብ የእግዚአብሔርን ሕግ በመታዘዝ ከዝሙት መራቅ እንዳለባቸው ገለጸ። ይህ ክርስቲያኖች ሁሉ ከዝሙት መራቅ አለባቸው የሚለው ጉዳይ በብሉይም ሆነ በአዲስ ኪዳን የተጠቀሰ በመሆኑ፥ በየትኛውም ዘመን ያሉ ክርስቲያኖችን የሚመለከት ትእዛዝ ነው፡፡ የሚያሳዝነው ታዲያ ዛሬ፥ ለዚህ የማይለወጥ የእግዚአብሔር ትእዛዝ የይገዙ ብዙ ክርስቲያኖች አሉ።

- ታንቆ የሞተ፦

እንስሳት በትክክል ታርዶ ደሙ መሬት ላይ ያልፈሰሰውን ሥጋ አለመብላት። ስለሆነም፥ ታንቀው የተገደሉ እንስሳት ሥጋን እንዳይበሉ ተከልክለዋል፡፡ ይህም ከአህዛብ የጣኦት አምልኮ ልምምድ ለማራቅ ነው።

- ደም አለመጠጣት፦

ደም ውስጥ ነፍስ እንዳለ ይታመናል። በእርግጥ ክርስቲያኖች ደም ያለመጠጣቱ ትእዛዝ ለአይሁዶች ብቻ ወይም ለክርስቲያኖች ሁሉ ስለ መሰጠቱ አንድ ዓይነት አሳብ የላቸውም። ስለሆነም፥ ዛሬ አንዳንድ ክርስቲያኖች ደም መብላት ብዙ

ችግር የሌለ መሆኑን ሲያስተምሩ ሌሎች ግን ይቃወማሉ። አብዛኞቹ የመፅሐፍ ቅዱስ አዋቂዎች ከሙሴ የምግብ ስርዓት ጋር ያቆራኙታል፡ (ዘሌ 17፡8-16) ማለትም በሙሴ ሕግ "ደም" የሚያመለክተው ግድያን ነው ብለውም ያምናሉ፡፡ መግደል አይፈቀድም።

የሐዋ. ሥራ 15፡31-35 ስናነብ በሐዋርያት የተላኩት አገልጋዮች የተሰጣቸውን አደራ ተወጥተዋል። ደብዳቤውን አስረከቡ። ቤተ ክርስቲያንም መሪዎች እንደ እግዚአብሔር ቃል የወሰኑትን ውሳኔ በደስታ ተቀብላለች። ስለዚህም አገልጋዮቹ ከዚህ በኋላ በነጻነት ማገልገል ቻሉ።

***የመወያያ ጥያቄዎች***

1. ሐዋ. ሥራ 15፡1-2 አንዳንድ አይሁዳውያን አማኞች እነ ጳውሎስ በነበሩበት የአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያስተማሩት ትምህርት ምን ነበር? ለምን ወደ ብዙ ጥልና ክርክር ቤተ ክርስቲያንን አስገባት?
2. ሐዋ. ሥራ 15:2-4 መሠረት ስለተፈጠረው ክርክር የአንጾኪያ ቤ/ክን እርምጃ ምንድ ነበር? እንዲሁም በሁለቱም ቤተ ክርስቲያንና አገልጋዮች መካከል ስለ ነበረውስ ግንኙነት ተወያዩ።
3. ሐዋ. ሥራ 15፡5-6 በማንበብ ለቡድናችሁ የተረዳችሁትን አስረዱ።
4. በቁጥር 7-12 ከብዙ ክርክር በኋላ ጴጥሮስ የተናገረውን ሲሰሙ "ሕዝቡም ሁሉ ዝም አሉ" (ቁጥር 12)። ሕዝቡን ዝም ያሰባለው የጴጥሮስ መልዕክት ምንድን ነበር? ከጴጥሮስስ ምላሽ ምን ልንማር እንችላለን?
5. በሐዋ.ሥራ 15፡13-18 መሠረት የያዕቆብ ምላሽ ምን ነበር? ውሳኔውንስ እንዲጻፍ የፈለገው ለምንድን ነው?
6. የሐዋ. ሥራ 15:19-21 ስናነብ ያዕቆብ ውሳኔውን መሠረት ያደረገው በምን ላይ ነው?
7. በሐዋ.ሥራ 15፡22-30 ሐዋርያት የጻፉትን ደብዳቤ በተመረጡ ሰዎች ወደ አንጾኪያ መልሰውመላካቸው ምን ያሳያል? በቁጥር 24 "ያላዘዝናቸው ሰዎች" ከሚለው ጋር በማነጻጸር ተነጋገሩ።
8. በቁጥር 31-35 መሠረት በሐዋርያት የተላኩት አገልጋዮች ሃላፊነታቸውን እንዴት ተወጡ? ከእነዚህ ቁጥሮች የተረዳችሁትን ነገር አብራሩ።
9. ከዛሬው ጥናት ስለ አስተምህሮት ልዩነትና ልዩነትን የመፍታት የአካሄድ ጥበብ ምን ተማርን?

***መ ደ ም ደ ሚ ያ***

ክርስቶስ በደሙ አንድ ያደረጋትን ቤተ ክርስቲያን፥ አስተምህሮንና አንድነቷን ለመጠበቅ የሚያስከፍለውን ዋጋ መክፈል አስፈላጊ ነው።

ጥናት ዘጠኝ

**ርዕስ፡** የሃሳብ ልዩነት መከሰት

**የንባቡ ክፍል፡-**የሐዋርያት ሥራ 15:36-41

***ዓላማ፡-***

በአገልግሎትና በአሰራር ሂደት በአገልጋዮች መካከል የሀሳብ ልዩነት ወይም አለመስማማት ሊከሰት እንደሚችል አውቀን፥ እንደ ሰበብ በመውሰድ የወንጌልን ሥራ ከማስኬድ እንዳንቆጠብና በልዩነት መስማማት እንደሚያስፈልግ ለማሳየት፡-

***መግቢያ፡-***

በዚህ ጥናት የሐዋርያው ጵውሎስና በርናባስ አዲስ ዕቅድና በመካከላቸው ስለተከሰው አለመስማማት እንመለከታለን (ሐዋ. 15:36-41)። በርግጥ በጳውሎስና በበርናባስ መካከል የተፈጠረው አለመግባባት የአስተምህሮ ሳይሆን፥ የአሰራር ልዩነት እንደነበረና የአሰራር ልዩነቱን መፍታት ስላልቻሉ፥ የወሰኑት በተለያየ ቦታ ሆነው የወንጌልን ሥራ መሥራት ነበር።

ሌላው ይህ ክፍል ሁለተኛውን የወንጌል ጉዞ ጅማሬ ይተርካል። በዚህ ሁለተኛው ጉዞ ሁለት ቡድን ሆነው በሁለት አቅጣጫዎች ሄደዋል። በርናባስና ማርቆስ ወደ ቆጵሮስ ድጋሚ ሲሄዱ ሐዋርያው ጳውሎስ ከሲሳስ ጋር “አብያተ ክርስቲያናትንም እያበረታታ በሶርያና በኪልቅያ በኩል አልፈው ሄደዋል (ሐዋ. ሥራ 15:41)። በዚህ በሁለተኛው የወንጌል ጉዞ በአንደኛው የወንጌል ጉዞ የተተከሉትን አብያተ ክርቲያናትን መጎብኘትና አዳዲስ አብያተ ክርስቲያናትን ደግሞ መትከል ዋናው ዓላማቸው ነበር።

እንዲሁም ደግሞ በመጨረሻዎቹ ዘመናት ሐዋርያው ጳውሎስና ማርቆስም ይቅር ተባብለው አብረው ይሰሩ እንደነበረም ይህ ጥናት ይዳስሳል (ቆላ 4:10)።

**የክፍሉ ጭብጥ ማብራሪያ**

ሐዋ. ሥራ 15:36-41

15:36 “36 ከጥቂት ቀኖች በኋላ ጳውሎስ በርናባስን ‘እንመለስና ከዚህ በፊት የጌታን ቃል ባበሠርንባቸው ከተሞች ሁሉ ያሉትን ወንድሞች <u>እንጐብኝ፤ እንዴት እንደ ሆኑም እንወቅ</u> አለው” በዚህ ክፍል እንደምናየው ጳውሎስ እርሱና በርናባስ የጌታን ቃል ባገለገሉባቸው ከተሞች ተመልሰው በመሄድ ወገኖችን እንዲጎበኙና እንዴት እንደሆኑም ማወቅ እንዳለባቸው አስቦ ለበርናባስ ያሰበውን ያካፍላል። ትልቅ ራዕይ አገኘ። በርናባስ ተስማምቶ ነገር ግን በጉዞአቸው ማርቆስም እንዲጨመር ቢፈልግም ጳውሎስ አልተስማማም። በዚህም ምክንያት የርስ በርስ መለያየታቸው መከፋፈትን አስከትሎ እያንዳንዳቸው የየራሳቸውን ምርጫ ማለትም በርናባስ ማርቆስን ጳውሎስ ደግሞ ሲላስን ይዘው ወደ ተለያዩ ከተሞች የክትትሉንና የማጽናናቱን ሥራ ለማከናወን እንደሄዱ እንመለከታለን። በሌላ አነጋገር ከላይ እንደተጠቀሰው በጳውሎስና በበርናባስ መካከል የተፈጠረው አለመግባብት የአስተምህሮ ሳይሆን፥ የአሰራር ልዩነት ነበር። የአሰራር ልዩነት መፍታት ስላልቻሉ፥ የወሰኑት በተለያየ ቦታ ሆነው የወንጌልን ሥራ መሥራት ነበር።

ማርቆስ ማን ነበር? ምንስ አደረገ?

1. ማርቆስ ክርስቶስ በምድር ላይ ባገለገለ ጊዜ ወጣት ልጅ ሲሆን በሐዋርያው ጴጥሮስና በበርናባስ እግር ሥር እንዳደገ ይነፈራል። ጌታችንን አይሁዶች አሳልፈው በሚሰጡበት ጊዜ በማርቆስ 14:51-52 የተጠቀሰው ራቁቱን የሸሸ ጎበዝ እንደሆነ ብዙዎች ያምናሉ።

2. ከዚህ በፊት በሐዋ.ሥራ 12:12 እንዳየነውና ቃሉም እንደሚከተለው እንደሚል የማርያም ልጅ ነበር፣ ሐዋርያው ጴጥሮስ ከተፈታ በኋላ "ብዙ ሰዎች ተሰብስበው በአንድነት ወደሚጸልዩበት፣ ማርቆስ ወደተባለው ወደ ዮሐንስ እናት ወደ ማርያም ቤት ሄደ" (ሐዋ 12:12)።
3. በሐዋ.ሥራ 13 በመጀመሪያው በሚስዮናዊያን የወንጌል ጉዞ አብሯቸው የሄደ ነገር ግን ጉዞው ሳያልቅ የተመለሰ ወጣትና ከ12ቱ ሐዋርያት አንዱ ያልሆነ ነበር።
4. የበርናባስ የቅርብ የሥጋ ዘመዱ እንደሆነና በሐዋርያው ጳውሎስ የአገልግሎቱ መጨረሻ ዓመታት ይቅርታ አድርጎለት አብረው ያገለግሉ እንደነበረ ይታወቃል "አብሮኝ የታሰረው አርስጥሮኮስና የበርናባስ የአክስቱ ልጅ ማርቆስ ሰላምታ ያቀርቡላችኋል፤ ስለ ማርቆስ መመሪያ ደርሷችኋል፤ እንግዲህ ወደ እናንተ ሲመጣ ተቀበሉት" (ቆላ 4:10)፣ "እንዲሁም አብረውኝ የሚሠሩት ማርቆስ፣ አርስጥሮኮስ፣ ዴማስና ሉቃስ ሰላምታ ያቀርቡልሃል" (ፊል ቁ.24፣ 2ጢሞ 4:11)።

*ማስተወሻ፡- እንግዲህ እዚህ ላይ ልንገነዘበው የሚገባን ነገር ቢኖር በእምነትና በወንጌል ጥሪ አንድ መሆን ማለት፥ የአሠራር ልዩነት አይኖርም ማለት አይደለም። የአሠራር ልዩነት ሲመጣ፥ ይህ ምርጫ ባያስደስትም አንድ ላይ ሆኖ ከመጣላት፥ በሰላም ተለያይቶ የእግዚአብሔር መንግሥትን ሥራ በየግል መሥራት እንዲሁም ይቅር መባባል አጅግ አስፈላጊ ነገር ነው። እንዲሁም ደግሞ ወንጌላዊ ሉቃስ ታሪክ እየነገረን እንጂ የግድ በያለንበት የአገልግሎት ቦታ ሁሉ አንስማማ ወይም እንጣላ ማለቱ አይደለም። ቃሉ አያዘንም አይጠቅምም!*

### *የመወያያ ጥያቄዎች*

1. ሐዋ. ሥራ 15፡36ን ከሐዋ. ሥራ 13:4-5፣14:1-8፣ 14:24-25 ጋር በማነጻጸር ጳውሎስና በርናባስ ከዚህ በፊት ወንጌልን የሰበኩባቸውን ቦታዎች ለህብረታችሁ አካፍሉ።
2. በቁጥ. 36 መሰረት ስለ ቤተ ክርስቲያን ተከላና አብያተ ክርስቲያናትን ስለማጽናት ምን ተረዳላችሁ?
3. በሐዋ.ሥራ 15፡37 መሰረት የጳውሎስና የበርናባስ መለያየት ምክንያት ማንና ምንስ በማድረጉ ነበር?
4. ሐዋ. ሥራ 15:38 እና በሐዋ. 13:13 መሰረት ዮሐንስ የተባለው ማርቆስን በተመለከተ ጳውሎስን ከእነርሱ ጋር እንዳይሄድ ያስከፋው ምን ነበር?
5. ቁጥር. 39-41ን በማንበብ ጳውሎስና በርናባስ ቡድናቸውን ይዘው የሄዱባቸውን ከተሞች ለቡድናችሁ አካፍሉ?
6. የጳውሎስና በርናባስ በማርቆስ ምክንያት መለያየትና መከፋፋት በየፊናቸው ወገኖችን ከመንብኘትና ከማጽናት ያልከለከላቸው ምን ይመስለዎታል?
7. ማርቆስ ማን እንደነበረ ከዚህ ጥናት ጭብጥ ማብራሪያ ክፍል በማንበብ ለቡድናችሁ አካፍሉ።
8. በመጨረሻዎቹ ዘመናት የሐዋ ጳውሎስንና የማርቆስ ግንኙነት ተነጋገሩ (እነዚህ ጥቅሶች ይነበቡ ቆላ 4:10፣ፊልሞና ቁ.24 እና 2ጢሞ 4:11)።
9. ከዛሬው ጥናት ምን ቀረልዎት?

### *መደምደምያ*

በአንድ አምላክ የዳንን እና ለአንድ ወንጌል የተጠራን አማኞች በአገልግሎታችን ወቅት ተካረን በሃሳብ ልንለያይ ብንችልም ግን እስከወዲያኛው መጣላትም ሆነ የወንጌልን ስራ ማቆም የለብንም።

## ጥናት አሥር

**ርዕስ፡-** የተመሰረቱትን አብያተ ክርስቲያናንት መጎብኘትና አዳዲሶችን ማደራጀት

ሁለተኛው የወንጌል ጉዞ

**የምንባብ ክፍል፡-** ሐዋ 16:1-40

**ዓላማ**፡-በክርስቶስ መሠረት ላይ የተተከሉትን አብያተ ክርስቲያናትን ማጠናከርና አዳዲሶችን መትከል የመጽሐፍ ቅዱስ መርሆ እንደሆነ ማስገንዘብ

**መግቢያ፡-**

ይህ ክፍል በሁለተኛው የሚሲዮናዊነት ጉዞ (ሐዋ 15፡36-18፡38) ውስጥ የሚጠቃለል ይሆናል። ይህ ጊዜ ከሶስት እስከ አራት ዓመታትን እንደፈጀም ይነገራል። ወንጌላዊ ሉቃስ በሐዋ.ሥራ 15:40ና 41 የጀመረውን በታሪኩ ጸኃፊ ትኩረት የተሰጣቸውን የሚስዮናውያኑን ሁለተኛውን የወንጌል ጉዞ ታሪክ በሐዋ.ሥራ 16 ላይ ይቀጥላል። ታሪክ ጸኃፊው ትኩረት የሰጣቸው በቆጵሮስ ደሴት በኩል ስለሄዱት ቡድን ስለ በርናባስና ማርቆስ ሳይሆን በሶርያና በኪልቅያ በኩል ስለሄዱት ስለ ሐዋርያው ጳውሎስና ስላስ ነው። በመጀመሪያው የወንጌል ሚስዮናዊነት ጉዞ የተተከሉትን የእስያና የገላትያ አብያተ ክርስቲያናትን ጉብኝት በተለይም በሶርያና በኪልቅያ እንደጀመሩ ማየት ጀምረናል።

በዚህ ጥናት ደግሞ ጉብኝቱ ወደ እስያና ወደ ገላትያ አብያተ ክርስቲያናት እንደቀጠለና እግዚአብሔርም ሚስዮናዊያኑን በመጠቀምና በመምራት የመዳን ወንጌል ከገላትያ ወደ አውሮፓ ማለትም ወደ መቄዶኒያ አውራጃ (ሐዋ. ሥራ 16:10) እንዴት እንደገባ የምናይ ይሆናል ( "እዚያ በሌሊት አንድ የመቄዶንያ ሰው ቆሞ "ወደ መቄዶንያ ተሻገርና እርዳን!" እያለ ሲለምነው ጳውሎስ በራእይ አየ። 10 ጳውሎስ ይህን ራእይ ካየ በኋላ ወዲያውኑ ወደ መቄዶንያ ለመሄድ ፈለግን፤ ይህም የሆነው ለመቄዶንያ ሰዎችም ወንጌልን እንድናስተምር ጌታ እንደ ጠራን ስለ ተረዳን ነው" (ሐዋ. ሥራ 16:9-10)።

### አጭር ማብራሪያ (ሐዋ. ሥራ 16:1-40)

ሐዋ. ሥራ 16:1-5 የደርቤንና የልስጥራን ጉብኝትና የጢሞቴዎስ መነሳት

ሐዋርያው ጳውሎስ ከቡድኑ ጋር ወደ ደርቤንና ወደ ልስጥራን (የዛሬዋ ቱርክ) ከደረሰ በኋላ ሁለት ታላላቅ ነገሮችን እንዳደረገ ታሪክ ጸኃፊው ያስረዳል። ከእነዚህም አንደኛው ጢሞቴዎስን ማስተዋወቅ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በኢየሩሳሌም የነበሩት መሪዎች ስለ እውነተኛ የድነት መንገድ የወሰኑትን ውሳኔ ማስተላለፍ ነው። እንዲሁም ደግሞ ይህ ክፍል ሐዋርያው ጳውሎስ ጢሞቴዎስን እንደገረዘ ይናገራል። ይህን ያደረገው በመገረዝ መዳን እንደሚገኝ ለማሳየት ሳይሆን መገረዝ የአይሁዶች ልማድ ስለሆነ በአካባቢው ወደ ነበሩት አይሁዶች ወንጌልን ይዞ ለመግባት የተጠቀመበት መንገድ ብቻ ነው። የገላትያ መልዕክት ለመዳን መገረዝም ይሁን አለመገረዝ ምንም ዋጋ እንደሌለው ይናገራል፡-ገላትያ 5:6 እንደሚከተለው ይላል "በክርስቶስ ኢየሱስ ከሆኑ፣ መገረዝ ወይም አለመገረዝ አይጠቅምምና፤ የሚጠቅመውስ በፍቅር የሚገለጽ እምነት ብቻ ነው"። ጢሞቴዎስ ከቁ.1-5 በተጠቀሱ ቦታዎች መልካም ዝና እንደነበረው ታሪኩ ይመግረናል (ቁ..2 "ጢሞቴዎስ በልስጥራና በኢቆንዮን ባሉት ወንድሞች ዘንድ መልካም ዝና ነበረው")። ይህ ሕይወት ለአገልግሎት እጅግ አስፈላጊ ነው።

### ሐዋ. ሥራ 16:6-15 ወንጌል በፊልጵስዩስ ከተማ

ይህ ክፍል ወንጌል ወደ መቄዶንያ ወይም ወደ አውሮፓ መግባት እንደጀመረ ይናገራል። በዚህ ክፍል ሐኪሙ ሉቃስ የሚስዮናውያንን ቡድን መንፈስ ቅዱስ ወደ ሚፈልገው አቅጣጫ ይመራቸው እንደነበርም ይተርካል (ቁ.10)። ይህ ደግሞ

እግዚአብሔር አብሮአቸው እንደነበርም ያስረዳል። ወደ አዎሮፓ መሄድ እንዳለባቸው እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ በህልም ተናገራቸው። ከዚህም የተነሳ የአከባቢውና የመቄዶንያ አውራጃ ዋና ከተማ በሆነው በፊልጵስዮስ ከተማ ወንጌል እንዴት እንደገባና በከተማው ከእስያ ሀገር ከትያጥሮን ከተማ የሆነች ሊዲያ የምትባል ነጋዴ እንዴት እንደተለወጠችና እንደተጠመቀችም ይተርካል። **በሐርያት ሥራ መጽሐፍ ሐዋርያት ለወንጌል ስብከት በብዛት ወደ ምኩራብ ይሄዱ እንደነበረ እናውቃለን። በፊልጵጵዩስ ከተማ ግን ጸሎት ወዳለበት ወደ ወንዝ ዳር ነበር የሄዱት (ሐዋ. ሥራ 16:13)። የሊዲያ ከተማ ደግሞ** ትያጥሮን በእስያ የምትገኝ በራዕይ መጽሐፍ ከተጠቀሱት ሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት አንዱ ነው (ራዕይ 2:18)።

ሉቃስም ከመቄዶኒያ ከጢሮአዳ ወይም ሌላ ስም ተሰጥቶት ከነበረው ከአሌክሳንደሪያው ጢሮአዳ የሆነ የግሪክ ሰው የሆነ እንደነበረ ይታወቃል። ከዚህ በኋላ ሉቃስ እራሱ ከሚስዮናዊያኑ ቡድን አባል አንዱ እንደሆነ አድርጎ ታሪኩን ይቀጥላል። ለምሳሌ በ16:10 "እኛ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው አብሮ መሆኑን ነው።

**ሐዋ. ሥራ 16:16-24 የፊልጵስዩስ ከተማ ወንጌል፣ስደትና ውጤቱ**

ስደት፡- በዚህ ክፍል በሚስዮናውያኑ ላይ የተነሳው ከባድ ስደት መነሻዋ በአጋንንት መንፈስ ትኖር የነበረችው ገረድ ነጻ መውጣት መሆኑን ይናገራል። ማለትም፤ ከገረዷ ጥንቆላ ይገኝ የነበረው ጥቅም ወይም ገንዘብ ከአሳዳሪዎቹ ስለቀረባቸው መሆኑን ክፍሉ ይናገራል። ሐዋ 16:19 "አሳዳሪዎቿም የገንዘብ ማግኛ ተስፋቸው ወጥቶ መሄዱን በተረዱ ጊዜ፣ ጳውሎስንና ሲላስን ይዘው እየጐተቱ ባለ ሥልጣኖች ወዳሉበት ወደ ገበያ ቦታ አመጧቸው"። በዚህም ምክንያት ሁሉም ተባብረው ሚስዮናውያኑን ወደ ወህኒ ቤት እስገቧቸው። የወንጌል መልዕክተኞቹ ታስረውም ለእግዚአብሔር ምስገና ሲያቀርቡ እናያለን።

**ሐዋ. ሥራ 16:25-40 ወንጌል በፊልጵስዮስ ወህኒ ቤት**

**የዚህ ክፍል ታሪክ የሚያስረዳን የወንጌል ሥራ ከሰው አቅም በላይ ሲሆን እግዚአብሔር ጣልቃ የሚገባ መሆኑን ነው። እግዚአብሔር** በወህኒ ቤት በመለኮታዊ ጣልቃ ገብነት የመሬት መንቀጥቀጥ አድርሶ የወህኒውን ደጆች እንደከፈተና፤ በዚህም ምክንያት የወህኒው ጠባቂና ቤተሰቦቹን ድነው እንደተጠመቁ ታሪኩ ይነግረናል። በዚህ ክፍል ሰው ሁሉ መጠየቅ ያለበትን መሠረታዊ ጥያቄ የወህኒ ጠባቂው ሲጠይቅና መልሱንም ሲያገኝ እናያለን። የወህኒውም ጠባቂው ይዞአቸው ከወጣ በኋላ፣ "እናንት ሰዎች፤ <u>**እድን ዘንድ ምን ላድርግ?" (ሐዋ. ሥራ 16:30)**</u> አላቸው ።

እነርሱም፣ <u>**"በጌታ በኢየሱስ እመን፤**</u> አንተም ቤተ ሰዎችህም ትድናላችሁ" አሉት። ከዚያም ለእርሱና በቤቱ ላሉት ሰዎች ሁሉ የጌታን ቃል ተናገሩ። የወህኒ ቤት ጠባቂውም ሌሊት በዚያኑ ሰዓት ወስዶ ቍስላቸውን አጠበላቸው፤ ወዲያውም እርሱና ቤተ ሰቡ ሁሉ ተጠመቁ። የወህኒ ቤቱ ጠባቂም ወደ ቤቱ ወስዶ ማእድ አቀረበላቸው፤ ከቤተ ሰቡም ሁሉ ጋር በእግዚአብሔር በማመኑ በደስታ ተሞላ (ሐዋ. ሥራ 16:30-34)። ድነት በክርስቶስ ብቻ እንደሆነ ግልጽ ነው።

**የመወያያ ጥያቄዎች**

1. በሐዋ. ሥራ 16:1 መሠረት ሐዋርያው ጳውሎስ ወደ ልስጥራንና ደርቤን ተመልሶ መሄዱ ለምን አስፈለገ? ተነጋገሩ።
2. ሐዋ. ሥራ 16:1-2 በማንበብ የጢሞቴዎስን ማንነትና የህይወት ምስክርነቱን ተነጋገሩ።
3. ሐዋ. ሥራ 16:3 በዚህ ክፍል ሐዋርያው ጳውሎስ ጢሞቴዎስን መግረዝ ለምን አስፈለገው? ተወያዩ።
4. ከቁ.6-10 ስናነብ መንፈስ ቅዱስ በህልም ምን ማድረግ እንዳለባቸው ነገራቸው? ይህ ክፍል ከማቴ ወንጌል 28:19-20 ተስፋ ምን ይገናኛል?
5. ከቁ.11-15 በማንበብ ስለ መቄዶንያና ስለ ልድያ ማንነት ተወያዩ።

6. ሐዋ. ሥራ 16:19 መሠረት በሐዋ ጳውሎስና ሲላስ የተነሳው የስደቱ ምክንያት ምን ነበር?
7. ከቁ.25-29 በማንበብ እግዚአብሔር በነገሩ እንዴት ጣልቃ እንደገባና ምን ውጤትስ እንዳስገኘ አብራሩ።
8. ሐዋ. ሥራ 16:30-34 በዚህ ክፍል የወህኒ ጠባቂው ስላቀረበው ጥያቄና የመልዕክተኞቹንም መልስ በማንሳትና በመወያየት ክፍሉ ለዛሬ ዘመን ስላለው አስፈላጊነት ተነጋገሩ፡፡
9. ካዛሬው ጥናት በአጠቃላይ የተማራችሁትን አካፍሉ እንዲሁም ለሃይማኖተኞችና አሳዳጆች እንፀልያለን።

**መ ደ ም ደ ሚ ያ**

የሐዋርያት ሥራ 16 ለአብያተ ክርስቲያናት ሌሎች ህብረቶችንም ይሁን አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናትን ስለመትከልና ስለ ቀጣይ ክትትል አስፈላጊነት ይነግረናል።መትከል፣ መንብኘትና ማጠናከር አስፈላጊ ነው። እንዲሁም በወንጌል ሥራ ላይ አገልጋዮች ብርቱ ፈተና ሲገጥማቸው እግዚአብሔር በእርሱ ሉዓላዊ ዕውቀት አስፈላጊ ከሆን በሚታይ መልኩ ጣልቃ ሊገባ እንደሚችልና፤ በአጠቃላይም እርሱ አንደቃሉ ዘወትር መሠረት አብሮን እንደሚሆን ያስተምረናል። በተጨማሪም እውነተኛውንና ብቸኛውን የመዳን መንገድ ይህ ክፍል በግልጽ አስቀምጦታል።

**ጥናት አሥራ አንድ**

**የጥናቱ ርዕስ፡-** በጽናት ማገልገል (ወንጌል በተሰሎንቄ፣በቤርያና በአቴንስ)

**የንባቡ ክፍል፡-** የሐዋርያት ሥራ 17፡1-34 (ሁለተኛ የወንጌል ጉዞ የቀጠለ)

**ዓላማ፡-**

የወንጌል አገልግሎት ዝግጅትን፣መታዘዝን፣ብርታትንና ጽናትን እንደሚያስፈልገው በመገንዘብ የተሰጠንን መንፈሳዊ የአንባሳደርነት ተግባር እንድንወጣ ለማሳሰብ፡-

**መግቢያ**

ባለፈው ጥናታችን ላይ በፊልጵስዮስ ከተማ የሐዋርያውንና የባልደረቦቹን የወንጌል ተጋድሎ እንዲሁም በፊልጵስዩስ ወህኒ ቤት ጌታ ያደረገውን ተአምራትና ውጤቱን ተመልክተናል። በዛሬው ጥናታችን ደግሞ በተሰሎንቄ፣በቤርያና በአቴንስ የነበረውን የሚያስደንቅና በጽናት የተሞላ የወንጌል አገልግሎት እናያለን።

**የንባቡ ክፍል አጭር ማብራሪያ**

**ሐዋ. ሥራ 17:1-9 የተሰሎንቄ አገልግሎትና ተግዳሮቱ**

ተሰሎንቄ በወቅቱ የመቄዶንያ አውራጃ የአካባቢው ታዋቂ ከተማ ነበረች፡፡ በዚህች ከተማ ሐዋርያው ጳውሎስ በደረሰ ጊዜ እንደልማዱ ወደ አይሁድ ምኩራብ በመግባት ለሶስት ሰንበት ያህል ጊዜ ወስዶ ከመጽሐፍት እየጠቀሰ ይናገር ነበር። በዚህ ክፍል “መጽሐፍት” የሚለው ቃል የብሉይ ኪዳን መጽሐፍትን እንደሆነ ይታወቃል። በዚህም በትምህርቱ ሐዋርያው ስለ ክርስቶስ መከራ መቀበል፣ ስለ ሞቱና ስለ ትንሳኤው በሚገባ በማብራራቱ ፤ትምህርቱን የተረዱ የግሪክ ሰዎችና አያሌ የታወቁ ሴቶች የሰሙትን ተቀብለው አምነዋል። ወንጌል ኃይል አለውና ይሰራል። አይሁድ ግን በዚህ መልካም ሥራ በመቅናት ስራ ፈቶችንና ክፉ ሰዎችን በማሰባሰብ ከተማውን እንዳወኩት ታሪኩ ያስረዳል። ይህም አልበቃ ብሎአቸው ቄሳርን በመቃወም “ኢየሱስ የሚባል ሌላ ንጉስ አለ” እያሉ ያስተምራሉ በማለት በሀሰት ከሰሷቸው። ነገር ግን እግዚአብሔር ያለ ፍሬ አልተዋቸውም።

- **ሐዋ. ሥራ 17: 10-15 የቤርያ አገልግሎትና የተግዳሮቱ መቀጠል**

ቤርያ ስልሳ ማይል ያህል ከተሰሎንቄ በስተምዕራብ በኩል ርቃ የምትገኝ ከተማ ነች። (የአዲስ ኪዳን ማብራሪያ ገጽ 322 መመልከት ይችላሉ)፡፡ በአሁኑ ጊዜ በሰሜናዊ ግሪክ የምትገኝ ቬሪያ ከተማ ነች (ከአልባኒያ በስተ ምስራቅና ከመቄዶኒያ በስተደቡብ ትገኛለች)። በተሰሎቄ ከተማ በነ ሐዋርያ ጳውሎስ ላይ በተነሳው የውሸት ክስና ረብሻ ምክንያት ወንድሞች ጳውሎስንና ሲላስን በሌሊት ወደ ቤርያ ሰደዷቸው፡፡ ቤርያ በደረሱም ጊዜ ወደ ምኩራብ ገቡ። የቤርያም ሰዎች ከተሰሎንቄ ሰዎች ይልቅ የሚያስደንቁ አስተዋዮች እና ልበ ሰፊዎች በመሆናቸውም ዕለት ዕለት መጽሐፍትን በመመርመር ቃሉን ተቀበሉ፡፡ በተሰሎንቄ ያሉ አይሁዶች ግን እነ ሐዋርያው ጳውሎስ በቤርያ የእግዚአብሔርን ቃል እያስተማሩ እንዳሉ በሰሙ ጊዜ፤ ወደ ቤርያ በመምጣት እንደልማዳቸው ከተማውን ማወክ ቀጠሉ፡፡ በዚህም ሁከት ምክንያት ወንድሞች ሲላስንና ጢሞቴዎስን እዚያው እንዲቀሩ በማድረግ ሐዋርያው ጳውሎስን ግን ወደ አቴንስ እንዲሄድ እስከ ባህር ወደቡ ድረስ ሸኙት። ወንጌል ይቀጥላል!

- **ሐዋ. ሥራ 17፡ 16-22 በአቴንስ ለፈላስፎች ወንጌልን መብሰር**

ከክርስቶስ ልደት ከ300-500 ዓመት በፊት በነበሩ ዓመታት በጠቅላላው ምዕራቡ ዓለም ውስጥ አቴንስ ታላቅ፣ስፍራ የነበረባት ከተማ ነበረች፡፡ የግሪክ ዋና ከተማ ከመሆንዋም በላይ፤ በጣም የታወቁና ዝነኛ የምዕራቡ ዓለም ፈላስፋዎች የምኖሩባት የጥንት ከተማ ነበረች። (ለተጨማሪ ዕውቀት የአዲስ ኪዳን ማብራርያ ገጽ 323 መመልከት ይቻላል)፡፡ ሐዋርያው ጳውሎስ አቴንስ እንደደረሰ በከተማው ውስጥ ጣኦት ሞልቶ በማየቱ መንፈሱ ተበሳጨ። ስለዚህ በምኩራብና በገበያ ሥፍራዎች እግዚአብሔርን ከሚያመልኩ የግሪክ ሰዎች እንዲሁም በየቀኑ ከሚያገኛቸው ጋር ይነጋገር ነበር። የከተማይቱም ሰዎች አዳዲስ ነገሮችን መስማት ይወዱ ነበር (17:22)። በዚህ ክፍል የተጠቀሰው "አርዮስፋጎስ" ትርጉሙ በግሪክ የአሬስ ኮርብታ ማለት ሲሆን " አሬስ " በግሪክ የነጎድጓድና የጦርነት አምላክ ሲሆን በሮማውያን ዘንድ ደግሞ "ማርስ" ተብሎ ይጠራል ቦታውን እንደ ፍርድ ቤትም ይጠቀሙበት ነበር።በጊዜው ይገዛ የነበረው ንጉስ ግማሽ ሰውና ግማሽ አማልክት ይመስል ነበር ይባላል።

- **ሐዋ.ሥራ 17፡23-34 የሐዋርያው ጳውሎስ የወንጌል ስብከት አቀራረብ (የማይታወቅ አምላክ ማን ነው?)**

በዚህ ክፍል መሠረት የአቴና ሰዎች ከሚያመልኳቸው አማልክት አንዱ "የማይታወቅ አምላክ" የሚል ነበር። **<u>ሐዋርያው ይህንን "የማይታወቅ አምላክ" የሚለውን ነገር ሲሰማ ክርስቶስን የመስበኪያ ዋና መንገድ አድርጎ ተጠቅሞበታል</u>**።

**የመወያያ ጥያቄዎች**

1. በሐዋ.ሥራ 17:1-4 መሠረት በተሰሎንቄ ከተማ ስንት ሳምንት ከመጽሐፍት አስተማሩ? እነዚህ መጽሐፍት ምንድ ናቸው?
2. በቁ.3 መሠረት በተሰሎንቄ ምኩራብ የስብከታቸው ዋና ነገር ምን ነበር (ይህ በጣም መሠረታዊ ነገር ነው)? ውጤቱስ?
3. ሐዋ. ሥራ 17:5-9 ስናነብ በሚስዮናውያኑ ላይ የተነሳው የስደቱ ዋና ምክንያት ምን ነበር? ከሉቃስ 23:2 ጋር ምን ግንኙነት አለው?
4. ከቁጥር 10-12 ስናነብ የቤርያ ሰዎች አስደናቂ ባህርያቸው ምንድ ነበር? መልዕክተኞቹ ከከተማይቱ ምን ፍሬ አገኙ?
5. ሐዋ. ሥራ 17:16-17 በማንበብ ሐዋ ጳውሎስን ምን እንዳበሳጨውና ዕለት ዕለትም ምን ያደርጉ እንደነበሩ ተወያዩ።
6. ከቁ.18-21 በአቴንስ ስለነበሩ ሰዎች አስገራሚ ባህርያት ተነጋገሩ።
7. የአቴንስ ሰዎች ሐዋርያው ጳውሎስን "ስለ አዳዲስ ባዕዳን አማልክት የሚናገር ይመስላል" የሚሉት ምኑን ነው?
8. የሐዋ. ሥራ 17፡22-34 በማንበብ ሐዋርያው ጳውሎስ ስለ "የማይታወቅ አምላክ" ምን ይናገራል? እንዴት ክርስቶስን ለመስበክ ተጠቀመ?
9. ቁጥር 34 ስናነብ ታሪክ ጸኃፊው ሉቃስ ስለ ስብከታቸው ውጤት ምን ይነግረናል?
10. ከዛሬ ጥናት ከሐዋርያው የወንጌል ስብከት ዘዴ ምን እንማራለን? አካፍሉ?
11. ለሚቀጥለው ሳምንት ወንጌል ከአንድ በላይ ለሆኑ ሰዎች ሰብካችሁ ምን ዘዴ እንደተጠቀማችሁ በሚቀጥለው ጥናት መስክሩ። ለዚህም የቤት ሥራ በመጸለይ እንለያያለን።

***መ ደ ም ደ ሚ ያ***

በዚህ ጥናት፤ ወንጌል መከራን አልፎ በተሰሎንቄ፣በቤርያና በአቴና እንዴት እንደደረሰ አይተናል። የእያንዳንዱ ከተማ ሰዎች ባህሪያቸው የተለያየ እንደሆነ ሐዋ. ሥራ 17 ላይ በግልጽ ተቀምጦአል። ወንጌል አመጽን፣ፍልስፍናንና የጣኦት አምልኮን አልፎ ወደ ሰዎች ሕይወት ለማዳን ሊገባ የሚችል ኃይል ነው። የአጋንንትን፣የሰዎችን ፍልስፍናንና የልማድ ኃይማኖትን አልፈን ወንጌል መመስከር አለብን።

**ጥናት አሥራ ሁለት**

**የጥናቱ ርዕስ፡-** የወንጌል ዘመቻ (ወንጌል በቆሮንቶስ ከተማ)

**የንባቡ ክፍል፡-** የሐዋርያት ሥራ 18፡1-28

**ዓላማ፡-**የምስራቹን የወንጌል ቃል ሰምተን ካመንበት ቀን ጀምሮ ይህንን ታላቅ ዜና ለሌሎች ለማዳረስ አደራ ስላለብን ቃሉን በጊዜውም አለጊዜውም ማወጅ እንዳለብን ለማሳሰብ፡፡

***መግቢያ***

ባለፈው ጥናታችን በሐዋ.ሥራ 17 መጨረሻ ላይ ሐዋርያው ጳውሎስ በሁለተኛው የወንጌል ጉዞው በአቴንስ የሙታን ትንሳዔን በመስበክ የሚያስደንቅ አገልግሎት እንዳገለገለ ተመልክተናል። ይህንኑ የወንጌል ዘመቻውን በማስፋት በቆሮንቶስ እንዴት እንደቀጠለ በዛሬው ጥናታችን እንመለከታለን።ሐዋ. 18

**የቆሮንቶስ ከተማ፡-**ቆሮንቶስ በአሁኑ ጊዜ በግሪክ ውስጥ የምትገኝ ከተማ ስትሆን በውቅቱ በባህር ዳር ወደብ የነበረች የንግድ ከተማ እንደሆነች ይታወቃል። ከተማው በጥንት ጊዜ በአካይያ አውራጃ ይገኝ የነበረ የሮማ ግዛት ነው። ይህ ከተማ በሥነ ምግባር እና በመንፈሳዊነት እጅግ የተበላሸ ነበር። ከተማው በተለያዩ የጣኦት አማልክት የታወቀ ነበር። ወደ አሥራ ሁለት የሚሆኑ አማልክትም በቆሮንቶስ ከተማ እንደነበሩ ይነገራል። ብዙ የጣኦታት ቤተ መቅደስም ነበሩት። ከእነዚህም ታዋቂዋ የአፍሮዲጡስ ቤተ ጣኦት ሲሆን የፍቅር አምላክ የምትመለክበት ቤተ ጣኦት ነበረች። ከክፉ አምልኮ አንዱ ዝሙት ነበር። “ቆሮንቶሳዊ” ተብሎ መጠራት ልቅ ከሆነ የዐመጻኝነት ሕይወት ጋር ተመሳሳይነት አለው። ለፈውስ አምላክ ደግሞ የተሰራ የአስክሌፐደስ የጣኦት ቤት ነበር። ለአይሁዶችም ደግሞ ምኩራብ ነበራቸው። አይሁዶች በምኩራብ አምላካቸውን ያመልኩ ነበር እንዲሁም ትምህርትና ማህበራዊ ኑሮም ያደርጉ ነበር። ለዚህ ከተማ ወንጌል በሐዋርያው ጳውሎስ የተሰበከው በሁለተኛው የሚስዮናዊነት ጉዞ ነበር (ሐዋ 18:1-21)። ጌታ ለጳውሎስ በራዕይ ተገልጦለታል፣ ብዙዎች እንደሚያምኑና የበረታ ተቃውሞ በተልዕኮው ላይ እንደማይኖር ተናገረው (ሐዋ. 18፡9-10)። ሐዋርያው ጳውሎስ አቂላንና ጵርስቅላን በዚህ ከተማ አገኛቸው። አቂላ እና ጵርስቅላ ያመኑ አይሁዶች ሆነው በድንኳን ሥራ በቆሮንቶስ ተሰማርተው ነበር።እነርሱም በቀላውዴስ ቄሳር ከሮሜ በ49ዓ.ም እንዲወጡ ተገደው የወጡ ናቸው። ሐዋርያው ጳውሎስ በከተማዋ ለአስራ ስምንት ወራት በአገልግሎት ቆይቷል (ሐዋ. 18፡11) (በ2017 ከነበረው ከቤተ ክርስቲያናችን የ1ቆሮንቶስ መልዕክት ጥናት የተወሰደ)።

***የንባቡ ክፍሉ አጭር ማብራሪያ***

***ሐዋ. ሥራ 18፡1-4 የሐዋርያው ወደ ቆሮንቶስ ከተማ መግባት***

ሐዋርያው ከአቴንስ ወደ ቆሮንቶስ በመጣ ጊዜ በዛ የሚያውቀው ማንም ሰው አልነበረውም:: ነገር ግን ከ**41 – 54 ዓ/ም** የሮም ንጉስ የነበረው ቀላውዴዎስ ቄሳር አይሁድን ከሮም ባስወጣበት ጊዜ፤ አቂላና ጵርስቅላ ሮምን ለቀው ወደ ቆሮንቶስ በመሰደዳቸው ምክንያት ሐዋርያው በወገኑ የጳንቶስ ሰው የሆነውን አቂላን ሊያገኘው ችሏል። ከእርሱ ጋርም በመሆን ለአገልግሎቱና ለኑሮው የሚሆነውን ገቢ ድንኳን በመስፋት ያገኝ ነበር። ሐዋርያው በዚህ በቆሮንቶስ ቆይታው በሌሎች ከተሞች እንደሚያደርገው ሁሉ በቆሮንቶስ ባለው ምኩራብ በየሰንበቱ ወንጌልን ለአይሁዳውያን እና ለግሪክ ሰዎች ያስተምር ነበር።

### ሐዋ. ሥራ 18፡5-17 በቆሮንቶስ አገልግሎቱ ሐዋርያው ላይ የተነሳ ተቃውሞ እና ከጌታ ያገኘው ማበረታቻ

ሲላስና ጢሞቴዎስ ከመቄዶንያ ወደ ቆሮንቶስ በወረዱ ጊዜ እጅግ ግሩም የሆነ ስለ ተሰሎንቄ ቤተክርስቲያን ልብ የሚያሳርፍ ዜና ይዘው መጡ። (1ተሰሎ 3፡6-10) በዚህ ሰዓት ደግሞ ሐዋርያው በሚያስደንቅ ሁኔታ ወንጌልን ለአይሁድ በመመስከር ለቃሉ እየተጋ ነበር። በሌሎች ከተሞች እንደሚደረገው ሁሉ በዚህም አገልግሎቱ ከአይሁድ ከፍተኛ ተቃውሞ እና ስድብ ገጠመው። እርሱም “እኔ ንጹህ ነኝ፡ እንግዲህ ደሙ በራሳችሁ ላይ ነው” በማለት ከእንግዲህ ፊቴን ወደ አህዛብ አዞራለሁ አላቸው።

ሐዋርያው ወደ አህዛብም በሄደ ጊዜ ሲዮስጦስ ወደሚባለው እግዚአብሔርን ወደ ሚያመልክ ግሪካዊ ሰው ቤት ገባ፡ የዚህ ሰው ቤትም በምኩራብ አጠገብ ስለነበረ ቀርስጶስ የሚሉት የምኩራብ አለቃ ከነቤተሰቡ ድነትን ከማግኘቱም በላይ ብዙዎች የቆሮንቶስ ሰዎች ወንጌልን በመስማት አምነው ተጠመቁ። ሐዋርያው በዚህ አገልግሎቱ ላይ እያለ ጌታ በራእይ እንዲህ በማለት ሐዋርያውን አበረታታው **”ጌታም ሌሊት በራእይ ጳውሎስን፦ እኔ ከአንተ ጋር ነኝ፥ ማንም ክፉ ሊያደርግብህ የሚነሣብህ የለምና አትፍራ፥ ነገር ግን ተናገር ዝምም አትበል፡ በዚህ ከተማ ብዙ ሕዝብ አሉኝና አለው”** (ሐዋ. ሥራ 18፡9-10)። የአይሁድም ተቃውሞ በመቀጠሉ አይሁድ በአንድ ልብ ሆነው ተነሱበት፡፡እግዚአብሔርንም ያመልኩት ዘንድ ሰዎችን ያግባባል በማለትም ከሰሱት፡፡ ነገር ግን ሐዋርያው የእግዚአብሔርን ቃል እያስተማረ በመካከላቸው ለአንድ ዓመት ከስድሰት ወር በማስተማር ተቀመጠ።

### ሐዋ. ሥራ 18፡18-21 የሐዋርያው ወደ ኤፌሶን ጉዞ

ሐዋርያው በዚህ ብዙ ቀኖች ተቀምጦ ካገለገለ በኋላ ወንድሞችን ተሰናብቶ ከኤፌሶን ወደ ቂሣርያ ከቂሣርያ ወደ ኢየሩሳሌም ከኢየሩሳሌ ወደ ሶርያ አንጾኪያ ሄዷል (የወንጌል ጉዞ ካርታ መመልከት ይችላሉ)። ነገር ግን እየሄደ በመንገድ ላይ ስለትም ስለነበረበት በክንክራዖስ ጠጉሩን ተላጨ፡፡ ይህን ያደረገበት ምክንያት “**አይሁዳውያን በየጊዜው ስእለት ያደርጉ ነበር። ሐዋርያው ጳውሎስ ስእለት ያደረገው ምናልባትም በቆሮንቶስ በነበረበት ጊዜ ጥበቃ ላደረገለት ለእግዚአብሔር ምስጋና ለመስጠት ይሆናል። እንዲህ ዓይነት ስእለት ከተደረገ በኋላ ስእለቱን ያደረገው ሰው የስእለቱ ጊዜ እስኪያበቃ ድረስ ጠጉሩን እንዲላጭ አይፈቀድም። ስእለቱ መጨረሻ ቀን ግን ይላጭና ጠጉሩን ለእግዚአብሔር ያቀርባል” (ዘኁልቁ 6፡1-21 የአዲስ ኪዳን ማብራርያ ገጽ 325 መመልከት ይችላሉ)።**

ኤፌሶን በደረሰ ጊዜም  አቂላንና ጵርስቅላን በዛ በመተው እርሱ ግን ወደ ምኩራብ በመግባት በአይሁድ ዘንድ አገልግሎቱን ቀጠለ። አገልግሎቱንም ሲጨርስ እንዲቆይ በጠየቁትም ጊዜ የሚመጣውን በዓል በኢየሩሳሌም አደርጋለሁ ነገር ግን እግዚአብሔር ቢፈቅድ  ወደ እናንተ ተመልሼ እመጣለሁ በማለት ጉዞውን ከኤፌሶን ወደ ቂሳርያ ቀጠለ።

**ሐዋ. ሥራ 18፡24-28  የጵርስቅላ፡አቂላና አጵሎስ በኤፌሶን መገናኘት**

**ይህ ክፍል የሁለተኛ የወንጌል ጉዞ መ ደ ም ደ ሚ ያ ክፍል ነው።** በዚህ ቦታ ጵርስቂላ  እና አቂላ በኤፌሶን በነበሩበት ጊዜ በወገኑ የእስከንድርያ የሆነ አይሁዳዊ አጵሎስ የሚሉት ሰው ወደ ኤፌሶን መጣ፡፡ ይህ ሰው በመጽሐፍ ቅዱስ እውቀቱ እጅግ የበረታ ፡ የጌታ መንገድ የገባውና የተረዳ፡ የዮሐንስን ጥምቀት ብቻ የሚያውቅ፡  በመንፈስ የተቃጠለና ትክክለኛውን ትምህርት የሚያስተምር ሰው ነበር። ጵርስቅላ እና አቂላ ስለዚህ ሰው በሰሙ ጊዜ ወደ ራሳቸው አምጥተው የእግዚአብሔርን መንገድ ከፊት ይልቅ በደንብ አርገው ገለጡለት። አጵሎስ ወደ አካይያ ለመሄድ በመፍቀዱ ወንድሞች እርሱን በማበረታታት እና በማጽናናት፤ በዚያ ቅዱሳኖች እንዲቀበሉትም ደብዳቤ ጽፈው በማስያዝ ሸኙት፡፡ በአካይያ ወገኖችም ጋ በደረሰ ጊዜ ከመጽሐፍ እየገለጠ ያስተምርና በጸጋው ያገለግላችው ነበር።

**የመወያያ   ጥያቄዎች**

1. ሐዋ. ሥራ 18፡1-4 መሰረት በማድረግ ሐዋርያው ከአቴንስ ወደ ቆሮንቶስ በመጣ ጊዜ እነ ማንን አገኘ አገልግሎቱስ ምን ነበር? አብረውስ ምን በመስራት ይተዳደሩ ነበር?
2. በሐዋ.ሥራ 18፡5 ላይ ሲላስና ጢሞቴዎስ ከመቄዶንያ ወደ ቆሮንቶስ በወረዱ ጊዜ ሐዋርያው በምን ተግባር ላይ ተሰማርቶ ነበር?
3. የሐዋ. ሥራ  18፡6-8 በማንበብ ሐዋርያው በአገልግሎቱ ላይ ተግዳሮት በገጠመው ጊዜ ለአይሁድ የተናገረው ነገር ምንድን ነው? በመቀጠልስ ወደ ማን ቤት ሄደ?
4. በሐዋ.ሥራ 18፡9-11 ጌታ በራእይ ለሐዋርያው ምን አለው? ይህስ መልእክት ምን ይረዳዋል?
5. ሐዋርያው በሐዋ.ሥራ 18፡12-17 አይሁድ በጋልዮስ ፊት ሐዋርያውን የከሰሱበት ምክንያቱ ምን ነበር? ውጤቱስ በምን መልኩ ተጠናቀቀ?
6. ሐዋ. ሥራ 18፡18-21 በማንበብ የተረዳችሁትን ለቡድናችሁ አካፍሉ።
7. ከሐዋ.ሥራ 18፡22-25 ስለ አጵሎስ የተገነዘባችሁትን ተነጋገሩ።
8. ሐዋ. ሥራ 18፡26-28 በማንበብ አቂላ እና ጵርስቅላ በአጵሎስ ህይወት ውስጥ ላይ የነበራቸውን ድርሻ ተወያዩ? ይህ ክፍል ስለ አጵሎስ ምን በመናገር ይደመድማል?

ሐዋ. ሥራ 18:9-10 በማንበብ በሕይወታችን እንዲተገበር በመጸለይ እንለያያለን።

**መ ደ ም ደ ሚ ያ**

መዳን ካገኘንበት ቀን ጀምሮ ልንታዘዘው የሚገባ በልባችን ውስጥ የሚኖር፣ ምንጊዜም የማይዘነጋ እና ነፍሳችንን እረፍት የሚነሳ ትልቅ ቁም ነገር አለ፡፡ ይህም ቁም ነገር የዳንበትን የሰማዩን ሚስጥር ማብሰር፡መናገር እና መስበክ ነው።በዚህ ባጠናነው ምዕራፍ በሐዋርያው እና በአጵሎስ ህይወት ውስጥ ድንቅ የወንጌል ስራ ተመልክተናል። ዛሬም በዚህ ዘመን ትኩረት ሰጥተን የምንሰራውና ግድ የሚለን ጉዳይ መሆን እንዳለበት ለአፍታም ሊዘነጋ አይገባም።

**ጥናት** አሥራ ሶስት

ሶስተኛው የወንጌል ጉዞ ተጀመረ

**ርዕስ፡-**ወንጌልና የጌታ ተአምራት (በኤፌሶን ከተማ)

**የንባብ ክፍል፡-** የሐዋ. ሥራ 19፡1-41

**ዓላማ፡-**የወንጌልን ሥራ በምንሰራበት ጊዜ ሁሉ የእግዚአብሔር መገኘት በተለየ መልኩ እንደሚገለጥ እና ጌታ ከእኛ ጋር አብሮ እንደሚሰራ ለማሳሰብ፡-

***መግቢያ፡-***

ሐዋርያው ጳውሎስ በሐዋ.ሥራ ምዕራፍ 18 ወደ ቆሮንቶስ በመጣበት ወቅት ድንቅ አገልግሎትን እንዳገለገለ፡ በአገልግሎቱም ምክንያትም ተቃውሞ እንደተነሳበት ፡ ነገር ግን አያሌ ቀናትን በዚሁ ከተማ ካገለገለ በኋላ ጉዞውን ወደ ቂሣርያ ከዚያም ወደ ኢየሩሳሌም ከዚያም ወደ ተነሳበት ወደ አንጾኪያ ማቅናቱን ተመልክተናል። ይህም የሁለተኛው የወንጌል ጉዞ መ ደ ም ደ ሚ ያ ነበር።

የዛሬው ጥናት ደግሞ ሶስተኛው የሚስዮናውያን የወንጌል ጉዞ ጅማሬ ነው። ወንጌል በኤፌሶን ከተማ፡- በኤፌሶን ሐዋርያው ጳውሎስ ወንጌልን በሁለተኛ የወንጌል ጉዞ በተለያዩ መንገዶች እንዳደረሰ ይታወቃል። በሦስተኛው የወንጌል መልእክተኝነት ጉዞው ውስጥ ለሦስት ዓመታት ያህል ያገለገለባት ቦታ ተብሎ ይታወቃል። ይህም የሚያሳየው ሐዋርያው ጳውሎስ በወንጌል መልእክተኝነት ጉዞው ከየትኛውም ስፍራ በላይ በኤፌሶን ብዙ ጊዜ መቆየቱን ነው።

ጳውሎስ በአሁኗ ቱርክ ውስጥ የነበረችውን ኤፌሶንን እንደ ቁልፍ የአገልግሎት መንደርደሪያ ከተማ አድርጓታል (የሐዋ. ሥራ 19፡10)። በወቅቱ የኤፌሶን ከተማ ዋነኛ የወደብ ከተማና የእስያ አውራጃ መዲና ነበረች። በከተማይቱ ብዙ አይሁዶችና ሌሎችም ከ500,000 የሚበልጡ ይኖሩ እንደነበር ይገመታል። በዚያ ከነበሩት አይሁዶች አንዳንዶቹ ወደ ክርስትና እምነት ሲመጡ፥ አብዛኞቹ ግን የወንጌሉ ጠላቶች ሆነው ክርስቲያኖችን ያሳድዱ ነበር። ከተማይቷ በባዕድ አምልኮ የሞላ ነበር። በተለይም አርጤምስ የምትባል ጣኦት አምላክ ትታወቅ ነበር።

ዛሬ በምናጠናው በሐዋ.ሥራ ምዕራፍ 19 ላይ ደግሞ ጥናቱን ለማጥናት እንዲመቸን ምዕራፉን በሶስት ከፋፍለን እንመለከታለን። ማለትም

1. የኤፌሶን ቅዱሳን በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅ (ሐዋ. ሥራ 19፡1-7)፤
2. የወንጌል ስርጭትና ተአምራቱ በኤፌሶን (ሐዋ. ሥራ 19፡8-23) እና
3. የህዝብ ሁከት በኤፌሶን ከተማ (ሐዋ. ሥራ 19፡23-41) ናቸው።

**አጭር ትንታኔ (**የሐዋ. ሥራ 19፡1-41**)**

**1. የኤፌሶን ቅዱሳን በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅ (ሐዋ ሥራራ 19፡1-7)**

ሐዋርያው ወደ ኤፌሶን በመጣ ጊዜ ጥቂት ደቀ መዛሙርትን ባገኛቸው ወቅት እንዲህ ሲል ጠየቃቸው፤ “ባመናችሁ ጊዜ መንፈስ ቅዱስን ተቀብላችሁ ነበርን?” እነርሱም እንዲህ በማለት መለሱለት “በፍጹም አልተቀበልንም ይህ አንተ ስለምትነግረን መንፈስ ቅዱስ እንዳለ እንኳ አልሰማንም” ብለው መለሱለት። ሐዋርያውም አስከትሎ ሌላ ጥያቄን እንዲህ በማለት ጠየቃቸው “ ታድያ በምን አይነት ጥምቀት ተጠመቃችሁ” እነርሱም መልሰው “ በዮሐንስ ጥምቀት ነው” በማለት መለሱለት። የዮሐንስ

ጥምቀት በዮሐንስ ወንጌል 1፡26 ላይ እንደተጠቀሰው መጥምቁ ዮሐንስ በዮርዳኖስ ወንዝ በንስሐ እያጠመቀ ከኋላው ለሚመጣው በእሳት ለሚያጠምቀው ለኢየሱስ መንገድ እየጠረገ መሆኑን በዚሁ ክፍል ውስጥ ያመለክታል። ሐዋርያውም ይህንኑ ሀሳብ አስረድቶ እጁን በጫነባቸው ጊዜ መንፈስ ቅዱስ በእነርሱ ላይ ወረደ፤ በሌላም ቋንቋ ወይም ልሳኖች ተናገሩ። በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ይህ የመንፈስ ቅዱስ መውረድ የታየው ይህ አራተኛው ታላቅ ከተማ ነው። ስለዚህ ነገር በሐዋርያት ሥራ ክፍል አንድ በጥናት 7 ላይ በጥልቀት ስላጠናን በዚህ ጥናት አናካትትም።

## 2. የወንጌል ስርጭት እና ተአምራት በኤፌሶን ከተማ (ሐዋ. ሥራ ራ 19፡8-23)

በኤፌሶን ከተማ ሐዋርያው ለሶስት ወር በአይሁድ ምኩራብ ስለእግዚአብሔር መንግስት ይናገርና ያስተምራቸው ነበር። አንዳንድ ሰዎች ግን ልባቸው በእልህ ስለተሞላ በህዝቡ ፊት አካሄዱን እየተሳደቡ ለማመን ልባቸው የጠነከረ ነበር። በዚህን ጊዜ ሐዋርያው ከእነርሱ ፈቀቅ በማለት ያመኑ ደቀ መዛሙርትን በመለየት ጢራኖስ በሚባል ት/ቤት እለት እለት ማስተማሩን ቀጠለ። እንዲሁም እግዚአብሔር በሐዋርያው እጅ ድንቅና ተአምራት ከማድረጉ የተነሳ ሰዎች የልብሱን ጨርቅ ለህመምተኖች ይወስዱም ነበር። ህመምተኞችም ከደዌያቸው ይፈወሱ ነበር:: እንዲሁም ክፉ መናፍስትም ይወጣላቸው ነበር።

ከተማው በብዙ መተተኞች ከመሞላቱ የተነሳ ይህን አስደናቂ ተአምር በመመልከት አንዳንዶች በአጋንንት ላይ የኢየሱስን ስም ያለአግባብ ይጠሩ ነበር። ይህንን ስም ያለአግባብ ከጠሩት ሰዎች መሐል የአስቄዋ ሰባቱ ልጆች ተጠቃሽ ናቸው። ታድያ ይህን የከበረ ስም በአጋንንት ላይ በጠሩ ሰዓት ክፉ መንፈስም ያለበት ሰው ኢየሱስን አውቃለሁ ጳውሎስንም አውቃለሁ በማለት በረታባቸው።እራቁታቸውንም እስኪሆኑ አቁስሎ እንዲሸሹ አደረጋቸው። በጌታም ድንቅ ስራ ምክንያት በኤፌሶን በሚኖሩ ሰዎች ላይ ፍርሃት ሆነ፤ <u>**የኢየሱስ ስምም ተከበረ።ከዚህም**</u> ባለፈ ብዙ ሰዎች ጌታን በማመን ወደ ኢየሱስ ተመለሱ። ከእነዚህም ሰዎችም መሐል አስማተኞች ተጠቃሽ ናቸው።

## 3. የህዝብ ሁከት በኤፌሶን ከተማ ሐዋ. ሥራ 19፡23-41

እነ ሐዋርያው ጳውሎስ በዚህ ከታማ ትልቅ የወንጌል ድልን ባገኙ ጊዜ ድሜጥሮስ የሚሉት አንጥረኛ ሌሎች አንጥረኞችን በማስተባበር የወንጌል ሥራውን ለማሰናከል ህዝቡን በማስተባበር በሁለት ጉዳይ ከተማውን ማመስ ተያያዘው። **አንደኛው** ጉዳይ ነገሩን የሃይማኖት ካባ በማልበስ "እስያ እና አለም ሁሉ የሚያመልካት የታላቂቱ አምላክ የአርጤምስ መቅደስ ምናምን ሆኖ እንዲቆጠር እንጂ ታላቅነትዋም ደግሞ እንዲሻር" (ሐዋ ሥራራ 19፡27) በማለት ነገሩን አጋጋለው። አርጤምስ በህዝቡ ዘንድ ከአማልክት ሁሉ ታላቅና የበለጠች እንደሆነች ይታሰብ ነበር። የአማልክቶችና የሰዎች ሁሉ እናት እንደሆነችም ይታመን ነበር። በቤተ ጣዖቱ ውስጥ ደግሞ እንደተወርዋሪ ኮኮብ ከሰማይ እንደወረደ የሚታሰብ የአርጤምስ ምስል ይገኝ ነበር። የዚህ ምስል የፊት ለፊት ገጽታው ጡቶች በሚመስሉ ነገሮች ተሞልቷል። ስለዚህም ይህ ምስል ብዙ ጡቶች ያሉዋት ሴትን ይወክላል በማለት የኤፌሶን ሕዝብ ያምኑ ነበር (የአዲስ ኪዳን ማብራርያ ገጽ 327)::

ሁለተኛው ደግሞ ሁከቱን ከገንዘብ ጋር በማያያዝ ያነሱት ጉዳይ ነበር። እነዚህ አንጥረኞች ገንዘብን የሚያገኙት በሰው እጅ የተሰሩትን የአማልክት ምስሎች ሰርቶ በመሸጥ ነበር (ሐዋራ ሥራ 19፡26):: ሐዋርያው ጳውሎስ ግን የእነዚህን ሰዎች ገቢ ህዝቡን ወደ ጌታ በመመለስ እጅጉን ቀነሰው። ይህ ከባድ ስደት ሊያስነሳ ምክንያት ሆኗል።

**የመወያያ ጥያቄዎች**

1. ከመግቢያ ስለ ኤፌሶን ከተማ የተረዳችሁትን ጥቂት ነገሮችን ለቡድናችሁ አካፍሉ።

2. የሐዋ. ሥራ 19፡ 1-2 መሰረት በማድረግ ሐዋርያው ወደ ኤፌሶን በመጣ ጊዜ ያገኛቸውን ደቀ መዛሙርት የጠየቃቸው ጥያቄና የሰጡት መልስ ምን ነበር?
3. ከቁ. 19፡ 3-7 መሠረት የኤፌሶን አማኞች በምን ዓይነት ሁኔታ እንደነበሩና ሐዋ ጳውሎስ ከመጣና ካስተማረም በኋላ ምን እንደሆነ አካፍሉ።
4. በሐዋ. ሥራ 19፡8-9 ሐዋርያው ጢራኖስ የሚባል ት/ቤት የመመስረት ዓላማው ምንድን ነው?
5. ከቁ.11-12 እና ሐዋ. ሥራ 5፡15 ላይ የሆነውን ተአምር አሁን ካለንበት ዘመን የእግዚአብሔር አሰራር ጋር እንዴት አስታርቀን መሔድ እንችላለን?
6. ሐዋ. ሥራ 19፡14-17 በማንበብ በዚህ ክፍል የሆነውን ነገር ተነጋገሩ?
7. ከቁ.18-20 ባለው ሀሳብ ላይ በማትኮር ከእግዚአብሔር ታላቅ ስራ የተነሳ የሆነውን ሁኔታ በዝርዝር አብራሩ?
8. ሐዋ. ሥራ 19፡23-29 ክፍል በማንበብ የተረዳችሁትን አብራራ?
9. በጥናት መጽሐፉ ውስጥ እንደተገለጠው አርጤምስ ማን ናት? ለምንስ የሁከቱ መነሻ ምክንያት ለመሆን ቻለች?

ከዛሬው ጥናት ውስጥ የተማራችሁትን ቁም ነገር ለቡድናችሁ በዝርዝር አብራሩ።

### መ ደ ም ደ ሚ ያ

ከእግዚአብሔር ጋር በወንጌል እርሻ ሥራ ስንሰማራ እግዚአብሔር እኛን እንደ መሳርያ አድርጎ ይጠቀምብናል። በስፋት ስራውን የሚሰራው ግን እርሱ እራሱ ነው። በዚህ የወንጌል ሥራ ላይ ቃሉ በሚያስገርም ሁኔታ የሰውን ልብ ነክቶ መቀየሩ ደግሞ እውነት ነው። እንግዲህ የጌታ ስራ በስፋት ሲሰራ ሰይጣን ደግሞ አርፎ ይቀመጣል ብሎ ማሰብ የዋህነት እንደሆነ ከዛሬው ጥናት ተረድተናል። ስለዚህ እኛ የጌታን ስራ እየሰራን የጠላትን ሀሳብ ደግሞ እያፈረስን አገልግሎታችንን ማገልገል አናቆምም።

## ጥናት አሥራ አራት

**ርዕስ፦** አገልግሎትን በታማኝነት መጨረስ

**የንባብ ክፍል፦** የሐዋ. ሥራ 20:1-38

***ዓላማ፦***

አንድ አገልጋይ አገልግሎቱን በታማኝነት መፈጸም እንደሚገባው ለማሳሰብ ነው

***መግቢያ፦***

ሐዋርያው ጳውሎስ መቀመጫውን በኤፌሶን ከተማ አድርጎ በዙሪያው ካሉ ከተሞች ወደ እርሱ የሚመጡትን ሁሉ እያስተማረ በጌታ መንገድ ካጸናቸው በኋላ ወደ መጡበት ከተማ ተመልሰው አገልግሎት እንዲጀምሩ ያሰማራቸው ነበር። ይህንን በሚያደርግበት ሂደት መካከል የአርጤምስ ጣዖትን ክብር ተጋፍቷል በሚል ሐዋርያው ጳውሎስ ተከሶ በኤፌሶን ከተማ ታላቅ ሁከት ተነስቶ ሳይሳካላቸው ተደምድሟል። ጳውሎስም በኤፌሶን ከተማ የተነሳው ብጥብጥና ሁከት እንደ ቀዘቀዘ ከተመለከተ በኋላ ኤፌሶንን ለቅቆ ወደ ሶርያና ኢየሩሳሌም ለመመለስ ፊቱን አዞሯል ። በዛሬው ጥናታችንም የጳውሎስን ጉዞ ወደ መቄዶንያና ግሪክ አገር (ቁ.1-6)፣የመጨረሻውን ጉብኝት በጢሮአዳ (ቁ.7-12)፣ከጢሮአዳ ወደ ሚሊጢኒ መሄዱ (ቁ.13-16)እና ለኤፌሶን ሽማግሌዎች ያደረገው የመሰነባበቻ ንግግር (ቁ.17-38) እንመለከታን። በዚህ የጉዞ ሂደት ላይ ስለተከናወኑት ነገሮች በዝርዝር ከክፍሉ የምንመለከት ይሆናል።

**የክፍሉ አጭር ማብራሪያ፦ 20: 1-38**

ሐዋ. ሥራ 20:1-3 ጳውሎስ ጉዞ በመቄዶንያ አልፎ ወደ በግሪክ አገር በመሄድ በዚያ ሶስት ወር በመቀመጥ አማኞችን መከራቸው፣ አጸናቸው።

ጳውሎስ በኤፌሶን ከተማ የተነሳው ብጥብጥና ሁከት እንደ ቀዘቀዘና ፍሬ አልባ እንደ ሆነ ከተመለከተ በኋላ በዚያ የነበሩትን መክሯቸው ኤፌሶንን ለቅቆ ወደ ሶርያና ኢየሩሳሌም ለመመለስ ፊቱን አዞሯል። በመርከብ ለመሳፈር ዝግጅት ላይ እያለ ግን የቆሮንቶስ አይሁድ እርሱን ለመግደል አድማ እንዳደረጉበት ሰማ። ስለዚህም በባህር ሊያደርገው የነበረውን እቅዱን በመለወጥ በየብስ በመቄዶንያ በኩል አልፎ ለመጓዝ ውሳኔ አድርጓል።

**ከቁ. 4-6** የጳውሎስ የአገልግሎት ባልደረቦች ግን በመርከብ ተሳፍረው ወደ ጢሮአዳ ቀድመው በመድረስ፡ ጳውሎስ እስኪመጣ ድረስ በዚያ ሆነው ይጠብቁት ነበር። በዚህ ወቅት ጳውሎስ በዚያ ጉዞ በፊልጵስዩስ ከተማ ሄዶ ሉቃስንም እንደገና እዚያ አገኘው። ከእርሱ ጋር ተያይዘው ወደ ጢሮአዳ ተጉዘዋል። ቁ. 4 ላይ የተጠቀሱት ወንድሞች ከመቄዶንያ አብያተ ክርስቲያናት የተሰበሰበውን ስጦታ በኢየሩሳሌም ለነበሩ ድሀ ክርስቲያኖች ለማድረስ የተወከሉ በመቄዶንያ፣በገላቲያና በኤፌሶን የነበሩ የተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት ተወካዮች ናቸው። የቆሮንቶስ (አካይያ) ተወካዮች እዚህ ላይ አልተጠቀሱም፡፡ ሆኖም ሌሎች ሁለት ወንድሞች የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያንን ስጦታ ለማድረስ ሳይወከሉ እንዳልቀሩ መገመት ይቻላል።

የሐዋ. ሥራ 20:7 **የጳውሎስ የመጨረሻ ጉብኝት በጢሮአዳ**

***ሐዋርያ*** ጳውሎስና ጓደኞቹ በጢሮአዳ ሰባት ቀን ከቆዩ በኋላ "የሳምንቱ የመጀመሪያ ቀን" ትልቅ ህብረት ነበራቸው። የቅዳሜ አምልኮው ወደ እሁድ መቀየሩ በአዲስ ኪዳን እዚህ ቦታ ተጠቅሶ ይገኛል። ይህ የሆነው የክርስቶስ ትንሳኤ ቀን ስለሆነ ነው(ዮሐ 20:19፣1ቆሮ 16:2)፤እንዲሁም ይህ ቀን በራዕይ "የጌታ ቀን" ተብሏል (ራዕይ 1:10) ። የጢሮአዳ አማኞች እንጀራ ቆርሶ ለመብላት ማለትም የጌታን እራት ሥርዓት ለማክበር በአንድነት ተሰብስበው ነበር።

**ከቁ. 8-12** በዚህ የምሽት ፕሮግራም ላይ ጳውሎስ ረጅም ንግግር በማድረግ ላይ እያለ በዚያ ከነበሩት አንዱ ኤውጢኮስ የሚባል ወጣት ከ3ኛ ፎቅ በመውደቅ የእንቅልፍ ሰለባ ሆኗል። ምናልባት ተሰብስበውበት ከነበሩበት ቤት ከነበረው ብዙ መብራት የሚወጣው ጭስ እንዲያንቀላፉ ምክንያት እንደሆነው ይገመታል። ምክንያቱ ምንም ይሁን ምን እንቅልፍ ስላሸነፈው ከሶስተኛ ፎቅ ወደ ምድር ላይ ወድቋል። ሰዎችም ተሯሩጠው ቢያነሱትም ብላቴናው ወዲያውኑ ሞቶ እንደ ነበር ተገልጿል። ቢሆንም ግን ጳውሎስ ወደ ሞተው ብላቴና ጎንበስ ብሎ እንዳቀፈው ብላቴናውም ወደ ሕይወት እንደ ተመለሰ እንመለከታለን።(ይህን የሐዋርያትን መጽሐፍ የጻፈው ሉቃስ ሐኪም በመሆኑ ብላቴናው በእርግጠኝነት መሞቱን ማረጋገጥ መቻሉን ልብ ይላል)። የጌታን ራት ሥርዓት ከፈጸሙና ምግባቸውንም በአንድነት ከተመገቡ በኋላ ጳውሎስ እስኪ ነጋ ድረስ ከሰዎቹ ጋር ሲነጋገር እንደ ቀየ እናያለን።

የሐዋ. *ሥራ* 20:**13-14 ጳውሎስ ለኤፌሶን ሰዎች ያደረገው ስንብት**

ከጳውሎስ በስተቀር ጓደኞቹ ሁሉ ከጢሮአዳ በመርከብ ተሳፍረው ጉዞ ጀምረዋል። ወደ ሚቀጥለው ወደብ ለመድረስ መርከብዋ ከባሕሩ ጋር በሚገናኘው ልሳነ ምድር ዙሪያ መሄድ ነበረባት። ለጳውሎስ በእግር መሄድ ፍጥነት ስለሚሰጥ ጳውሎስ እስከ ሚቀጥለው ወደብ አሶስ ድረስ በእግሩ መጓዝን መርጧል። ስለዚህም መርከቡን በአሶስ ለመገናኘት ከመሄዱ በፊት በጢሮአዳ አንድ ቀን የማሳለፍ እድልም ነበረው።

**የሐዋ. *ሥራ* 20:15-17 ሐዋርያው በሚሊጢኒ**

ኤፌሶን ከሚሊጢኒ ሰላሳ ማይል ያህል ትርቃለች፡፡ መርከቡ በሚሊጢኒ ጥቂት ቀኖች ስለሚቆይ ወደ ሚሊጢኒ መጥተው ከእርሱ ጋር እንደሚገናኙ ጳውሎስ ወደ ኤፌሶን ቤተ ክርስቲያ ሽማግሎዎች መልእክት ልኮባቸዋል። ጳውሎስ የኤፌሶንን ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ አባት ወይንም መስራች መሆኑ የሚዘነጋ አይደለም። የኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች በሙሉ በጳውሎስ ስብከትና አገልግሎት ነው ወደ ጌታ የመጡት ተብሎ ይታወቃል። በተጨማሪም ለሦስት ዓመት በየቤቱ እየዞረ ያስተምራቸው እንደነበረም ግልጽ ነው። በመሆኑም የቤተ ክርስቲያኒቱ ሽማግሌዎች በሙሉ ጳውሎስን ለማግኘት ናፍቆት እንደ ነበራቸው ሳይታለም የተፈታ ነው።ስለዚህም ሌላውን ጉዳያቸውን ወደ ጎን በመተው ጳውሎስን ለመገናኘት የሠላሣ ማይል ርቀት በእግር ተጉዘው ሚሊጢኒ መጥተዋል።

**የሐዋ. *ሥራ* 20፡18-19** ጳውሎስ ለኤፌሶን ሽማግሌዎች ያደረገው የመሰነባበቻ ንግግር

በኤፌሶን በነበረበት ጊዜ ጳውሎስ ስለ ነበረው ሕይወቱና አገልግሎቱ ለኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ያሳስባቸዋል። ጳውሎስ በፍጹም ትህትና፤ በእንባና በታማኝነት ነበር ያገለገላቸው። በእንባ የሚለው አሳብ ምናልባት ጳውሎስ ስለ ክርስቲያን ወንድሞች ማንባቱን ያመለክታል ይላሉ።

**የሐዋ. *ሥራ* 20፡20-21**

በዚህን ወቅት ሐዋርያው ጳውሎስ ምንም እንኳን የተለያዩ ችግሮችና መከራ ቢደርስበት ለኤፌሶን አማኞች የሚጠቅማቸውን ሁሉ በግልጽ ከመስበክና ከማስተማር ወደ ኋላ አላለም። ጳውሎስ ይሰብክ የነበረው ስለ ክርስቶስ መስቀልም ጭምር እንጂ፡ ደስ የሚያሰኘውንና የሚያጽናናውን የወንጌል መልዕክት ብቻ  አልነበረም። ምንም እንኳን መስቀሉ ለአይሁዳውያን መሰናከያ ለግሪኮች ሞኝነት መስሎ ቢታያቸውም፡፡ (1ቆሮ: 1:23) ሐዋርያ ጳውሎስ ለአይሁድም ሆነ ለግሪክ ያለ አንዳች ፍርሃት ስለተሰቀለው ክርስቶስ ሰብኳል። ከዚህም ሌላ ሁሉም ደግሞ ንስሓ እንዲገቡና ወደ እግዚአብሔርም እንዲመለሱ ለአይሁዳውያንና ለግሪካውያንም አስተምሯል (የሐዋ. 17:30 26:20)።ይሁን እንጂ ንስሓ መግባት ብቻውን

በቂ አይደለም ፡፡ነገር ግን ሰዎች ሁሉ በኢየሱስ ክርስቶስ እንዲያምኑ አስተምሯል።በሄደበት ሁሉ የጳውሎስ ሕይወት ለአዳዲስ ደቀ መዛሙርት ምሳሌ ነበር (1 ቆሮ 11:1፤ፊል 3:17 4:19)።ስብከቱ ፍሬያማ የሆነውም በዚህ ምክንያት ነበር። ሐዋርያው ጳውሎስ የሚያስተምሩትን በተግባር ላይ እንደማያውሉት እንደ ፈሪሳውያን አልነበረም (ማቴ 23:1-3)። በአብዛኞቹ መልእክቶቹ ስለ ሕይወቱና ስለ አገልግሎቱ በግልጽ እንደ ጻፈም እንመለከታለን (1 ቆሮ2:3-5 2 ቆር 6:4-10 1 ተሰ 2:1-12)።

**ከቁ. 22-24**

እነዚህ ቁጥሮች እንደሚያመለክቱን የሐዋርያ ጳውሎስን ታማኝነት ስለተሞላው የአገልግሎት ህይወትና ወደ ኢየሩሳሌም ተመልሶ መሄድ በጣም አደገኛ ጊዜ ሊሆን እንደሚችልና ለዚያም እስከ ሕይወቱ መስዋዕትነት ቆራጥ በመሆን የተዘጋጀ እንደሆነ ነው።

በቆሮንቶስ በነበረበት ጊዜ በይሁዳ ካሉት ከሚያምኑ ሰዎች እጅ እንድድን ጸልዩልኝ በማለት ለሮም ክርስቲያኖች ጽፎላቸው ነበር (ሮሜ 15:31):: ወደ ኢየሩሳሌም በመጓዝ ላይ እያለም እዚያ ሲደርስ እስራትና ችግር እንደሚገጥመው ብዙ መንፈስ ቅዱስ ነግሮታል(ቁ. 23):: በየደረሰበት ሁሉ ክርስቲያኖች ወደ ኢየሩሳሌም እንዳይሄድ በመደጋገም ይነግሩት ነበር (ሐዋ. 21: 4 10-14):: ሐዋርያው ጳውሎስ ግን ስደትንም ሆነ ሞትን የሚፈራ ሰው አልነበረም። ለክርስቶስ ወንጌል ሕይወቱን እንኳን ለመስጠት ፈቃደኛ ነበር (ሐዋ.21: 13 ፊል. 2:17 ቆላ 1:24 )። ጳውሎስ በሕይወቱ አንድ ግብ ብቻ ነበረው። እርሱም "ጌታ ኢየሱስ የሰጠውን ሥራ መፈጸምና "መልካሙን ገድል ተጋድያለሁ ሩጫውን ጨርሻለሁ" ለማለት መቻል ነበር ( 2 ጢሞ 4: 7-8)። ጳውሎስ ለሕይወቱም ሆነ ለሞት ደንታ አልነበረውም ነገር የእርሱ ዋናው ዓላማ ምን እንደሆነ ሲናገር አሁን በሕይወት ብኖር ወይም ብሞት በሁለንተናዬ ክርስቶስ እንዲከብር ለማድረግ ሙሉ ድፍረት አለኝ (ፊል. 1:20)።

**የሐዋ. ሥራ 20፡25**

ይህ ቁጥር እንደሚነግረን ሐዋርያው ምንም እንኳን ከኤፌሶን የተነሳው በሰላም ቢሆንም ወደ ኤፌሶንና እስያ አውራጃ የመመለስ እቅድ አልነበረውም። የእርሱ አሳብ ከኢየሩሳሌም ወደ ሮም ከዚያም ደግሞ ወደ እስፔን ለመሄድ ነበር (ሐዋ. 19:21 ሮሜ 15:23-24 28 )። ስለዚህም በኢየሩሳሌም የሚጠብቀው ምንም ይሁን ምን ከእንግዲህ ወዲህ ከኤፌሶን ክርስቲያኖች ጋር ዳግመኛ መተያየት እንደማይችሉ በእርግጠኝነት ከጌታ ተረድቶ ነበር።

**ሐዋ. ሥራ 21፡26-27**

ጳውሎስ እንደ ታመነ አገልጋይ በኤፌሶን በነበረበት ጊዜ የእግዚአብሔርን አሳብ ሁሉ ለኤፌሶን ሰዎች አንድም ሳያስቀር ነግሯቸዋል፡፡ የሚቀረው ነገር ከእርሱ በተማሩትና በተረዱት እውነት እስከ መጨረሻው ድረስ በታማኝነትና በታዛዥነት ለጌታ መኖር ብቻ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ከእርሱ የተቀበሉትና የተማሩትን ቸል በማለት የእግዚአብሔርን ፍርድ በራሳቸው ላይ እንዲመጣ ካደረጉ ጳውሎስ ምንም ኃላፊነት አይኖርበትም (ቁ. 27)፡፡ ለሚደርስባቸው ዘላለማዊ ፍርድ ከማንም ሰው ደም ጳውሎስ ንጹህ እንደ ሆነ አስታውቋቸዋል።

**ቁ .28** እንግዲህ ለራሳችሁና ለመንጋው ተጠንቀቁ ማለቱ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በመጀመሪያ ደረጃ ለራሳቸው ጥንቃቄ ማድረግ አለባቸው፡፡ ምክንያቱም ሰይጣን ከሌሎች ይልቅ መሪዎችን ማጥቃት ነው የሚፈልገው። አንድ መሪ በሰይጣን ወጥመድ ውስጥ ከወደቀ፤ በመንጋው ማለትም በአማኞች ላይ ታላቅ ችግር ይደርሳል (ቁ. 30)። የቤተ ክርስቲያን መሪዎች

የመንጋው እረኞች እንዲሆኑ በመንፈስ ቅዱስ ተመርጠዋል። በመሆኑም ያለማቋረጥ በመንፈስ ቅዱስ እየተሞሉ መኖር አለባቸው። ጳውሎስ እጁን በጫነባቸው ጊዜ እንዴት መንፈስ ቅዱስን እንደተቀበሉ እነዚህ የኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች የሚዘነጉት አይደለም ( የሐዋ. 19:1-5)። በአዲስ ኪዳን ውስጥ የበላይ ጠባቂ (1 ጢሞ 3:1 ) እና ሽማግሌዎች የሚሉት ቃላት ጥቂት ልዩነት ብቻ ነው ያላቸው፡፡ አዲስ ኪዳን በተጻፈበት ዘመን የበላይ ጠባቂዎችና ሽማግሌዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በመሰረታዊ ነገሮች ያላቸው ደረጃ አንድ ዓይነት ነው። እረኞች በመባልም ተሰይመዋል። በአዲስ ኪዳን እነዚህ ቃላት በተወራራሽነት ወይንም ተለዋዋጭነት ጥቅም ላይ ውለዋል (ኤፌ4:11)።

**የሐዋ. *ሥራ* 20፡29**

ሐሰተኛ መምህራንና ሐሰተኛ መሪዎች እንደ ተኩላ ናቸው (ማቴ 7: 15፣1 ጢሞ 4:1-2 2 ጴጥ2፡ 1-3 1 ዮሐ 2: 18-19)።ከጥቂት ጊዜ በኋላ ደግሞ ሐዋርያው ጳውሎስ.. “በእስያ ያሉት ሁሉ እንደከዱን ታውቃለህ” በማለት ለጢሞቴዎስ ጽፎለታል (2 ጢሞ 1:15)። ይህም የኤፌሶን ክርስቲያኖችን ይጨምራል። በመጨረሻም በራዕይ መጽሐፍ ሐዋርያው ዮሐንስ ከራሱ ከኢየሱስ ክርስቶስ የተቀበለውን መልእክት ለኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን ሲጽፍ “ነገር ግን አንድ የምነቅፍብህ ነገር አለኝ ፤ ይኸውም የቀድሞውን ፍቅርህን ትተሃል ከመውደቅህ በፊት የት እንደነበርክ አስታውስ ንስሓ ግባ፤ በመጀመሪያ ታደርገው የነበረውን ሥራህን አድርግ፤ ይህን ሁሉ ባታደርግ ግን ወደ አንተ እመጣለሁ፤ ንስሓም ክልገባህ መቅረዝህን ከስፍራው አነሣዋለሁ ብሏል” (ራዕ 2: 4-5)።

**የሐዋ. *ሥራ* 20፡30-31**

በእነዚህ ቁጥሮች ሐሰተኛ ነቢያትና ሐሰተኛ መምህራን ከቤተ ክርስቲያን መሪዎች መካከል እንኳን ሊነሱ እንደ ሚችሉ ያስገነዝባል (1 ጢሞ 1: 19-20 2 ጢሞ 2: 16-18 3 የሐ 9-10)፡፡ በዚህም ምክንያት ያስጠነቅቃቸዋል ( 1 ቆሮ 16: 13 1 ጴጥ 5:8)፡፡ እዚህ ላይ ጳውሎስ ሦስት ዓመት ሌሊትና ቀን እንባውን እያፈሰሰ እንደ መከራቸው በማስታውስ ለህይወታቸውና ለመንጋው እንዲጠነቀቁ ያሳስባቸዋል። እዚያ ያገለገለው ለሁለት ዓመት ከሦስት ወር ነው፤ ማለትም ከ52 ዓ.ም ማለቂያ አንስቶ እስከ 55 ዓ.ም መጀመሪያ ድረስ በኤፌሶን ነበር ይህንንም ጳውሎስ በማጠጋታት ይመስላል ሦስት ዓመት ያለው።

**የሐዋ. *ሥራ* 20፡32-35**

ሐዋርያው ጳውሎስ የኤፌሶንን ቤተ ክርስቲያን ለእግዚአብሔርና ለጸጋው ቃል አደራ እንደ ሰጣቸው እናያለን። ከዚህ በኋላ እርሱ ተለይቷቸው የሚሄድ ቢሆንም ከእነርሱ የማይለየው ከእርሱ የተማሩት የጸጋው ቃል እንደሆነ አጽንኦት ሰጥቷል ( ዮሐ 15:7)። ይህ ከእርሱ የተማሩት የጸጋው ቃል ክርስቶስን በማመን የጀመሩትን የድነት ሂደትና ጉዞ ሊያስቀጥላቸውና ሊያስጨርሳቸው የሚችል መሆኑን ያሳያል። ለኤፌሶን አማኞች የእርሱን ፈለግ እንዲከተሉ ጳውሎስ የህይወት ምሳሌነቱን በድጋሚ ያቀርብላቸዋል፡፡ ኑሮውን ለመደጎምና አብረውት ያሉትንም ይረዳ ዘንድ በገዛ እጁ እየሰራ እንደ ነበር ግልጽ አድርጎ አቅርቧል። እነርሱም በተመሳሳይ እንደዚያው በማድረግ የጌታን ለሌሎች የመስጠት ትምህርቱንና ትእዛዙን ልብ እንዲሉት ያበረታታቸዋል።

**የሐዋ. *ሥራ* 20፡36-38**

በመጨረሻም ሐዋርያው ጳውሎስ ከባዱ የመለያየትና የመሰነባበት ሰዓት ሲደርስ ለሦስት ዓመት በየቤታቸው እየዞረ ሲያገለግላቸው ከነበሩት የኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ጋር ተንበርክኮ ጸለየ። እነርሱም በሚሆነው ሁኔታ ልባቸው

ስለተነካ እንባቸውን መቆጣጠር አቅቷቸው አንገቱን በማቀፍ ያለቅሱና ይስሙት እንደ ነበር ክፍሉ ይነግረናል።ይሁን እንጂ ለመንፈስ ቅዱስ ምሪት በመታዘዝ ወደ ኢየሩሳሌም ለመሄድ ዝግጁ ነበር። እንዲሁም ከአረማውያን አብያተ ክርስቲያናት የተሰበሰበውንም ስጦታ ለኢየሩሳሌም ቤተክርስቲያን ማድረስ ነበረበት።

***የመወያያ ጥያቄዎች፡-***

1. በሐዋ. *ሥራ* 20፡1-6 *መሠረት* ጳውሎስ ኤፌሶንን ለቆ ከመሄዱ በፊት ያደረገውና የገጠመው ችግር ምንድን ነበር?
2. ከቁ. 7-12 በጢሮአዳ በነበረው የምሽት ፕሮግራም ላይ ስለ ተፈጠረው ነገር በዝርዝር ተነጋገሩ።
3. በሐዋ. *ሥራ* 20፡13-16 *መሠረት* ከጢሮአዳ እስከ ሚሊጢኒ የተደረገውን ጉዞ በዝርዝር ተወያ።
4. ከቁ. 17-21 በማንበብ ስለ ጳውሎስ ህይወትና አገልግሎት የተረዳችሁት አካፍሉ።
5. በሐዋ. *ሥራ* 20፡22-24 ሐዋርያው ጳውሎስ ወደ ኢየሩሳሌም ለመሄድ የጸና ውሳኔ ያደረገው ከምን የተነሳ ነው? ተወያዩ።
6. ከቁ. 25-30 በዚህ ክፍል ሐዋርያው ጳውሎስ በተጨማሪ ያቀረበው ምክርና ማስጠንቀቂያ በዝርዝር ተነጋገሩበት።
7. የሐዋ. *ሥራ* 20፡32-38 በማንበብ የሐዋርያው ጳውሎስ የመጨረሻው አደራውን ከምን ጋር አያይዞ ነው ያቀረበው?
8. ሐዋርያው ጳውሎስ ለወንጌል እስከሞት ድረስ ዋጋ መክፈልን ያልፈራው ለምንድ ነው? ምን እንማራለን?
9. ከዛሬው የጥናት ክፍል ስለ አገልጋይ ህይወትና አግልግሎት የቀረላችሁን ምንድን ነው? አካፍሉ።

***መ ደ ም ደ ሚ ያ***

አገልግሎታችንን በታማኝነት እንዳንፈጽም የሚገጥሙን ፈተናዎችና ተግዳሮቶች ቀላል አይደሉም። ይሁን እንጂ በፈተናዎችና በተግዳሮቶች መካከል በጽናት አልፈው ሩጫቸውን የፈጸሙት ሐዋርያው ጳውሎስን ጨምሮ በብሉይም ይሁን በአዲስ ኪዳን ብዙ ምስክሮች በዙሪያችንም ስላሉ (ዕብ 11)። ዓይነቱና ደረጃው የቱም ይሁን ከጌታ የተቀበልነውን የአገልግሎት አደራ ጠንቅቀን መጨረስ ይኖርብናል።

# ጥናት አሥራ አምስት

## ርዕስ፦ ሶስተኛ የወንጌል ጉዞ ማጠቃለያ

## (ጉዞ ወደ ኢየሩሳሌምና ስደት)

**የንባብ ክፍል፦** የሐዋ. ሥራ 21: 1-40

**ዓላማ፦**

ስደት የሚመጣ ቢሆንም አንድ አገልጋይ ከጌታ ወደ ተቀበለው ግብ በጽናት መገስገስ እንዳለበት ለማሳሰብ ነው።

***መግቢያ፦***

አንድ አገልጋይ ከጌታ የተቀበለውን አደራ ጥሩ አጨራረስ እንደሚያስፈልገው በኤፌሶን ከነበረው የሐዋርያው ጳውሎስ ህይወትና አገልግሎት በዝርዝር ተመልክተናል። አጨራረሳችንን ለማበላሸት ድካማችንን ፍሬ ቢስ ለማድረግ የሚገጥሙን ተግዳሮቶች ብዙ ናቸው። የምንሄድበትን ግብ ማወቅ ግባችንን እንድንጨርስ ይረዳናል። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የአገልግሎቱን ግብ ያውቅ ስለነበረ የተለያዩ የሰዎችና የሰይጣን ግብዣዎች አላታለለውም። በዚህ ክፍል የሐዋርያው ጉዞ **ከሚሊጢኒ ወደ ጢሮስ** በቂሳርያ በኩል **ወደ ኢየሩሳሌም፣እንዲሁም በጉዞው ስላጋጠመው ነገር፣ ኢየሩሳሌም መድረሱንና በኢየሩሳሌም ስለ ገጠመው ስደት ተጽፏል።**በእነዚህ ጉዞዎች ላይ በመነሳት በዛሬ የጥናት ጊዜያችን ከሐዋርያው ጳውሎስ በብዙ ተግዳሮት አልፎ ወደ ግብ እንዴት እንደደረሰ የምንመለከት ይሆናል።

**የክፍሉ አጭር ማብራሪያ፦ የሐዋ. ሥራ 21:1-40**

**ቁ. 1-6 ከሚሊጢኒ ወደ ጢሮስ**

ጳውሎስና ጓደኞቹ የሜዲትራንያንን ባሕር ምሥራቃዊ ክፍል አቋርጠው፡በዚያ ዘመን ሮማውያን በሶርያ ውስጥ የነበራቸው ግዛት አካል ወደ ነበረችው ፊንቄ (የአሁን ዘመን ሊባኖስ) ሄዱ። የቆጵሮስን ባሕር ዳርቻ ተሻግረውም በፊንቄ ውስጥ ታላቅ ከተማ ወደ ነበረችው ጢሮስ ደረሱ። በጢሮስ ቤተ ክርስቲያን ነበረች። ስለዚህም መርከቡ ጭነቱን እስኪያራግፍ ድረስ ጳውሎስና ጓደኞቹ እዚያ ከነበሩት ደቀ መዛሙርት ዘንድ ተቀመጡ። ከእነዚህም ደቀ መዛሙርት አንዳንዶቹ በኢየሩሳሌም ጳውሎስን ስለሚገጥመው ችግር በመንፈስ ቅዱስ ተረድተዋል። ስለዚህም ወደዚያ እንዳይሄድ ለመምከር ሞክረዋል። ይሁን እንጂ ጳውሎስ ወደ ኢየሩሳሌም ለመሄድ ምሪትን ከመንፈስ ቅዱስ አግኝቶ ስለነበረ ይህንን ምክራቸውን ወይንም ልመናቸውን ተቀብሎ ጉዞውን እንደማያቋርጥ በግልጽ ነገራቸው። መርከቡ ጭነቱን ማራገፉን ካበቃ በኋላ ጳውሎስና ጓደኞቹ በጢሮስ ከነበሩት ደቀ መዛሙርት ጋር ተሰነባብተው በመርከብ ወደ ጴጤሌምስ ደረሱ።

**ከቁ. 7-16 ጳውሎስ በቂሳርያ**

ጳውሎስን አሳፍራው የነበረችው መርከብ ከእስራኤል በስተሰሜናዊ ምስራቅ ወደ ነበረችው ወደ ቂሳርያ ሄደች። ጳውሎስና አብረውት ሲጓዙ የነበሩትን ጓደኞቹ ያረፉት በፊልጶስ ቤት ነበረ። ፊልጶስ ከመጀመሪያዎቹ የኢየሩሳሌም ሰባት ዲያቆናት አንዱ ነበር። አራቱም ልጆቹ በትንቢት መናገር ስጦታቸው በቤተ ክርስቲያን የሚያገለግሉ ነበር። እንዲሁም አጋቦስ የተባለው ነብይ ከኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን ወደ ቂሳርያ በመምጣት ከነ ጳውሎስ ጋር እንደተገናኘ እንመለከታለን። አጋቦስም የኢየሩሳሌም አይሁድ ጳውሎስን እንደሚይዙትና ለአረማዊያን (ሮማውያን) አሳልፈው እንደሚሰጡት ትንቢት ተናገረ። ይሁን እንጂ አጋቦስ ወደ ኢየሩሳሌም እንዳይሄድ ጳውሎስን አልተጫነውም። እዚያ ሲደርስ ምን እንደሚገጥመው መንፈስ ቅዱስ ያመለከተውን ብቻ ነበር የተናገረው። የጳውሎስ ጓደኞች ግን የእግዚአብሔር ፈቃድ ምን እንደ ነበረ አልተረዱም። ስለዚህ

እነሱም ተጨምረው ወደ ኢየሩሳሌም እንዳይሄድ ይለምኑት ነበር። ጳውሎስም በቁርጠኝነት ወደ ኢየሩሳሌም ከመሄድ አንዳችም ነገር እንደማያግደው አስረድቷቸዋል።

**የሐዋ. *ሥራ* 21፡17-26 የጳውሎስ ኢየሩሳሌም መድረስ**

በኢየሩሳሌም የነበሩ ወንድሞች ጳውሎስን በደስታ በታጀበ የሞቀ አቀባበል አድርገውለታል። እርሱን ከአረማውያን አብያተ ክርስቲያናት ተወካዮች ጋር በመሆን የተሰበሰበውን ስጦታና ጌታም በአገልግሎት የፈጸማቸውን ብዙ አረማውያን ወደ ጌታ እንደመጡና በእስያና በግሪክ ስለተመሰረቱት አያሌ አብያተ ክርስቲያናት ያዕቆብን ጨምሮ ለኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ሪፖርቱን አቅርቧል። ያዕቆብና አብረውት የሚያገለግሉትም ስለ ሁሉም ነገር እግዚአብሔርን ካመሰገኑ በኋላ፤ በእነርሱ በኩል ደግሞ አይሁዳዊያን በሐዋርያው ጳውሎስ አግልግሎት ላይ ያለውን ግልጽ ቅሬታና ሊነሳ ስለሚችል ስደት አስረድተውታል። ስለዚህ በአይሁዳዊያን አማኞች መካከል ስለ ተፈጠረውም ቅሬታ የመፍትሄ ሃሳብ ነው ብለው ያሰቡትን ምክር አቅርበዋል። በዚህም መሰረት ጳውሎስ አይሁዳዊያን አማኞችን ለማስደሰት ሲል የሙሴን ህግ የሚቃወም አለመሆኑን ራሱ የመንጻት ሥርዓት በመፈጸም እንዲያረጋግጥላቸው ወደ ቤተ መቅደስ አራት ሰዎችን ጨምሮ ይዞ በመግባት ሙከራ አድርጓል።

**21፡27-36 ጳውሎስ በኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስና ስደት**

የጴንጠቆስጤ ቀን ለማክበር አንዳንድ አይሁዳዊያን ከኤፌሶንና ከእስያ ከተሞች ወደ ኢየሩሳሌም መጥተው ነበር። ጳውሎስ በአይሁድ አማኞች ዘንድ የተፈጠረውን ቅሬታ ለማርገብ በማሰብ ከኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን መሪዎች የተሰጠውን አሳብ ተቀብሎ በቤተ መቅደስ የመንጻት ሥርዓት ሲፈጽም ሲያዩት የሙሴን ሕግ እንዳይጠብቁ ያመኑትን አይሁዳዊያንን ማስተማሩ ሳያንስ አሁን ደግሞ አረማውን ይዞ ወደ ቤተ መቅደስ ውስጥ ይዞ እንደገባ በማሰብ በመጡት አይሁዳዊያን አንድ ታላቅ ቁጣ አስነሳባቸው። እነርሱም በዚያ የሚገኙትን ሌሎች አይሁዳዊያንን በማስተባበር የኢየሩሳሌምን ከተማ በሁከትና በብጥብጥ እንዳወኩት ይናገራል። ጳውሎስንም ጎትተው ሊገድሉት ሳሉ ከቤተ መቅዱስ በቅርብ ርቀት ላይ ከነበረው የሮማዊያን የጦር ሰፈር ወታደሮች ደርሰው ከእጃቸው አድነውታል። ከዚያም ሁከት አልበርድ ሲል የጦር አዛዡ በመምጣት ችግሩን ለመፍታት ቢሞክርም ከአቅሙ በላይ ስለሆነ ጳውሎስን ይዞ ወደ እስር ቤት ይዘውት እንዲሄዱና ከግርፋት ጋር ምርመራ እንዲደረግበት ለወታደሮቹ ትዕዛዝ ሰጥቷል።

**ሐዋ. *ሥራ* 21፡37-40 የጳውሎስ የመከላከያ ንግግር**

ጳውሎስም በመንገድ ሳሉ ለጦር አዛዡን ስለማንነቱ ለሕዝቡ መናገር እንዲችል ዕድል እንዲሰጠው ጠየቀ። አዛዡም በጠርሴስ ከተማ የተወለደ አይሁዳዊ እንደሆነ ስለተረዳ ስለ ቀረበበት ክስ ለህዝቡ የራሱን መከላከያ እንዲያቀርብ ፈቃድ ሰጥቶታል። አዛዡም መከላከያውን እንዲያቀርብ ፈቅዶለት ህዝቡን ሁሉ ሰብስቦ በዕብራይስጠኛ ቋንቋ ንግግር ጀመረ።ይህ ምዕራፍ በዚህ ይዘጋል።

**የመወያያ ጥያቄዎች**

1. የሐዋ. *ሥራ* 21፡1-6 ከሚሊጢኒ ወደ ጢሮስ በተደረገው ጉዞ ስለ ተከናወኑ ነገሮች በዝርዝር ተነጋገሩ?
2. ከቁ. 7-11 ቂሳርያ ከደረሱ በኋላ እነማንን እንዳገኙና ምን ምን እንደተከናወነም ጭምር በዝርዝር ተውያዩ?
3. የሐዋ. *ሥራ* 21፡12-16 ወደ ኢየሩሳሌም በሚደረገው ጉዞ የጳውሎስ፤ የጓደኞቹና የነብዩ አጋቦስ አቋም ምንድን ነበር? ተወያዩ።
4. ከቁ. 17-19 ጳውሎስ ለኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ያቀረበው ሪፖርት ይዘቱ ምንድን ነበር?

5. የሐዋ. ሥራ 21፡20-22 የኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን መሪዎችስ ጳውሎስን በተመለከተ ይወራ ስለነበረው ቅሬታ ምን እንደነገሩት ለቡድናችሁ አካፍሉ።
6. ከቁ. 23-26 የቤተ ክርስቲያን መሪዎች መፍትሄ ነው ብለው ያቀረቡት አሳብ ምንድን ነበረ?
7. የሐዋ. ሥራ 21፡27-36 ጳውሎስን ችግር ለማስወገድ አስቦ ወደ ቤተ መቅደስ ሲገባ የገጠመውን ነገር በዝርዝር ተወያዩ።
8. ከዛሬው የንባብ ክፍል ሌላ የተገነዘባችሁትን ነገሮች ካሉ አካፍሉ።
9. ከዛሬው ጥናት በአግልግሎት ሊገጥሙ ስለሚችሉ ነገሮችና ስለጽናት የተረዳችሁትን አካፍሉ።

***መ ደ ም ደ ሚ ያ***

በዛሬው ጥናት እንደተመለከትነው ሐዋርያው ጳውሎስ፣ ከጌታ ወደ ተቀበለው የአገልግሎት አደራ የቱም ዓይነት ፈተና በፊቱ ቢቆምም ነፍሱን በእርሱ ዘንድ እንደ ማትከበር በማሰብ ግስጋሴው ወደ አገልግሎቱ ግብ ሲያደርግ አይተናል። እኛም ጌታ በረዳን መጠን በመንገዳችን ላይ በሚገጥሙን ተግዳሮቶች ሳንፈታ በጽናት ወደ ግባችን ልንገሰግስ ያስፈልገናል።

## ጥናት አስራ ስድስት

**ርዕስ፦** የኢየሩሳሌም ስደትና የሐዋርያው መልስ

(ድል በመንሳት የሚያዞረን ጌታ ነው)

**የንባብ ክፍል የሐዋ.** 22: 1-30

***ዓላማ፡-***

አገልጋይ በተሳሳተ ግንዛቤ ያልተገባ ክስ ሲደርስበት ምን ማድረግ እንዳለበት ለማሳሰብ ነው።

***መግቢያ፡-***

ከዚህ በቀደሙ ጥናቶች የሐዋርያው ጳውሎስ አገልግሎት በብዙ ተአምራት ታጅቦ የጌታ ሥራ እየሰፋና አብያተ ክርስቲያናትም እየታነጹ እንደነበር ተመልክተናል። ይህንን አገልግሎቱን ለመግታት ሰይጣን "የኤፌሶንን አርጤምስ ክብር" ነክቷል የሚል ክስ አቅርቦበታል። የዚህ ክስ ጭብጥም ያነጣጠረው በጳውሎስ በራሱ ላይ በመሆኑ፤ የኤፌሶንን ከተማ ለቆ ለመውጣት የግድ ብሏል (ሐዋ. 19: 24-28)። ይህ ምዕራፍ ከሶስቱ ከሐዋርያው ጳውሎስ የሕይወት ታሪክ ምስክርነት ስብከቶች አንዱ ነው ሌሎቹ ያሉት በሐዋ. ሥራ 9 እና 22። በዛሬ የጥናት ክፍላችን ደግሞ የምንመለከተው ሌላ ክስ ሲሆን የዚህኛውን ክስ ጭብጥ ስንመረምር ያነጣጠረው በራሱ በጳውሎስ ላይ ሳይሆን በጳውሎስ መልዕክት ላይ መሆኑን አብረን የምንመለከተው ይሆናል።

**የክፍሉ አጭር ማብራሪያ፦ 22:1-30**

**ከቁ. 1-5 ጳውሎስ ለህዝቡ ያደረገው ንግግር**

አይሁድ ይጠብቁ የነበረው ጳውሎስ በግሪክ ቋንቋ ብቻ እንደሚናገር ነበር ነገር ግን በተቃራኒው ጳውሎስ ንግግሩ በዕብራይስጥ ቋንቋ መናገር ሲጀመር ወዲያውኑ ጸጥ ብለው በእርጋታ ማዳመጥ ጀመሩ። በመጀመሪያ እርሱም እንደ እነርሱ ጥርት ያለ አይሁዳዊ መሆኑን፣ በኢየሩሳሌም ከተማ ማደጉን፣አይሁድ አለን ከሚሏቸው ታላላቅ መምህራን አንዱ በሆነው በገማልያል እግር ስር የተማረ እንደሆነ አሳወቀ። በተጨማሪም የቤተ መቅደስም ሆነ የአይሁድ ሕግ ጠላት አለመሆኑን እንዲያውቁለት በአጽንዖት አስረድቷል። እንዲሁም ክርስቲያኖችን በማሳደድ፣እነርሱን በመያዝና ወህኒ እንዲገቡ በማድረግ የተጫወተውን ሚና ጨምሮ በማብራራት ገልጿል።

**ሐዋ. *ሥራ* 22፡6-16 የጳውሎስ ህይወት መለወጥ**

የክርስትናን መንገድ እየተቃወመ ባለበት ሁኔታ ለዚህ ተልዕኮ በደማስቆ ጎዳና ላይ ሳለ ድንገት ጌታ እንዴት እንደተገለጠለት ጨምሮ በሰፊው አስረድቷል። ጌታም በደማስቆ በሚኖሩ አይሁዶች ዘንድ የተመሰገነ ሐናንያ ወደ ሚባለው ደቀ መዝሙር ላከው።አገልጋዮችን ለማሳደግ ሌሎች አገልጋዮችን እየተጠቀመ እንዳለ እዚህ እናያለን።።

ሐናንያም እንደ ጸለየለትና ዓይኖቹ እንደተከፈቱ ከዚያም በውሃ እንደተጠመቀ አብራርቷል። ወዲያውም ወደ ኢየሩሳሌም ተመልሶ በቤተ መቅደስ በሚጸልይበት ጊዜ፤ በተመስጦ ራእይ እንዳየና በራእዩም ከኢየሩሳሌም በፍጥነት እንዲወጣና በሩቅ ወዳሉ ወደ አህዛብ በመሄድ ምስክሩ እንድሆንለት ጌታ እንደላከው ያስረዳል።

**ሐዋ. *ሥራ* 22፡22-29 ጳውሎስ የሮም ዜጋ መሆኑን መግለጡ**

እስከዚህ ድረስ ህዝቡ ሁሉ በጸጥታ የጳውሎስን ንግግር ያዳምጡ ነበር።ነግር ግን ከሰሙት በኋላ ወዲያውኑ በታላቅ ጩኸትና ቁጣ እንዲህ ዓይነቱ ሰው በህይወት መኖር አይገባውም በማለት ታለቅ ሁከት ተፈጠረ። አዛዡም ህዝቡ ማረጋጋት

ስላልተቻለው ወታደሮቹን ወደ ጦር ሰፈር እንዲያስገቡትና እየተገረፈ ምርመራ እንዲደረግበት ትዕዛዝ ሰጣቸው። ወታደሮቹም በጠፍር ወጥረው በማሰር ሊገርፉት ሲዘጋጁ፤ አጠገቡ የቆመውን የመቶ አለቃ የሮም ዜግነት ያለውን ሰው "ያለ ፍርድ መግረፍ ተፈቅዶላችኋል ወይ? ብሎ ይጠይቃል። መቶ አለቃውም ወደ አዛዡ በመሄድ የሮም ዜግነት ያለው እንደሆነ ሲነግረው፤ አዛዡም ወደ ጳውሎስ በመቅረብ እውነታውን ከጳውሎስ ተረድቶ ውሳኔውን ቀልብሷል።

**ሐዋ. ሥራ 22፡30 ጳውሎስ በአይሁድ ሸንጎ ፊት መቅረቡ**

በማግስቱ አዛዡ ጳውሎስን የከሰሱበትን ምክንያት ምን እንደሆነ እንዲያስረዱ የካህናት አለቆችና የሸንጎው አባሎች በሙሉ እንዲሰበሰቡ አዘዘ። ጳውሎስንም ከእስራቱ ፈትቶ ወሰዶ በፊታቸው አቀረበው።

**የመወያያ ጥያቄዎች**

1. ሐዋ. ሥራ 22፡1-2 ጳውሎስ በዕብራይጥ ቋንቋ መናገሩ በአድማጮቹ ላይ የፈጠረው ነገር ምንድን ነው?
2. ከቁ. 3-5 ጳውሎስ ስለ ራሱ ለአድማጮቹ ያቀረባቸውን ነጥቦች በዘርዝሩ ተወያዩ?
3. ከቁ. 3-5 ጳውሎስ በእነዚህ ነጥቦች ሊያገኝ የፈለገው ውጤት ምንድን ነው ትላላችሁ?
4. ሐዋ. ሥራ 22፡6-11 መሠረት የሐዋርያ ጳውሎስን የህይወት መለወጥ በማየት ስለ ድነት የተረዳችሁትን አካፍሉ።
5. ከቁ. 12-16 ያለው ሀሳብ ከሐዋ. 9:10-18 ጋር የሚለይበት ነገሮችን ተነጋገሩ?
6. ሐዋ. ሥራ 22፡12-16 የሐዋርያው ጳውሎስ የህይወት ምስክርነት ትኩረቱ በምን ጉዳይ ላይ ነው? ለምን?
7. ሐዋ. ሥራ 22፡17-21 የጳውሎስ ንግግር እንዳይሰሙ ያደረጋቸው ምንድን ነው?
8. የሐዋ.ሥራ 22፡22-30 የሐዋርያው ምስክርነት በህዝቡ መካከል የፈጠረውን ነገር ከሉቃ 23:1-5 በክርስቶስ ላይ ከቀረበው ክስ በማነጻጸር ተወያዩ።
9. የሕይወት ታሪክ ስብከት ወይም ምስክርነት ጥቅሙ ምንድ ነው?
10. ከዛሬ ጥናት በተለየ መንገድ የቀረላችሁን ለቡድን አባላችሁ አካፍሉ።

**መ ደ ም ደ ሚ ያ**

ከዚህ ቀደም ሰይጣን የጳውሎስን አገልግሎት ለማስቆም ክስ አቅርቦበት እንደነበር አይዘነጋም። በዚህም በተወሰነም ምክንያት የኤፌሶንን ከተማ ለቅቆ ወጥቷል። ይሁን እንጂ እግዚአብሔር ጳውሎስ በሄደበት ስፍራ ሁሉ የአገልግሎት በር ስለከፈተለት ሰይጣን ከግስጋሴው ሊገታው አልቻለውም። በዛሬው ጥናታችንም እንደተመለከትነው ሰይጣን የጳውሎስን ግሥጋሴ ማስቆም ስላልተቻለው የጳውሎስ መልዕክት ተቀባይነት ለማሳጣት ከፍተኛ ሙከራ አድርጓል። ይሁን እንጂ በዚህ ሁሉ ነውጥና መከራ ውስጥ እግዚአብሔር ባሪያውን በብዙ ጸጋ ደግፎና ተሸክሞ በየስፍራው ድል በመንሳት አዙሮታል።

**ጥናት አስራ ሰባት**

**ርዕስ**፡ ንጹሕ፡ህሊናና የእግዚአብሔር ጥበቃ

**የንባብ ክፍል፡-** የሐዋ. ሥራ ምዕ. 23:1-35

***ዓላማ፡-***

በመልካም ህሊና ስናገለግል እግዚአብሔር ከሚያሴሩብን ጠላቶቻችን እንዴት እንደሚያድን ለማሳየት፡-

***መግቢያ፡-***

ባለፈው ምዕራፍ ሐዋርያው ጳውሎስ በሮማዊው የጦር አዛዥ ከታሰረበት ተፈትቶ በሰበሰባቸው የአይሁድ ሸንጎ ፊት እንደቀረበ ተመልክተን ነበር ትረካውን ያቆምነው። ጳውሎስ "ወንድሞች" እያለ በሚጠራቸውና በሚያከብራቸው አይሁዳዊያን መካከል ሥርዓትን ከመጠበቅ አኳያ የነበረበትን ኃላፊነት ሙሉ በሙሉ በእግዚአብሔር ፊት እንደተወጣ ይናገር ነበር፡፡ ይህንን የአኗኗር ዘይቤ በፊል.1:27 "ብቻ ለክርስቶስ ወንጌል እንደሚገባ ኑሩ..." በማለትም ለፊልጵስዩስ ወገኖች መምከሩ እንዴት ወንጌልን ያለነቀፋ ለመስበክ ሁልጊዜ የነቃ እንደነበር ያመላክተናል።

በተጨማሪም ለቆሮንቶስ ሰዎችም በ1ቆሮ.1:12 በቅድስናና በቅንነት ለመኖሩ እንዴት ኅሊናው ይመሰክርለት እንደነበር ገልጿል። ሆኖም አንዳንድ ጊዜ እውነቱን መናገራችን ከመከራና ስደት ለመዳን ዋስትና አይሆነንም። ከመለወጡ በፊት እንኳን ሕግን ከመጠበቅ አኳያ ያለነቀፋ እንደነበር ይናገራል (ፊል. 3:6)። እነዚህንና ሌሎች ነገሮችን ከዚህ ምዕራፍ እናያለን።

**የክፍሉ ማብራሪያ**

**የሐዋ. ሥራ 23:1-5**

ጳውሎስ ንጹህ ህሊና እንዳለው ቢገልጽም በሊቀ ካህኑ ትዕዛዝ አፉ ተመታ እውነተኛና ታማኝ የአይሁድ ዜጋ መሆኑን መናገሩ ነው። ለዚህ ተግባርም ተቆጥቶ ሊቀ ካህኑን ሐናንያ በመሳደቡ ባጠገቡ የነበሩት ሰዎች "ሊቀ ካህንን እንዴት ትሳደባለህ?" ሲሉት ባለማወቁ እንደሆነ ይቅርታ ሲጠይቅ እናያለን። ሐዋርያው ጳውሎስ የማየት ችግር ስለነበረው ሊቀ ካህኑን አጥርቶ ባለማየቱ ይሆናል የሚሉ ያሉ ሲሆን ሌሎች ደግሞ የሊቀ ካህኑን ሥልጣን እያፌዘ ወይም እያላገጠም ይሆናል ይላሉ። ይህም ማለት ሊቀ ካህኑ ኃላፊነቱን በትክክል እንዳልተወጣ ለማሳየት ነው ማለታቸው ነው።

**የሐዋ. ሥራ 23:6-11 - ሐዋርያው ጳውሎስ የተገኘው እድል ሁሉ ተጠቅሞ ወንጌልን ሰበከ**

በዚህ ክፍል ሐዋርያው በፈሪሳውያንና በሊቀ ካህናቱ ተደማጭነት እንዲያገኝ የትምህርቱ የሚያውቀውን የእውቀት ቃል ሲጠቀም እንመለከታለን። እንዲህ ይላል "ስለ ተስፋና ስለሙታን ትንሳኤ" በማለት ጳውሎስ በሰዱቃውያንና በፈሪሳውያን መካከል ያለውን የስነ መለኮት ትምህርት ልዩነት አንስቶ ጉባኤው በሁለቱ ሃሳቦች ላይ እንዲከፈል አደረገው። እነዚህ የአይሁድ ሁለት የሃይማኖት ጽንፈኞች በመሃከላቸው ልዩነት ነበር። በመሆኑም ጳውሎስ ይህንን ልዩነታቸውን የተጠቀመበት ብልሃት ነው። በ23፡8-9 መሠረት ሰዱቃውያን የሙታን ትንሣኤን፥መላዕክትን፣ መናፍስትንም የሉም የሚሉ ሲሆኑ፣ ፈሪሳውያን ግን በእነዚህ ሁሉ መኖር የሚያምኑ ነበሩ። ሳዱቃውያን ሕግን የሚጠቀሙት ለማበራዊና ለፓለቲካ

አስተዳዳር ነው። መንፈሳዊነትን ታውረው ነበር። በመከፋፈላቸው ምክንያት ታላቅ ሁከትም ሆነ።ከፈሪሳውያን ወገን የሆኑ አንዳንድ የኦሪት ሕግ መምህራንም ተነሥተው፣ “በዚህ ሰው ላይ ምንም ጥፋት አላገኘንበትም፤ መንፈስ ወይም መልአክ ተናግሮትስ እንደ ሆነ ምን ይታወቃል?” በማለት አጥብቀው ተከራከሩ። ጠቡ እየከረረ ሲሄድ የሮማው ወታደራዊ አዛዥም ጳውሎስን ለሁለት እንዳይገነጣጥሉት ፈርቶ ጭፍሮቹ ወርደው ከመካከላቸው እንዲነጥቁት ወደ ሰፈሩም እንዲያገቡት አዘዘ። በሁለተኛውም ሌሊት ጌታ ባጠገቡ ቆሞ ጳውሎስን በኢየሩሳሌም ስለ ጌታ እንደመሰከረ እንዲሁ በሮምም እንደሚመሰክርለት ገልጾ እንዳበረታታው እናያለን። ይህ በጣም አስደናቂ ክፍል ነው!

**የሐዋ. ሥራ 23:12-22 - ሐዋርያው ጳውሎስን የመግደል ሴራ መሃላ**

በዚህ ምንባብ ውስጥ የአይሁድን ስውር የሆነውንና ሐዋርያውን ለመግደል በመሃላ የታሰረውን የግድያ እቅድ እንመለከታለን። መሃላውን የፈጸሙት አርባ የሚሆኑት አይሁዶች እንደሆኑ ከታሪኩ እናያለን። በኢየሱስ ሕይወት እና አገልግሎት ላይ ተመሳሳይ ነገር ተደርጓል፡፡ ይህ መሀላም ጥብቅ የሆነ እንደነበር በሌላ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች ስንመለከተው የእርግማን ኪዳን እንዳደረጉ ይገልጻል። የሐዋርያው ሐዋርያው ጳውሎስ የእህቱ ልጅ (ጎልማሳ) ሴራቸውን እንዴት እንዳወቀ፡ ባይታወቅም፤እግዚአብሔር ነገሩን አቀነባብሮ በጳውሎስ የእህት ልጅና በአንዱ የመቶ አለቃ ፍንጭ ሰጪነት አማካኝነት ጳውሎስ ከግድያው እንደተረፈ እናያለን።

**የሐዋ. ሥራ 23:23-35 - ከኢየሩሳሌም ወደ ቂሳርያ**

ሐዋርያው ጳውሎስ በሮማውያን ሰዓት አቆጣጠር ከምሽቱ ሦስት ሰዓት ላይ አገረ ገዥ ፊሊክስ ወደሚገኝበት ቂሳርያ ደብዳቤ ተጽፎለት፣ በወታደሮች ታጅቦና በፈረስ ተቀምጦ ቂሳርያ እንደደረሳና ከሳሾቹ ሲቀርቡም ጉዳዩ እንደሚታይ ተነግሮት በሄሮድስ ግቢ እንዲጠበቅ ሆነ። ቂሳርያ ከኢየሩሳሌም ወደ 74 ማይል ወይም 120 ኪ.ሜ ያህል ይሆናል።

**የመወያያ ጥያቄዎች**

1. በሐዋ. ሥራ 23፡1 መሰረት ለሐዋርያ ጳውሎስ ንጹህ ህሊና ምን ዓይነት ነው?
2. ከቁጥ. 2-5 ባለው መሰረት የሊቀ ካህናቱና የተከታዮቹ ድርጊት ምን ነበር? የጳውሎስስ ምላሽ ?
3. በሐዋ. ሥራ 23፡6 ላይ በተገለጸው መሰረት አይሁዳውያንን የለያየበት የሐዋርያው ጳውሎስ ጥበብ ምን ነበር?
4. ከቁጥር 7–9 በተጻፈው መሰረት የፈሪሳዊያንና የሰዱቃዊያንን እምነት አብራሩ
5. ቁጥ. 11 ለጳውሎስ ሕይወትና አገልግሎት ምን ጥቅም አለው ትላላችሁ? አካፍሉ?
6. የሐዋ. ሥራ 23፡12-21 ባለው መሰረት ጳውሎስ ከግድያ ሴራው ያመለጠው እንዴት ነበር?
7. የጦር አዛዡ (23፡23-33) ስለ ጳውሎስ የነበረው አቋም ምን ነበር?
8. ከዛሬው ጥናት ሌላ የተረዳችሁት ነገሮች ካለ አካፍሉ።

## መ ደ ም ደ ሚ ያ

ከሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 23 እንደምንረዳው ጳውሎስ እንደ መልካም አገልጋይ በበጎ ሕሊና በሰው ፊት ልቡ ሳይፈርድበት እያገለገለ ይኖር ነበር። ምንም እንኳን ስደት ቢነሳበትም ሆነ ቢመታም ደግሞም ለሞት የሚያደርሰው ሴራ ቢሴርበትም ጌታ የመውጫውን መንገድ አዘጋጅቶለት አምልጧል። ደግሞም ለወደፊቱ አገልግሎቱ የሚያበረታታውን አግኝቶአል። ይህ ለኛ ሕይወትና አገልግሎት ጥሩ ምሳሌ ነው።

**ጥናት አስራ ስምንት**

**የንባብ ክፍል፡** የሐዋ. *ሥራ* 24:1-27

**ርዕስ፡** በተከፈተ በር ወይም ዕድል ሁሉ ወንጌልን ማበሰር

***ዓላማ፡-***

በከሳሾች ፊት በጥበብ ወይም በመንፈስ መመላለስና በተገኘው አጋጣሚ ወንጌልን ማብሰር እንደሚቻል ለማሳየት፡-

***መግቢያ***

ባለፈው ጥናታችን የጦር አዛዡ ሉስዮስ ጳውሎስን በዚያ ክሱን ይሚገት ዘንድ ወደ ቂሳርያው አገረ ገዥ ወደ ፊልክስ እንደላከው ተመልክተን ነበር። ምንም እንኳን ክሱ መሰረት የሌለው ክስ መሆኑን ከክሱ ጭብጥ መረዳት ባያዳግትም ፤ ፊልክስ ጨካኝ ሰው እና ጉበኛ ስለነበር የጳውሎስን ማስረጃ ከሰማ በኋላ እንኳን እውነቱን እያወቀ ከእስር አልፈታውም። በዚህ ጥናት ሐዋርያው ጳውሎስ በቂሣርያ እስር ቤት በገዡ ፊልክስ ፊት እንዴት እንዳሳለፈ እናያለን። ፊልክስ የሮማውያን ገዥ ሲሆን የአይሁዳዊት ሚስቱ ስም ድሩስላ ትባላለች።

**የክፍሉ ማብራሪያ**

የሐዋ. *ሥራ* 24:1-27

**24:1-4 -** የጳውሎስ ከሳሾች ስብጥር ፡-

ሊቀ ካህኑ ሐናንያ፣ አንዳንድ የአይሁድ ሽማግሌዎችና ጠርጡለስ የተባለ ጠበቃ ሆነው ጳውሎስን ከሄሮድስ ግቢ በማስመጣት ለክስ ሲያቀርቡትና በአገረ ገዥ ፊልክስ ፊት ሲከሱት እንመለከታለን። ደግሞም "ብዙ ሰላም ስለምናገኝ" በሚል ዘዴ የአይሁድ ፅንፈኞችን አመፅ ፊልክስ መቆጣጠሩን እየመሰከሩለት እና ጳውሎስንም እንደ አመጸኛ እንዲፈርድበት እያነሳሱት መሆኑን እንገነዘባለን።

**ቁጥር 5-9** ባለው ክፍል ደግሞ ጠበቃቸው ጠርጡለስ "በዓለም ሁሉ" ብሎ በመጥቀስ የጳውሎስ አገልግሎት የደረሰበትን የሮማውያን ግዛት እና ሌሎችንም እንዳዳረሰ እያሳየ፤ የኢየሱስ ተከታዮች ትምህርትን የሚመራ ቀንደኛ መሆኑን **"የናዝራውያን ወገን"** በማለት ያመላክታል። አይሁድም የጠርጡለስን ሙግት በአንድ ድምጽ ሲደግፉ እናያለን።

***ሐዋ. ሥራ* 24፡10-21 -** የአባቶቻችንን አምላክ አመልካለሁ፡-

በዚህ ክፍል ሐዋርያው ጳውሎስ በኢየሩሳሌም ያደረገው ሁሉ የአይሁድን ሃይማኖታዊ ሥርዓት የጠበቀ እና ተቀባይነት የነበረው እንደሆነ አስረግጦ ያስረዳል። ደግሞም ጳውሎስ "በህግ እና በነቢያት" እያለ የብሉይ ኪዳን መፅሐፍት ዓይነቶችን እንደሚያምን በመጥቀስ ሃይማኖታዊ ትንታኔ ለከሳሾቹ ሲሰጥ እንመለከታለን። በተጨማሪም ጻድቃንና ኃጥአን ከሙታን ይነሱ ዘንድ በእግዚአብሔር ዘንድ ያለውን ተስፋ አስገንዝቧል። አሁንም በንጹህ ህሊና እንደሚኖር ደግሞ ገልጿል።

***ሐዋ. ሥራ* 24፡21-27 -** ግንዛቤ ብቻውን አያድንም፡-

ፊልክስ ስለ ኢየሱስና ስለ ክርስቶስት በቂ የሆነ ግንዛቤ ነበረው። በተጨማሪም ባለቤቱ አይሁዳዊት ነበረች (ሐዋ 24፡24። በመሆኑም የአይሁዳውያንን ሃይማኖት እና ሥርዓቶቻቸውንም ጠንቅቆ ያውቃል፡፡ ነገር ግን የክርስትና ሃይማኖት ለሮማውያን ገዥዎች የፓለቲካ ጥያቄ ባለመሆኑ ትኩረት አይሰጡትም ነበር፡፡ ሆኖም ሐዋርያው ጳውሎስ ለፊልክስ እና ላባለቤቱ ለድሩሲላ ወንጌልን በግልፅ ለመስበክ እድል አግኝቶ ተጠቅሞበታል። ነገር ግን ፊልክስ በልቡ እውነት እንደሆነ ቢረዳም ገንዘብ ከጳውሎስ ለመቀበል መፈለጉ በስልጣን ጥቅም መፈለጉን ያሳያል፡፡

**የመወያያ ጥያቄዎች**

1. የሐዋ. ሥራ 24፡1-4 መሰረት የጳውሎስን ከሳሾች ስብጥር ይዘርዝሩ
2. የሐዋ. ሥራ 24፡2-8 ባለው መሰረት የጠበቃውን የክስ ጭብጥ ሀሳብ ይዘርዝሩ
3. ጳውሎስ ከቁጥ. 9-13 በጠቀሰው መሰረት አይሁድ ማስረጃ ማቅረብ የማይችሉት በምን ላይ ነው?
4. ከቁጥ 14-16 በተጻፈው መሰረት ጳውሎስ "አመልካለሁ"፣ "አምናለሁ" እና "ተስፋ አለኝ" ያላቸውን ነገሮች በዝርዝር ተወያዩ
5. ከቁጥ. 17-21 ያለው የጳውሎስ ጭብጥ ንግግር ምን ነበር?
6. በቁጥ. 22-26 መሰረት ፊልክስ የጌታን መንገድ በሚገባ አውቆ እያለ ለምን ጌታን አልተከተለም?
7. ከቁጥ. 2-3 እና ከቁጥ. 24-27 ባለው መሰረት የአገር ገዡ ፊልክስ ምን ዓይነት ገዥ ነበር? ሥልጣኑንስ ሲያበቃ በማን ተተካ? አካፍሉ።
8. ሐዋርያው ጳውሎስ በማንኛው ሁኔታና ገጠመኞች ትኩረቱ ምን ነበር? እኛስ ምን እንማራለን? ምንስ እናድርግ?

**መ ደ ም ደ ሚ ያ**

በዚህ ጥናት እንዳየነው ሐዋርያው ጳውሎስ ቂሳርያ በነበረው ሙግት እንደሌላውም ጊዜ እድሉን ተጠቅሞ ክርስቶስን ሲሰብክ እናያለን። ከዚህም የምንማረው በማንኛውም ሁኔታ ጌታን በእውቀት መስበክ እንዳለብን እንረዳለን።

## ጥናት አስራ ዘጠኝ

## የንባብ ክፍል፡- የሐዋ. ሥራ 25:1-27

**ርዕስ፡** ለከሳሾች በእውነት ላይ የተመሰረተ የመከላከያ መልስን መስጠት

***ዓላማ፡-***

***በጥበብና በእግዚአብሔር መንፈስ በመመራት ከሆነ*** *ፍትህን ለማግኘት በሕግ ፊት መከራከርም ሆነ ይግባኝ ማለት የክርስቲያንም መብት መሆኑንና በዚያም ክርስቶስን መስበክ እንደሚቻል ለማሳየት፡-*

***መግቢያ***

*ሐዋርያው ጳውሎስ ምንም እንኳን በበጎ ህሊና የተከሰሰበት ጉዳይ መሰረት አልባ መሆኑን ቢያስረዳም ሆነ ከሳሾቹም ለሙግታቸው ጭብጥ ማስረጃ ማቅረብ ባይችሉም እርሱ ግን አልተፈታም። በሌላ በኩል ደግሞም በሮም ግዛት ሁሉ በአስተዳደር ላይ የነበሩ ገዥዎች ሲቀየሩ እስረኞች ይለቀቁ ነበር፤ ነገር ግን ጳውሎስ አለመለቀቁ የሮምን መንግስት ሕግጋት ኢ-ፍታዊነትና መላላትን ያሳየናል። በዚህ ምዕራፍ ፊስጦስ በፊልክስ ቦታ እንደተተካ ክፍሉ ይነግረናል።*

*ፊስጦስ ከፊልክስ ቀጥሎ የነገሰው ሲሆን ጥሩ ስዕብና የነበረው ቢሆንም በሮማዊያን የፖለቲካ አመራር ስለሚመራ እንደፈለገ ማድረግ አይችልም ነበር። እርሱ በኢየሩሳሌም ሳለ የካህናት አለቆችና የአይሁድ መሪዎች ፊቱ ቀርበው ጳውሎስን መንገድ ላይ ለመግደል በማሴር ከቂሳሪያ ወደ ኢየሩሳሌም እንዲያመጣላቸው ቢፈልጉም ሳይሆንላቸው እንደቀረና ጳውሎስ በቂሳርያ ጉዳዩን እንዲያስረዳ የተደረገ ሲሆን በመቀጠልም ፊስጦስ የንጉስ አግሪጳን ምክር ጠይቆ ሲወያዩና በስተመጨረሻም የሐዋርያው ጳውሎስን ወደ ሮም ይገባኝ እንደተቀበለና ሌሎችንም ነገሮች በዚህ ጥናት እናያለን።*

***የክፍሉ አጭር ማብራሪያ***

***ሐዋ. ሥራ* 25:1-27**

*የሐዋ. ሥራ* 25:1-8፡- **"*የፈጸምኩት በደል የለም*"**

*የታሰረው ሐዋርያው ጳውሎስና ከሳሾቹ የካህናት አለቆች እንዲሁም የአይሁድ መሪዎች በፊልክስ ቦታ በተተካው ከፊስጦስ ጋር ወደ ቂሳርያ በመውረድ በጳውሎስ ላይ የሀሰት ክስ ማቅረብ እንደጀመሩና ጳውሎስም በምላሹ የአይሁድን ሕግ እንዳልጣሰ፣ ቤተ መቅደስንም ይሁን ቄሳርን እንዳልበደለ የመከላከያ መልስ ሲሰጥ እናያለን።*

*የሐዋ. ሥራ* 25፡ 9-11፡- **"*ይግባኝ ብያለሁ*"**

*ፊስጦስ አይሁድን ለማስደሰት ፈልጎ ጳውሎስ ወደ ኢየሩሳሌም ወርዶ እንዲሚገት ቢጠይቀውም ምንም የፈጸመው በደል እንደሌለና ወደ ኢየሩሳሌም መሄድ እንደማያስፈልገው ገልጾ፤ እንዲያውም ወደ ቄሳር ይግባኝ እንዳለ በማስታወቁ የፊስጦስን አወንታ ሲያገኝ እንመለከታለን።*

**ቁጥር. 12-21 *የፊስጦስና የአግሪጳ ምክክር***

*ንጉስ ሄሮድስ አግሪጳና እህቱ በርኒቄ ፊስጦስን እጅ ለመንሳት ወደ ቂሳርያ ሲወርዱ ፊስጦስ የጳውሎስን ጉዳይ በዝርዝር ለአግሪጳ ከተናገረ በኋላ እንደ ከሳሾቹ ፍላጎት ወደ ኢየሩሳሌም መውረድ እምቢ እንዳለውና ጉዳዩ በንጉስ ነገስቱ እንዲታይለት ይግባኝ ማለቱን ይገልጽለታል። ይህ አግሪጳ የተባለው የታላቁ ሄሮድስ የልጅ ልጅና ሐዋርያው ያዕቆብን ያስገደለው የንጉስ ሄሮድስ ልጅ ነው። እርሱም ንጉስ ሄሮድስ አግሪጳ ይባላል። እነዚህ የይሁዳ ገዦች ሥልጣን ፍለጋ ነፍስ ገዳዮች እንደሆኑ ግልጽ ነው።*

**ቁጥር 23-26፡- *እስረኛና የክሱ ምክንያት***

በዚህ ክፍል እነ አግሪጳና ሹማምንቱ በተሰበሰቡበት አዳራሽ ፊስጦስ ጳውሎስ እንዲቀርብ ካደረገ በኋላ ለተሰብሳቢው ጳውሎስ ለሞት የሚያደርሰው ጭብጥ ወንጀል ባይኖርበትም አይሁድ ሞቱን እንደሚፈልጉ ከገለጸ በኋላ ጳውሎስ ደግሞ ወደ ቄሳር ይግባኝ በማለቱ ፊስጦስ መርምሮ የሚጽፈውን ነገር ካገኘ በኋላ ወደ ቄሳር እንደሚልከው ውሳኔውን ሲያሳውቅ እንመለከታለን።

***የመወያያ ጥያቄዎች***

1. በሐዋ. 25:27 መሰረት አይሁድን ለማስደሰት ለሁለት ዓመታት ያህል ጳውሎስን አስሮ የተወው ማን ነበር?ምን ዓይነት ማንነት ያለው ይመስላችሁሃል? በቦታውስ የተተካው ማን እንደሆነ አስረዱ።
2. በሐዋ.ሥራ 25:1-3 መሰረት የአይሁድ መሪዎችና የካህናት አለቆች ፍላጎታቸው ምን ነበር? አካፍሉ።
3. ከቁጥር 4-7 እንደምንገነዘበው ሐዋርያ ጳውሎስን በተመለከተ የፊስጦስ የመጀመሪያው አቋም ምን ይመስላል? አብራሩ።
4. ሐዋ ጳውሎስ በቁ.9-11 መሰረት ለፊስጦስ የሰጠውን ምላሽ ለቡድናችሁ አብራሩ።
5. በቁጥር 11 መሰረት "ከሞት ልዳን አልልም" እና "ማንም አሳልፎ ሊሰጠኝ አይችልም" የሚለውን በማነጻጸር ተወያዩ። ምን ማለቱ ነው?
6. ሐዋ.ሥራ 25፡13-16 በተገለጸው መሰረት የአይሁዳዊያንን ፍላጎትና የፊስጦስን አቋም አብራሩ።
7. በቁጥር. 19 መሰረት አይሁድን እና ሊቀካህናቱን ያበሳጨው የጳውሎስ አንኳር ንግግር ምን ነበር?
8. አግሪጳ በቁጥር 22 መሰረት ጳውሎስ ስለ ምን ሲናገር ለመስማት የፈለገ ይመስላል?አግሪጳ ማን ነው?
9. የሐዋ. ሥራ 25፡23-27 መሰረት ፊስጦስ ማድረግ የፈለገውን ነገር አካፍሉ
10. ከዛሬው ጥናት ምን ጭብጥ ነገር ተማሩ?

***መ ደ ም ደ ሚ ያ***

በዚህ በጳውሎስና በከሳሾቹ ፊት በነበረው ሙግት እንደተረዳነው ሐዋርያው ብቻውን አይሁዳዊያንና ሊቀ ካህናት በሀሰት ክስ ሲወነጅሉትም ሆነ አንዳንድ ጊዜ በፍርድ ወንበር የተቀመጡት ባለሥልጣናትም ለሌላው ወግነው ፍርድን ሊያጣምሙ ሲፈልጉ ጌታውን ታምኖና እውነትን ተመርኩዞ ይግባኝ በማለት ንክች እንዳያደርጉት እንዳደረጋቸው ተመልክተናል። ሕግን የሰጠ አምላካችን በመሆኑ እኛም ሲያጋጥመን እንደዚሁ ማድረግ እንደምንችል ትምህርት ይሰጠናል። ነገር ግን በማንኛውም እድሎች ክርስቶስ መሰበክ ይገባል።

**ጥናት ሃያ**

**ርዕስ፦** *መታዘዝና የወንጌል ጉልበት*

**የንባቡ ክፍል፦** የሐዋርያት *ሥራ* 26:1-32 (የሕይወት *ታሪክ* ምስክርነት በቂሣርያ)

***ዓላማ፦***

የምስራቹን የወንጌል *ቃል* ለማብሰር ስንታዘዝ *ያ*ለንበት ሁኔታ ይሁን የምናልፍበት የመከራ መንገድ በፍጹም ጌታን እንደማይገድበው እና እንደማ*ያ*ግደው ለማሳሰብ፦

***መግቢያ፦***

ሐዋርያው ጳውሎስ ስለ ክሱ ጉዳይ ገለጻ እንዲሰጥ ከንጉስ አግሪጳ ዕድል በተሰጠው ጊዜ እድሉን በመጠቀም እንዴት ከራሱ የህይወት ለውጥ *ጋ*ር አዛምዶ ወንጌልን በድፍረት እንዳበሰረ በዚህ ክፍል ውስጥ እናያለን።

ይህ የሐዋርያው የሕይወቱ ለውጥ *ታሪክ* ምስክርነት ለሶስተኛ ጊዜ የተጻፈ ቦታ ነው ከሐዋ. *ሥራ* 9፣ 22 ጨምሮ። ክፍሉን በአራት ከፍለን እናያለን፦

(1ኛ) 26:1-3 የንጉሱ የመናገር ፈቃድን መስጠት እና የሐዋርያው የመግቢያ ንግግር

(2ኛ) 26:4-11 ሐዋርያው ከመለወጡ በፊት የነበረው የህይወት ታሪክ

(3ኛ) 26፡12-18 ጌታችን **ኢየሱስ ክርስቶስ በደማስቆ መንገድ ለሐዋርያው እንዴት እንደተገለጠ ማስጠንቀቅያው**

(4ኛ) 26፡19-32 የሕይወት ምስክርነቱ ግብና ለገዥዎቹ የቀረበ የሕይወት ጥሪ ግብዣ ናቸው።

**የንባቡ ክፍሉ ማብራሪያ (ሐዋ. *ሥራ* 26:1-32)**

***ሀ. የሐዋርያት ሥራ 26:1-3 የንጉሱ የመናገር ፈቃድን መስጠት እና የሐዋርያው የመግቢያ ንግግር፦***

በዚህ ክፍል ውስጥ ሐዋርያው ጳውሎስ ስለተከሰሰበት ክስ ራሱን ለመከላከል እና የመናገር ፈቃድ ከንጉሱ አግሪጳ የተሰጠውን ዕድል በአግባቡ በመጠቀም ንግግሩን ሲያቀርብ እናያለን። ሐዋርያው በዚህ የመግቢያ ክፍል ንግግሩ ራሱን እንደ እድለኛ አድርጎ ይቆጥራል:: ምክንያቱም ንጉስ አግሪጳ የአይሁድን ሥርዓት እና ክርክርን በሚገባ ስለሚያውቅና ስለሚገነዘብ የክሱን መከለከያ ንግግር ንጉሱ በሚገባ እንደሚገነዘበው ስለተረዳ ነው። በዚህ በተሰጠው የመናገር እድል ሐዋርያው በተጨማሪ ንጉሱን በትዕግስት እንዲያዳምጠው ሲለምነው እንመለከታለን።

***ለ. የሐዋርያት ሥራ 26:4-11 ሐዋርያው ከመለወጡ በፊት የነበረው የህይወት ታሪክ***

ሐዋርያው በዚህ የቀድሞው የህይወት ታሪክ ምስክርነት ብዙ ነጥቦችን በማንሳት እና በመዘርዘር ይናገራል። በዚሁ ንግግሩ ከልጅነቱ ጀምሮ በሚኖርበትም ሀገር ሆነ በኢየሩሳሌም እንዴት እንደኖረ እና አይሁድ በሚገባ እንደሚያውቁት በመናገር ይጀምራል። ሐዋርያው ንግግሩን በመቀጠል ስለክሱ ተጨባጭ ሁኔታ ከማንሳቱም ባሻገር ቁጥር 5 ላይ ህግን በመጠበቅ የሚተ*ጋ* ፈሪሳዊ እንደነበረ፣ የኢየሱስን ስም በመቃወም እጅግ ብዙ ነገር ያደርግ እንደነበርና እንዲሁም ከካህናት አለቆች ስልጣንን በመቀበል ቅዱሳንን በወህኒ ያሳስርና ያስገድል እንደ ነበር ይገልጻል።ይህም ሳይበቃው ከኢየሩሳሌምም ውጪ ቅዱሳንን ያሳድድ እንደ ነበር በዚህ ክፍል ውስጥ ሐዋርያው በዝርዝር ያብራራል።

***ሐ. ሐዋርያት ሥራ 26፡12-18 ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በደማስቆ መንገድ ለሐዋርያው እንዴት እንደተገለጠና ማስጠንቀቂያው፦***

ሐዋርያው ከካህናት አለቆች ስልጣንና ትዕዛዝ ተቀብሎ በደማስቆ መንገድ ላይ በሜድ ላይ እያለ፤ የሚያስገርምና ያልታሰበ ክስተት በህይወቱ ተከሰተ። ከጸሐይ ብሩህነት የበለጠ ብርሃን ሲበራ አየ። በዚህን ጊዜ እርሱና በዙሪያው ያሉ ሁሉ በምድር ላይ ወደቁ። በዚህ ሁኔታ ውስጥ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሳውልን "ለምን ታሳድደኛለህ?" በማለት የራሱን ማንነት በግልጥ ከማስረዳቱም በላይ ኢየሱስ ለሐዋርያው የወንጌል ተልዕኮ እንደሰጠው በሐዋ.ሥራ 26፡15-18 እንመለከታለን።

መ. ሐዋርያት ሥራ 26፡ 19-32 የሕይወት ምስክርነቱ ግብና ለገዥዎች የቀረበ የሕይወት ጥሪ ግብዣ

በዚህ ክፍል ውስጥ ብዙ ለወንጌል ስርጭት የሚረዱ ድንቅ ሀሳቦች ታጭቅው እንመለከታለን። ከቁጥር 19-23 **"ንጉሥ አግሪጳ ሆይ፥ ስለዚህ ከሰማይ የታየኝን ራእይ እምቢ አላልሁም"** ብሎ በመጀመር ሐዋርያው የተሰጠውን ተልዕኮ በመታዘዝና የምስራቹን ወንጌል በመናገር ንግግሩን መቀጠሉን ይህ ክፍል ያስረዳናል። በዚሁ ክፍል ሐዋርያው በወንጌል ምስክርነቱ የተነሳ በንግግሩ እንደ እብድ ቢቆጥሩትም የወንጌሉ ጉልበት ግን ንጉስ አግሪጳን ልቡን እንደነካውና ወንጌልን ለማመን ጫፍ መድረሱን እንዲህ በማለት በቁጥር 28 ላይ ገልጦታል"**አግሪጳም ጳውሎስን፡- በጥቂት ክርስቲያን ልታደርገኝ ትወዳለህ አለው?"** ሐዋርያው ግን ወንጌሉ ለእርሱ ብቻ ሳይሆን ምስክርነቱን ለሚያዳምጡ ሁሉ መሆኑን አስረግጦ ሲነግረው እንመለከታለን። በመጨረሻም የመጽሐፉ ክፍል የክሱን ከንቱነትና የሐዋርያውን ንጽህናን ከማመልከቱም በላይ እስከ ሮም ድረስ ወንጌልን ለማብሰር የሚያስገርም በር እንደተከፈተ ክፍሉ ይናገራል።

**የመወያያ ጥያቄዎች**

1. ሐዋ. ሥራ 26፡1 መሰረት በማድረግ ሐዋርያው ተከሶ በንጉሱ ፊት በቆመበት ሰዓት ስለክሱ እንዲናገር የፈቀደለት ማን ነው? ስለማንስ እንዲናገር ተፈቀደለት?
2. ከቁ.2-3 በዚህ ክፍል ሐዋርያው ራሴን እጅግ እንደተመርቀ (እድለኛ) አድርጌ እቆጥራለሁ፤ ያለበት ምክንያት ምን ይመስላችሁሃል? በተጨማሪም ሐዋርያው በዚሁ ክፍል ንጉሱን ምን ሲለምነው እናያለን? ለምን?
3. 26፡4-5 ያለውን ክፍል በማንበብ አይሁድ ስለሐዋርያው ስለነበራቸው እውቀትና ግንዛቤ በማብራራት ለጥናት ቡድንህ አስረዳ/አስረጂ።
4. ሐዋ. ሥራ 26፡6-8 መሰረት በማድረግ አይሁድ በሐዋርያው ላይ የመሰረቱትን ክስ መሰረታዊ ጭብጡን በማንሳት በስፋት ተወያዩበት።
5. ከቁጥር 9-11 በማንበብ በክፍሉ ሐዋርያው ምን ያድርግ እንደነበረና ቁ.10 ላይ እንደሚናገረው ማንን በማስገደል እንደተባበረ አካፍሉ (ሐዋ. ሥራ 8:1)።
6. በሐዋ.ሥራ 26፡ 12-18 የሐዋርያው ጳውሎስን የህይወት ለውጥ በዝርዝር ተወያዩ።
7. በቁጥር 19-23 ሐዋርያው **"ንጉሥ አግሪጳ ሆይ፥ ስለዚህ ከሰማይ የታየኝን ራእይ እምቢ አላልሁም"** በማለት ይናገራል። ለመሆኑ ሐዋርያው ያየው ራዕይና ምላሹ ምን ነበር?
8. በሐዋ.ሥራ 26፡24-32 የሐዋርያው የወንጌል ምስክርነት የድል ምዕራፍ በዚህ ክፍል እንዴት እንደ ነበረና የበርንቄና አግሪጳስ ስለ ሐዋርያው የነበራቸውን አመለካከት ተወያዩበት።
9. በዚህ የጥናት ክፍል ውስጥ ለወንጌል ስርጭት ይጠቅማል የምትሉትን ዘዴዎች በመጥቀስ ተወያዩባቸው።እንዴትስ እንደዚህ ደፋር ሊሆን ቻለ? እንዲሁም ለሚቀጥለው ሳምንት ሰዎችን በድፍረት መስከረን ምን እንደገጠመን እናካፍል?

**መ ደ ም ደ ሚ ያ**

የወንጌልን እሳት ከመቀጣጠል የሚያግደው አንዳችም ሀይል እንደሌለ መጽሐፍ ቅዱስ ትልቅ ምስክር ነው:: በየዘመናቱ ብዙዎች ይህን የወንጌል እሳት ለማቆም ሞክረው አቅቷቸዋል:: በዚያው መጠን ወንጌሉ ግን በእርሱ በታመኑትና ለእርሱ በታዘዙት ወንጌሉ ከዘመን ዘመን በቅብብል ዘመናትን ተሻግሮ እዚህ ትውልድ ላይ ደርሷል። ይህ ትውልድ ደግሞ ይህን የወንጌል እሳት የማቀጣጠል አደራ አለበት። ስለዚህ በዙሪያው እንደ ደመና የከበቡትን የእምነት አርበኞች በመመልከት ወንጌልን የማስቀጠል ትልቅ ሥራ እንዳለበት ለአፍታም ሊዘናጋ አይገባም።

ጥናት ሃያ አንድ

**የንባቡ ክፍል፡-** የሐዋ. ሥራ 27:1-44 (ጉዞ ወደ ሮም በጊዜው የዓለም ዋና ማዕከል)

**ርዕስ፡- የእግዚአብሔር** ቃል ተስፋና ተፈጻሚነቱ

**ዓላማ፡-**እግዚአብሔር ለተናገረው ቃል ታማኝ በመሆንና ቃሉን በመጠበቅ ያቀደልንን ስፍራ እስከንደርስ ከነናችን በመቆም እንደሚያበረታታንና እንደሚረዳን ለማስገንዘብ

***መግቢያ***

ባለፈው ጥናታችን ሐዋርያው ጳውሎስ በቂሳርያ ምንም ጥፋት እንዳልተገኘበትና ወደ ቄሳር ይግባኝ በማለቱ ጉዞውን ወደ ሮም መሄድ እንደሚችል መወሰኑን አይተናል። በዚህ ጥናታችን ደግሞ ወደ ሮም ጉዞ በሚያደርግበት ጊዜ ሰለ ሐዋርያው አስቸጋሪ ጉዞና በጉዞው ስለገጠመው ተግዳሮት እና የእግዚአብሔር ጥበቃ እናያለን።

**የንባቡ ክፍል ማብራርያ**

***ሀ. ሐዋ. ሥራ 27፡1-12 ወደ ኢጣልያ ወይም ወደ ሮም የሚደረገው ጉዞ መጀመር እና ስለጉዞው አደገኝነት የሐዋርያው ማስጠንቀቅያ***

በ27፡1 ላይ **"ወደ ኢጣሊያም በመርከብ እንሄድ ዘንድ በተቈረጠ ጊዜ፥ ጳውሎስንና ሌሎችን እስረኞች ከአውግስጦስ ጭፍራ ለነበረ ዩልዮስ ለሚሉት ለመቶ አለቃ አሳልፈው ሰጡአቸው"** በማለት የጉዞውን መጀመር የሐዋርያት ሥራ ጸሀፊ ይናገራል። አውግስጦስ **ሮምን ወይም ብዙውን የዓለምን ክፍል ለመጀመሪያ ጊዜ ከ27 ዓ.ዓለም -14 ዓ/ምህረት ማለትም እስከሞተበት ዓመት ይገዛ የነበረ በዓለም ላይ ከተነሱ ታላላቅ ነገሥታት አንዱ የሆነ ሮማዊ ንጉስ።** ይህን የኢጣልያ ወይም የሮም ጉዞ ስናስብ በሐዋ.ሥራ 1፡8 ላይ **"እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ"** የሚለው ቃል ሊፈጸም የመጀመሪያው የጉዞ ምዕራፍ እንደሆነ ያመላክተናል። በዚህ የወንጌል ጉዞ ላይ የመቄዶንያም ሰው በተሰሎንቄ የሚኖረው አርስጥሮኮስ (ቆላስያስ 4፡10) አብሮት እንደተጓዘ ይሄው ክፍል ያስረዳናል። በተጨማሪም በዚህ የመርከብ ጉዞ ላይ በሐዋ.ሥራ 27፡3 ላይ ሲዶና በደረሱ ጊዜ ዩልዮስ ለሐዋርያው ቸርነት በማድረጉ እርዳታን ይቀበል ዘንድ ወደ ወዳጆቹ እንደ ሄደ እንመለከታለን።

በዚህ ጉዞ ብዙ ጊዜን በባህር ላይ በማሳለፋቸው አደገኛው የክረምት መግቢያ ወቅት ስለነበር የጉዞውን አደገኝነት በ27፡10 ላይ ሐዋርያ እንዲህ በማለት ሲመክር እንመለከታለን **"እናንተ ሰዎች ሆይ፥ ይህ ጉዞ በጥፋትና በብዙ ጉዳት እንዲሆን አያለሁ፤ ጥፋቱም በገዛ ሕይወታችን ነው እንጂ በጭነቱና በመርከቡ ብቻ አይደለም ብሎ መከራቸው"** የመቶ አለቃው ግን በሐዋርያው ምክር ይልቅ የመርከቡን አዛዥና የመርከቡን ባላቤት በማመን ለሐዋርያው ጆሮ ሳይሰጠው መጓዝ ቀጠሉ።

**ለ. ሐዋ. ሥራ 27፡13-39 መከራ የበዛበት አደገኛው ጉዞ እና የሐዋርያው የማጽናኛ ምክር**

መጠነኛ የደቡብ ነፋስ በነፈሰ ጊዜ መንገዳቸው የተቃና ስለመሰላቸው መህልቁን ነቅለው ጉዞአቸውን በቀርጤስ አጠገብ ጥግጥጉን በመጓዝ ቀጠሉ። ነገር ግን ብዙም ሳይጓዙ አውራቂስ የሚሉት ምስራቃዊ ነፋስ በመንፈሱ መርከቡን ከቁጥጥር ውጭ በማድረግ ለተወሰነ ጊዜ ነፋሱ እየነዳ ወሰዳቸው። ነገር ግን ቄዳ በደረሱ ጊዜ መርከቢቱን ለመቆጣጠር ቻሉ፡ ፡ የሐዋርያት ሥራ ጸሐፊ የጉዞውን አደገኝነት እንዲህ በማለት ከቁጥር 18-19 ይገልጠዋል **"ነፋሱም በርትቶ ሲያስጨንቀን በማግሥቱ ከጭነቱ ወደ ባሕር ይጥሉ ነበር፥በሦስተኛውም ቀን የመርከቡን ዕቃ በእጃችን ወረወርን። ብዙ ቀንም ፀሐይን ከዋክብትንም ሳናይ ትልቅ ነፋስም ሲበረታብን ጊዜ፥ ወደ ፊት እንድናለን የማለት ተስፋ ሁሉ ተቈረጠ።"** ከጉዞው ክብደት በላይ ያለ ምግብ በረሃብ ብዙ ቀንን አሳለፉ፡፡ ነገር ግን ሐዋርያው በብዙ ማጽናናት እንዲህ በማለት ያበረታቸው ነበር

**"አሁንም፦ አይዞአችሁ ብዬ እመክራችኋለሁ፤ ይህ መርከብ እንጂ ከእናንተ አንድ ነፍስ እንኳ አይጠፋምና። እርሱ የምሆንና ደግሞ የማመልከው የእግዚአብሔር መልአክ በዚች ሌሊት በአጠገቤ ቆሞ ነበርና፥ እርሱም፦ጳውሎስ ሆይ፥ አትፍራ፤ በቄሣር ፊት ልትቆም ይገባሃል፤ እነሆም፥ እግዚአብሔር ከአንተ ጋር የሚሄዱትን ሁሉ ሰጥቶሃል አለኝ።ስለዚህ እናንተ ሰዎች ሆይ፥ አይዞአችሁ፤ እንደ ተናገረኝ እንዲሁ እንዲሆን እግዚአብሔርን አምናለሁና።" በማለት ከርሱ ጋር የሚጓዙትን ሰዎች ከጌታ ባገኘው ብርታት ሲያጽናናቸው እንመለከታለን።**

### *ሐ. ሐዋ. ሥራ 27፡39-44 የመርከቡ ተሳፋሪዎች በሙሉ ከአደጋ መትረፍ*

በነጋውም መልሕቆቹን ፈትተው መጓዝ እንደጀመሩ መርከቡ ከተከመረ አሸዋ ጋር በመላተሙ የመርከቡ የፊተኛው ክፍል በአሸዋው ተይዞ መርከቡ ወደፊት ለመሔድ አቃተው:: በተጨማሪም የኋለኛው የመርከብ ክፍል በማዕበሉ ስለተመታ መሰባበር ጀመረ። በዚህን ጊዜ ወታደሮቹ ማንም እስረኛ ለማምለጥ ቢሞክር ለመግደል ተስማሙ። ነገር ግን የወንጌሉ የምስራች ቃል ግን እስከ አለም ዳርቻ መሰማት ስለነበረበት የመቶ አለቃው ግን ሐዋርያው እንዲተርፍ ስለፈለገ ወታደሮቹ ያሰቡትን ሀሳብ ከለከለ። በመጨረሻም ጌታ ለሐዋርያው በቁጥ 23-26 ላይ እንዲህ ብሎ እንደተናገረው **"...የእርሱ የምሆንና ደግሞ የማመልከው የእግዚአብሔር መልአክ በዚች ሌሊት በአጠገቤ ቆሞ ነበርና፥ እርሱም፦ጳውሎስ ሆይ፥ አትፍራ፤ በቄሣር ፊት ልትቆም ይገባሃል፤ እነሆም፥ እግዚአብሔር ከአንተ ጋር የሚሄዱትን ሁሉ ሰጥቶሃል** አለኝ።" ይህም ቃል እውን ይሆን ዘንድ ዋና መዋኘት የሚችል በዋና፤ የቀረው ደግሞ በመርከቡ ስብርባሪዎች በመንሳፈፍ ሁሉም ከሞት ተርፈው ወደ ዳር ወጡ።

***የመወያያ ጥያቄዎች***

1. በሐዋ.ሥራ 27፡1 ላይ የሚናገረውን የኢጣልያ የጉዞ ጅማሬ እና በሐዋ.ሥራ 1፡8 ላይ ያለውን ሐሳብ በማቀናጀት የተረዳኸውን ሐሳብ አብራሩ።
2. በ27:2 ላይ አርስጥሮኮስ ተብሎ የተጠቀሰው ሰው በቆላስያስ 4:10 ሐዋ. ሥራ 19:29 እንዲሁም ፊልሞና 1:4 ያለውን ሐሳብ በማንበብ ከሐዋርያው ጋር የነበረውን ቁርኝት ተናጋገሩ።
3. በሐዋ.ሥራ 27፡3 ላይ እነ ሐዋርያው ጳውሎስ ሲዶና በደረሱ ጊዜ የሆነው መልካም ነገር ምንድን ነው?
4. 27:1-9 ይሁን ከዚያም በኋላ ባሉት ቁጥሮች ታሪክ ጸኃፊው ከሐዋርያው ጳውሎስ ጋር እንደነበረ ምን ምልከታ አለ። አስረዱ።
5. በ27፡10 መሠረት በማንበብ የጉዞውን አደገኝነት ሐዋርያው እንዴት ነው የገለጠው? የመቶ አለቃው አመለካከትስ ምን ይመስል ነበር?
6. የሐዋርያት ሥራ ጸኃፊ በሐዋ.ሥራ 27፡18-19 ስለ ጉዞው ክብደት በምን መልኩ እንደገለጠው የተረዳኸውን ለጥናት ቡድንህ አስረዳ።
7. ሐዋርያው ጳውሎስ በሐዋ.ሥራ 27፡22-25 ከጌታ የተቀበለው መልእክት ምን ነበር? ይህ መልእክት ከጉዞው ጋር ያለው ግንኙነት ምን ይመስልሃል?
8. በሐዋ.ሥራ 27፡42 ላይ የወታደሮቹ ምክር ምን ነበር? ከዚህ ምክር ሐዋርያው እንዴት ሊተርፍ ቻለ?
9. በዚህ ጥናት ውስጥ የጌታን ታማኝነትና ጥበቃ እንዴት ትገልጠዋለህ? በአጠቃላይስ ከዛሬው ጥናት ምን እንማራለን?

***መ ደ ም ደ ሚ ያ***

የእግዚአብሔር ቃል ሁል ጊዜም በአሸናፊነት የሚጓዝ፣ዘመን እና ጊዜ የማያግደው እውነት ነው። ነገር ግን እግዚአብሔር ለዚህ ድንቅ ስራው በየዘመናቱ ሰውን ይፈልጋል። መጽሐፍ ቅዱስም እንደሚነግረን እነዚህን ያገኛቸውን ሰዎች በመጠቀም ብዙ ሰዎችን ወደ ራሱ መንግሥት አስገብቷል። ከዛም ባለፈ ወንጌል በብዙ ተጋድሎ ለዛሬው ዘመን ድረስ ደርሷል። በዚህ በእኛ ዘመን ደግሞ አንተን፤ አንቺን እና እኔን ለዚህ ለመንግስቱ የከበረ ስራ ይፈልገናል። ስለዚህ ይህን ትልቅ እድል በመጠቀምና ለእርሱ መታዘዝ ከፊታችን ያለውን እድል በመጠቀም የምስራች የማድረሱን ሩጫ በጥንቃቄ እንሩጥ።

## ጥናት ሃያ ሁለት

**ርዕስ፦** ጌታ የከፈተውን የወንጌል በር በአግባቡ መጠቀም

**የንባቡ ክፍል፦** የሐዋርያት ሥራ 28፡1-31

**ዓላማ**

የእግዚአብሔር ቃል ጊዜ የማይሽረው፣ሥፍራ የማያግደውና ምድራዊ ሥልጣን የማያቆመው መሆኑን በመረዳት ማገልገል እንዳለብን ለማሳሰብ፦

**መግቢያ**

በባለፈው ጥናት ስለ መርከቡ ጉዞ አደገኛነት ተሳፋሪው ከፍርሃት የተነሳ እህል አለመቅመስና የሐዋርያው ህዝቡን ማጽናናት ተመልክተናል። በዚህ ምዕራፍ የሚስዮን ቡድኑ እግዚአብሔር እንደተናገራቸው ከሞት ተርፈው መላጥያ መድረሳቸውንና ከዚያም ወደ ሮም መሄዳቸውን ታሪክ ጻሃፊው መዝግቧል። ስለዚህ በዚህ ጥናታችን ደግሞ በመረከብ ጉዞው ላይ በተለያዩ ሰፍራዎችና በሮም በነበረበት ጊዜ እግዚአብሔር የተናገረውን ነገር በሐዋርያው ሕይወት ሲፈጽምና የእርሱንም የተሳካ የወንጌል አገልግሎት እንመለከታለን።

**የንባቡ ክፍል ማብራርያ**

**ሐዋ. ሥራ 28:1-31**

**ሀ. የሐዋርያው አቀባበል እና አገልግሎት በመላጥያ ደሴት ሐዋ. ሥራ 28፡**1-10

እነ ሐዋርያ ጳውሎስ መላጥያ በምትባል ደሴት በደህና እንደደረሱ <u>አረማውያን</u> ( **ያልተማሩ ወይንም ያልሰለጠኑ ማህበረሰብ እንደሆኑ** የአማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት በገጽ 132 ይናገራል**) ወይም የመላጥያ ሰዎችም** የሚያስደንቅ አቀባበል አደረጉላቸው። ወቅቱ ክረምት እና በጣም ይበርድ ስለነበረ እሳት በማንደድ ተቀባሏቸው። በዚህን ጊዜ ሐዋርያው ብዙ ጭራሮን ወደ እሳቱ በሚጨምርበት ሰዓት ከሙቀቱ የተነሳ እፉኝት ከእሳቱ ወጥታ እጁን ነደፈችው በዚህ ጊዜ የደሴቲቱ ነዋሪዎች በ28፡4-6 ላይ ሐዋርያውን እንዲህ አሉት **"እባብ በእጁ ተንጠልጥላ ባዩ ጊዜ፥ እርስ በርሳቸው፦ ይህ ሰው በእርግጥ ነፍሰ ገዳይ ነው፥ ከባሕርም ስንኳ በደኅና ቢወጣ የእግዚአብሔር ፍርድ በሕይወት ይኖር ዘንድ አልተወውም አሉ።" እርሱ ግን እባቢቱን ወደ እሳት አራገፋት አንዳችም አልጐዳችውም፤እነርሱም፦ ሊያብጥ ወይም ወዲያው ሞቶ ሊወድቅ ነው ብለው ይጠባበቁት ነበር። ብዙ ጊዜ ግን ሲጠባበቁ በእርሱ ላይ የሚያስገርም ነገር ምንም ባላዩ ጊዜ፦ <u>ይህስ አምላክ ነው</u> ብለው አሳባቸውን ለወጡ።"** በዚህ ደሴት ፑፕልዮስ የሚባል ባለጠጋ ለሶስት ቀን በፍቅር ተቀብሎ ባስተናገደበት ቀናቶች በጳውሎስ እጅ እግዚአብሔር አስደናቂ ታምራቶችን አደረገ። የዚህ የከበርቴ ሰው አባት በንዳድ እና በተቅማጥ ታሞ ተኝቶ ነበረና ሐዋርያውም ወደዚህ ሰው በመቅረብ እጁን ጭኖ ስጸልይ እግዚአብሔር ፈወሰው። ከዚህም የተነሳ በደሴቲቱ ታመው የነበሩ ወደ ሐዋርያው በመምጣት ከነበረባቸው ደዌ ነጻ ይሆኑ ነበር።

**ለ. ወደ ሮም ጉዞውን መቀጠል ሐዋ. ሥራ 28፡11-15**

ከሶስት ወር የደሴቲቱ ቆይታ በኋላ በዛው ደሴት ከርሞ በነበረው <u>የዲዮስቆሮስ</u> አርማ ባለው **( የመንታ አምላክ አርማ ሮማውያን ገናና መንግስት በነበሩበት ዘመን እነዚህ መንታ አማልክት ለባህር ጉዞአቸው ልዩ እርዳታ ያደርጉልናል በማለት መርከበኞች ያምኑ ነበር** የአዲስ ኪዳን ማብራርያ ገጽ 340 ይመልከቱ**)።** በእስክንድርያው መርከብ ወደ ሮም ጉዞ ተጀመረ።

ከአንድ ቀንም ጉዞ በኋላ ፑቲዮሉስ ደረሱ። በዚያም አማኞች የሚያስገርም አቀባበል ከማድረጋቸውም በላይ ሰባት ቀን ከእነርሱ ጋር እንዲከርሙ ለመኑአቸው።

### ሐ. የሐዋርያው በሮም መድረስና በህግ ጥበቃ ሥር ሆኖ የነበረው የወንጌል አገልግሎት ሐዋ. ሥራ 28፡16-23

ሐዋርያው ሮም በደረሰ ጊዜ ጳውሎስ ከሚጠብቀው ወታደር ጋር ለብቻው ይቀመጥ ዘንድ መፈቀዱ። የወንጌል ስራን በነጻነት ለመስራት ትልቅ በር ተከፈተለት። ሐዋርያው ሮም ከደረሰ ከሶስት ቀን በኋላ የአይሁድ መሪዎችን በአንድነት ጠርቶ ስለተከሰሰበት ጉዳይና ስለ ክሱም መከላከያ እና ስለእርሱ ንጽህና በደንብ አርጎ አስረዳቸው። ከዚያም በኋላ መሪዎቹ የበለጠ ከእርሱ ለመስማት ሐዋርያውን ቀን በመቅጠር ተለያዩ። በቀጠሮውም ቀን ብዙ ሆነው መጡ። ሐዋርያውም ከጠዋት እስከማታ ለእነርሱ የእግዚአብሔርን መንግስት እየመሰከረ ከሙሴ ህግና ነቢያት እየጠቀሰ ስለ ኢየሱስ አስረዳቸ። በዚህም ስብከት ብዙዎች አመኑ ቀሪዎቹ ሳያምኑ ተመለሱ። ሐዋርያው ሁለት አመት በተቀመጠበት ቤት ሰዎችን በመቀበል የእግዚአብሔርን መንግስት በመስበክ ሳይታክተው ያገለግል ነበር። እግዚአብሔር ገና ሲጠራውና በመካከልም የነገራቸውን ተስፋዎች ፈጸመ። ይህ ደግሞ ከላይ እንደተጠቀሰው የሐዋ ሥራ 1:8ም ይሁን የማቴ 28:19-20 ትዕዛዝ ስኬት ነው። ከዚህ በኋላ ሐዋርያው በሮም ሁለት ዓመታትን ያህል ነጻነት ያለበት እስር እንደነበረና ብዙ ቁም ነገሮችንም እንደሰራ ይነገራል። እንዲሁም ደግሞ በሮሜ ታስሮ እያለ የጻፋቸው መልእክቶች፡-የኤፌሶን፣ የፊልጵስዩስ፣ የቈላስይስ፣ የፊልሞናና የ2ኛ ጢሞቴዎስ ናቸው። 1ጢሞቴዎስና ቲቶ በመካከል ከእስር ተፈቶ ከመቄዶኒያ እንደጻፈ ይነገራል።

***የመወያያ ጥያቄዎች***

1. ሐዋ. ሥራ 28፡1-3 ባለው ክፍል ውስጥ ሐዋርያውና ሌሎች መንገደኞች መላጥያ ደሴት በደረሱ ጊዜ አረማውያን ምን መልካም ነገርን አደረጉላቸው?
2. በሐዋ.ሥራ 28፡4-6 መሰረት በሐዋርያው ጳውሎስ በእባብ መነደፍ ምክንያት የደሴትቱ ሰዎች በመጀመሪያ ምን አሉ? በመጨረሻስ በምን ደመደሙ? በዚህ ታሪክ ውስጥ የተማርከውን ለጥናት ቡድንህ አስረዳ።
3. ሐዋ. ሥራ 28፡ 7-13 በማንበብ በደሴቱ አለቃ በፑፕልዮስ የሶስት ቀን የእንግድነት ጊዜ የሐዋርያው አገልግሎት ምን ይመስል ነበር? የሐዋርያው የጸሎት አገልግሎት ምን እንማራለን?
4. ሐዋ. ሥራ 28፡14-15 ከ 3ኛ ዮሐንስ 5-6 ጋር በማዛመድ ስለ ቅዱሳን መልካም አቀባበልና መስተንግዶ ምን ትረዳላችሁ? እናንተስ ይህን ለማድረግ ምን ያህል ዝግጁ ናችሁ?
5. ሐዋ. ሥራ 28፡16 ላይ **“ወደ ሮሜም በገባን ጊዜ ጳውሎስ ከሚጠብቀው ወታደር ጋር ለብቻው ይቀመጥ ዘንድ ተፈቀደለት”** ይላል። ይህ መሆኑ ለሐዋርያው ምን ጠቀመው ብላችሁ ታስባላችሁ?
6. ሐዋ. ሥራ 28፡17-22 ሐዋርያው ሮም በገባ ከሶስት ቀን በኋላ የአይሁድ ታላላቆችን ጠርቶ ምን አደረገ? የእነርሱስ መልስ ምን ነበር?
7. ሐዋ. ሥራ 28፡23-29 መሰረት በማድረግ ከአይሁድ አለቆች ቀን ቀጥረው ከተገናኙ በኋላ የሆነውን ነገር በዝርዝር አስረዳ?
8. በሐዋ.ሥራ 28፡30-31 ላይ ቀሪ አገልግሎቱ ምን ይመስል ነበር?
9. በዚህ የጥናት ክፍል ውስጥ ያገኘሽውን ቀሪ እውነት ለጥናት ቡድንህ አስረዳ?

10. በአጠቃላይ የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ጥናት የተማርነውንና ማድረግ የሚገባንን ነገሮች እናካፍላለን።
11. እንደተመቻችሁ በሚቀጥለው ሳምንት ግሩም የህብረት ጊዜ እንድታደርጉ እናበረታታለን።

***መደምደምያ***

በእርግጥ ጌታን ማገልገል ስለ ስሙ መሰደድ እና መከራን መቀበል ለአማኝ ትልቅ ክብር ነው:: ይህንኑ አገልግሎት ማገልገል ክብር እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ በደንብ አስረግጦ በማስረጃ ይነግረናል:: የማይካደው እውነት ግን የወንጌል አገልግሎት ትልቅ ዋጋ ያስከፍላል። አገልግሎቱ ደግሞ የጌታ ትዛዝ ስለሆነ በመታዘዝ ጌታን ማገልገል ደግሞ ውስጥን በሐሴት የሚሞላ ትልቅ እርካታ አለው። ከዚህም በላይ ደግሞ የክብር ሽልማት እንዳለው መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል። ስለዚህ ይህን ክብር የሞላበትን የበረከት አገልግሎት ጌታን በማገልገል እንደ ሐዋርያው የተሰጠንን የምድር ዘመን ማጠናቀቅ ይገባናል።

**ቡራኬ**

**ይህን ጥናት በትጋት ላዘጋጁት፣ጥናቱ እንዲጠና ቤታቸውን ለሰጡ፣ጥናቱን ለሚመሩ እና ሳይሰላቹ ለሚያስተባብሩ ምስጋናችን እጅግ ብዙ ነው።**

**እናመሰግናለን፤እግዚአብሔር ይባርካችሁ እንላለን!**

በተረፈው ማንኛውም ጥያቄ፣አስተያየትና የሚያበረታታ ቃል ካላችሁ በቀጥታም ይሁን በመሪዎቻችሁ በኩል ንገሩን!


የኢትዮጵያ ወንጌላዊት አማኞች ቤ/ክ ትምህርትና ሥልጠና ክፍል በዳላስ

Pr Getachew Habte (Dr.)

እናመሰግናለን።

Getachew@eebcdallas.org

214-227-1921/214-703-0100

www.eecdallas.org